# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ

# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

# ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

## የወሊሶ  ኦሮሞ ጎሣ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ ትንተና

## ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በባይሤ ከበደ

ሰኔ 2013 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

# የወሊሶ ኦሮሞ ጎሣ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ ትንተና

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ

ጥናት

በባይሤ ከበደ

አማካሪዎች

ዶክተር ለማ ንጋቱ (ዋና አማካሪ)

ዶክተር ምህረት ሳዳሞ (ረዳት አማካሪ)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሐፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

ሰኔ 2013 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የእኔ ወጥ ስራ መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም

ፊርማ

የማስረከቢያ ቀን

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የወሊሶ ኦሮሞ ጎሣ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ ትንተና

በባይሤ ከበደ

ሰኔ 20/2013 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ ፊርማ

------------- ----------------

የዉስጥ ፈታኝ ፊርማ

------------------- -------------

የዉጭ ፈታኝ ፊርማ

------------------- -------------

# ምስጋና

በሁሉም ስራዬ ላይ ጤና እና ሰላም ሰጥቶኝ የረደኝን አምላክ ኣመሰግናለሁ፡፡ ከኢግዚኣብሔር ቀጥሎ በዋናነት ዶክተር ለማ ንጋቱ በስራው መጀመሪያ ላይ ተመካሪዎቻቸውን በሙሉ ሰብስበው የእያንዳንዱን ክንውን ማስረከቢያ ቀናት በውይይት እንድንወስን በማድረጋቸው እና በተቆረጠው ቀን ለማስረከብ ምን ማድረግ እንዳለብን ያላቸውን ልምድ ስላካፈሉን አብዛኞቻችን በጊዜ አጠቃቀም ረገድ ያሉብንን ችግሮች አስወግደን ጥናታችንን እንድናካሂድ ረድተውናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሆሄያት ግድፈት ጀምሮ እያንዳንዱን ችግር በመንቀስ እና የሚስተካከልበትን መንገድ ያለመሰልቸት በመምከር ረቂቅ በማስተካከል እና አስፈላጊውን እርማት በሰዓቱ በመስጠት ላደረጉልኝ ከፍ ያለ እገዛ ረጅም ዕድሜ ተመኝቼ እጅግ የከበረ ምስጋናዬን ላቀርብላቸው እወዳለሁ፡፡ እንዲሁም ሁለተኛ አማካሪዬ ዶክተር ምህረት ሰዳሞ በጥናቴ ያለብኝን ክፍተት እንዳሟለ ላበረከቱልኝ ድጋፍ በጣም ኣመሰግናለሁ፡፡

በመረጃ ስብሰባ ወቅት በጥሩ አቀባበል ተቀብለዉኝ ጊዜያቸዉን ሰጥተው ከእኔ ጋር መረጃ ለመሰብሰብ በየወረዳዎቹና በየቀበሌዎቹ ስጓዙ የነበሩትን የወሊሶ ባህልና ቱርዝም ጽ/ቤት ሠራተኛ አቶ ነገሱ አምዲሳ እና አቶ ሽፈራዉ አሰፋ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ በተለይም የወሊሶ “አባ ገዳ” አቶ ተስፋዬ ቱጂ፣ አቶ ሽፈራው አሰፋ፤ “ሀደ ሲቄ” ወጋየሁ ንጋቱ እና አቶ ሞሮዳ ቶሌራ የነበራችሁን ውድ ጊዜ እየሰዋችሁ ከቀጠሮው ቀን በተጨማሪ በተደጋጋሚ እያገኛችሁኝ ስለ ማህበረሰቡ ባህል እና ታሪክ በሰፊው ስታስረዱኝ ለወገኖቻችሁ ያላችሁን ተቆርቋሪነትና ቅንነት በሰፊው ያሳየኝ በመሆኑ  እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብያለሁ፡፡ የጅማ ዩኒቨርሲቲም የጥናት በጀት ስለፈቀደልኝ ኣመስግናለሁ፡፡

ዉድ ባለቤቴ አቶ ታደለ ጭንድ፤ ልጆቼ ህፃን ጋሩማ እና ኢብስቱ ሁሌም ስራዬን በአግባቡ እንድሰራ የቤት ዉስጥ ስራን በማከናወንና አበረታች ሀሳብ በመስጠት የአቅማችሁን እርደታ ስለደራጋችሁልኝ ከልብ ኣመሰግናለሁ፡፡ ወንድሜ እና እህቶቼ በደወላችሁ ቁጥር "አላለቀም እንዴ!" ስትሉኝ ባያልቅ ሊሰማችሁ የሚችለው ስሜት አስፈርቶኝ በሞራል የተቻለኝን ሁሉ እንዳደርግ ስለረዳኝ ፈጣሪ ዕድሜና ጤና እንዲሰጣችሁ እፀልያለሁ፡፡

## *አጠቃሎ*

*ይህ ጥናት በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ የተደረገ ነው፡፡ የጥናቱ አቢይ ዓላማ የማህበረሰቡን የለቅሶ ስርዓት ከሞት እስከ ግብዓተ መሬት ፍፃሜ ድረስ ያለውን የአከዋወን ሂደት ማሳየትና መተንተን ነው፡፡ ይህንን እና ሌሎች ዝርዝር ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ መረጃዎች የተሰበሰቡት  በሁለት ተፈጥሯዊ አውዶች ላይ ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ እና ስለማህበረሰቡ ባህል ጥልቅ መረጃ አላቸው ተብለው ከታመነባቸው የማህበረሰቡ አባላት ጋር ቃለ-መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማካሄድ ነው፡፡ በዚህ ጥናት በአጠቃላይ አላማ ተኮር (purposive sampling) የናሙና አመራረጥ ዘዴን ተግባራዊ አድርጌዋለሁ፡፡*

*ከእነዚህ መረጃዎች የተገኙት ውጤቶች እንደሚያሳዩት የማህበረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ በሁለት የተለያዩ መልኮች ማለትም የህፃናት እና የአዋቂዎች በሚል በተለያየ አግባብ እንደሚፈፀም ማወቅ ተችሏል፡፡ በማህበረሰቡ ባህል መሰረት አንድ ጥርስ ያላበቀለ ህፃን ሲሞት አወቂዎች የሚቀበሩበት ቦታ አይቀበርም፡፡ በመሆኑ ከእናታቸው እቅፍ ሳይወርዱ/ ጥርስ ሳያበቅሉ በሞት የሚነጠቁ ህፃናት የሚቀበሩት በሌላው የዕድሜ ክልል ከሚገኝ የህብረተሰቡ አባል በተለየ ሁኔታ ቤት ዉስጥ ነው፡፡ ሟች በእድሜ የገፋ፣ አንዳች ማህበራዊ ስልጣን ያለው እና ኢኮኖሚያዊ አቅሙ የደረጀ ከሆነ የለቅሶ ስርዓቱ ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ይበልጥ የተለያዩ ክዋኔዎች የሚስተዋሉበት፣ ረዘም ያለ የዝግጅት ጊዜ የሚፈልግና የደመቀ ይሆናል፡፡ ይህም የሚደረገው በዋናነት በየአካባቢው ያሉ የማህበረሰቡ ተወላጆች በቀብሩ ዕለት እንዲገኙ ጊዜ ለመስጠት፣ በዝግጅት ጊዜም የሚፈልገውን ባህላዊ ምግብ እና መጠጥ ለለቀስ ተኞች ለማዘጋጀት እና በሟች ማሳ ውስጥ መፈፀም ያለባቸውን የእርሻ ስራዎች ለማከናወን መሆኑ ጥናቱ ተመልክቷል፡፡*

*በማህበረሰቡ የለቅሶ ክዋኔ ወቅት በዕድሜ፣ በፆታ እና በማህበራዊ ደረጃ ምክንያት የተወሰኑ ክዋኔዎች ልዩነት መኖሩን የጥናቱ ግኝት ያመለክታል፡፡  ጥናቱ በተካሄደበት ኦሮሞዎች ባህል ዋንኛው ለቅሶ የሚከወነው የቀብሩ ዕለት ሲሆን በዚህን ጊዜ ሁሉም እጅጉን መሪር በሆነ ለቅሶ ሟችን የመሰናበት ማህበራዊ ግዴታ አለባቸው፡፡  በጥናቱ የተደረሰበት ሌላው መሰረታዊ ነገር የኦሮሞ ማህበረሰብ በቀብሩ ዕለት የሚፈፀመውን መሪር ሀዘን የሚያሳርገው "ኦፈን" በተባለ ሙሾ እና ክዋኔ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ግጥም የሟችን እና የቤተሰቦቹን መልካም ገፅታዎች የሚያወሱ፣ ሞት ለሁሉም የቀረበ ግዴታ መሆኑን የተመለከቱ እና ሞት ዳግም የሟችን ቤተሰቦች እንዳይጎበኝ የሚመኙ ግጥሞች የሚደረደሩበት ነው፡፡*

*“ኢልሞ ኤኬሮ ” የሚበለዉ አንድ ሰዉ በትዳር ቆይታዉ ልጅ ከሌለዉ ከወንድሞቹ ወይም ከቅርብ ዘመድ ወንድ ልጅ ተፈልጎ አስከሬኑ አጠገብ በማስቀመጥ ልጁ የሟቹን ስም ይዞ እንዲቀር ይደረጋል፡፡ ይህም የሚደረገዉ ልጅ አለዉ የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ለለቅሶ ስርዓት የሚሰጠው ቦታ ከፍ ያለ መሆኑን እና ይህ አጋጣሚ ህብረተሰቡ ማህበራዊ ትስስሩን የሚያጠነክርበት፣ ኢኮኖሚያዊ አቅሙን የሚገልጥበት፣ አስተሳሰቡን የሚያጎላበት፣ ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶቹን እና ማህበራዊ ቁርኙቱን የሚያፀናበትና ከትውልድ ትውልድ የሚያሸጋግርበት መድረክ መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያመለክታል፡፡*

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

*አጠቃለሎ*----------------------------------------------------------------------------------------v
*ምስጋና*----------------------------------------------------------------------------------------ix
አጠቃሎ----------------------------------------------------------------------------------------vi
*ማዉጫ*----------------------------------------------------------------------------------------vii
*መግለጫ*----------------------------------------------------------------------------------------x
*ሙዳዬ ቃላት*----------------------------------------------------------------------------------------xi

**ምዕራፍ አንድ**

**መግቢያ**----------------------------------------------------------------------------------------1
1.1. የጥናቱ ዳራ----------------------------------------------------------------------------------------2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት----------------------------------------------------------------------3
1.3. የምርምር ጥያቄዎች----------------------------------------------------------------------------4
1.4. የጥናቱ አቢይና ንዑሳን ዓላዎች----------------------------------------------------------4
1.4.1. የጥናቱ አቢይ ዓላማ----------------------------------------------------------------------4
1.4.2. የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች----------------------------------------------------------------4
1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት----------------------------------------------------------------------------4
1.6. የጥናቱ ወሰን----------------------------------------------------------------------------------5

**ምዕራፍ ሁለት**

**ክለሳ ድርሳናት**----------------------------------------------------------------------------------11
2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት----------------------------------------------------------------------------11
2.1.1. የሞት ምንነት----------------------------------------------------------------------------------11
2.1.2. የለቅሶ ምንነት--------------------------------------------------------------------------------12
2.1.3. የለቅሶ ስርዓት--------------------------------------------------------------------------------12
2.1.4. የሙሾ ስርዓት ምንነት------------------------------------------------------------------------13
2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት----------------------------------------------------------------------------14
2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት----------------------------------------------------------------------17

**ምዕራፍ ሶስት**

**የጥናቱ ዘዴ**----------------------------------------------------------------------------------23
3.1.የመረጃ ምንጮች--------------------------------------------------------------------------------23
3.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች------------------------------------------------------------------24
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች----------------------------------------------------------24
3.3.1. ምልከታ----------------------------------------------------------------------------------------24

3.3.2. ቃለ-መጠይቅ------------------------------------------------------------------------------25
3.3.3. የቡድን ተኮር ውይይት-----------------------------------------------------------------26
3.4. የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ስልት------------------------------------------------26
3.4.1. የመረጃ አደረጃጀት-------------------------------------------------------------------26
3.4.2. የመረጃ አተናተን---------------------------------------------------------------------27
3.5. የመስክ ተሞክሮ-----------------------------------------------------------------------27
**ምዕራፍ አራት**
**የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ትንተና**-----------------------------------32
4.1. በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ምንነት--------------------------------------32
4.2. የህጻናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ---------------------------------------------------------34
4.2.1. የህጻናት ቅድመ ቀብር ክዋኔ---------------------------------------------------------35
4.2.2. የህጻናት የቀብር ጊዜ ክዋኔ----------------------------------------------------------36
4.2.3.ድህረ ቀብር ክዋኔ------------------------------------------------------------------38
4.3. ለአዋቂዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ---------------------------------------------38
4.3.1. ቅድመ ሞት ክዋኔ--------------------------------------------------------------------39
4.3.2. ጊዜ ሞት ክዋኔ----------------------------------------------------------------------41
4.3.3. ቅድመ ቀብር ክዋኔ-------------------------------------------------------------------43
4.3.4. የቀብር ጊዜ ክዋኔ--------------------------------------------------------------------52
4.3.5. ድህረ ቀብር ክዋኔ--------------------------------------------------------------------62
4.3.5.1. የማኅረጊያ /የምርቃት/ ስርዓት-------------------------------------------------------62
4.3.5.2. የሙት ዓመት አከባበር ስነ ስርዓት (ድባዩ) ------------------------------------------66
4.3.5.3. ሐዘንተኞችን ለማጽናናት የሚደረግ ክዋኔ------------------------------------------68
4.3.5.4 ለቅሶ የማህበረሰቡን ታሪክ፣ እምነትና አመለካከት ከመግለጽ አንጻር--------70
**ምዕራፍ አምስት**
**ማጠቃለያ**------------------------------------------------------------------------------71
5.1 ለቀጣይ አጥኚ ያለኝ አስተያየት------------------------------------------------------73
**ዋቢዎች** ---------------------------------------------------------------------------------74
**አባሪዎች**

## የፎቶ ግራፍ ማውጫ


ፎቶ፡ 1 አራቱ የወሊሶ ልጆች---------------------------------------------------------------6

ፎቶ፡ 2 የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የዘር ግንድ-------------------------------------------------7

ፎቶ፡ 3 ወንጪ ሀይቅ------------------------------------------------------------------------9

ፎቶ፡ 4 በኦሮሚያ ክልል የወሊሶ ከተማ ካርታ------------------------------------------------10

ፎቶ፡ 5 የወሊሶ ማህበረሰብ የሬሳ ሳጥን-----------------------------------------------------41

ፎቶ፡ 6 እስከሬን የሚቀመጥበት "ተምቦሺለ"-------------------------------------------------42

ፎቶ፡7 በስርአቱ ላይ የሚያዙ ቁሶች---------------------------------------------------------44

ፎቶ፡ 8 ፈረስ በቀሚሲ "ፈርደ ቀሚሲ"------------------------------------------------------46

ፎቶ፡ 9 የቀብር ጉድጓድ----------------------------------------------------------------50

ፎቶ፡ 10 ሴቶች ለቅሶ ቤት---------------------------------------------------------------53

ፎቶ፡ 11 በእግር በግል ሙሾ የሚያቀርብ ሰዉ----------------------------------------------55

ፎቶ፧12 የሟች ፎቶና ልብሶች ለማስለቀሻ-----------------------------------------------------55

ፎቶ፡13 በፈረስ ሙሾ ስያቀርቡ----------------------------------------------------------------56

ፎቶ፡14 በእግር/በቡድን ሙሾ (ኦፈን) የሚያቀርቡ ሰዎች-------------------------------------61

ፎቶ፡15 የመራቂዎችና ታዳሚዎች ፎቶ----------------------------------------------------64

ፎቶ፡ 16 "ቡና ቀላ"-----------------------------------------------------------------------67


### የሰንጠረዥ ማዉጫ


ሰንጠረዥ፡1 ቁሳዊ ባህሎቹ መቼና የት የት እንደሚያገለግሉ-------------------------------45

**መግለጫ**

በዚህ ርዕስ ስር መግለፅ የፈለኩት በጥናቱ ውስጥ የተገለገልኩባቸውን ምህፃረ ቃላት እና ዓመተ ምህረቶችን በተመለከተ ነው፡፡

ጥናቴን የተሳካ ለማድረግ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር ምሁራንን ልዩ ልዩ ፅሁፎች እና ጥናቶች ተገልግዬባቸዋለሁ፡፡ እነዚህን ጥናቶች በምቃኝበት ወቅት በእንግሊዘኛ የተፃፉ ስራዎችን ዓመተ ምህረት የጠቀስኩት በአውሮፓውያን አቆጣጠር ሲሆን ሌሎች ሀገርኛ ስራዎችን ግን ጥናቶቹ ወይም ፅሁፎቹ የተገለገሉበትን በኢትዮጵያዊያን አቆጣጠርን ነው፡፡

አላስፈላጊ ድግግሞሽን ማስወገድ ይቻለኝ ዘንድ የተወሰኑ ተደጋጋሚ ጉዳዮችን በምህፃረ ቃል ጠቅሻለሁ፡፡ እነርሱም፡-

በ.ደ.ም.ሸ. = በኦሮሚያ ክልል የደቡብ  ምዕረብ ሸዋ ዞን፤

ቃ.መ. = ቃለ-መጠይቅ፣

የተ.ቡ.ው. = የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣

ዓ.ም = ዓመተ ምህረት የሚሉ ናቸው፡፡

በመሆኑም አንባቢ እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ አስገብቶ ጥናቴን ያነብልኝ ዘንድ አስቀድሜ እጠይቃለሁ፡፡

## ሙዳዬ ቃላት

Haadha Siiqqee	በኦሞሮዎች ዘንድ ክብር ያለት ሴት (የአባ ገዳ ሚስት)

Siiqqee	በእጅ የሚያዝ በትር (ከወንዛ ዛፍ የሚዘጋጅ)

Abbaa Gadaa	ስልጣን ያለዉ ከአባቱ በአርባ አመት (40) ወይም ከአያቱ በሰማንያ አመት (80) ስልጣን የተቀበለ ማለት ነዉ

Buttaa qaluu	አባ ገዳ ለመሆን በሚካሄድ ሥርአት ላይ የሚታራድ ወይፈንና አጠቃለይ ሥርዓቱ ነዉ

Guula	ጎሳ መሪ

Ilmoo Ekeroo	ከሞቱ በኋለ ስም እንዲቀጥል (የሟችን ስም ይዞ የሚቀር)

Farda qamisii	ጀግና ሲሞት ፈረስ ልብስ በማልበስ የሚደረግ ተምሰሌት

Buna qalaa	ቡና ከጀንፈሉ ጋር ተቆልቶ ትንሽ ጨዉ እና ቅቤ በደንብ ተደርጎ የሚቀርብ ባህላዊ ምግብ

Dhibaayyuu	ኦሮሞዎች በሙት ሳምንት እና በሙት አመት የሚደራገዉ ስርዓት ላይ በሰኞ ቀን በጠላ መልክ "ፈርሶ ኦሮሞ" ተሰርቶ የሰዉ እግር በማይደርስበት ቦታ የሚደፋ

Farsoo Oromoo	ኦሮሞዎች እንደ ጠላ የሚጠቀሙበት

Guyyaa ekeraa	በሰኞ ቀን የሞተ ሰዉ የሚታሰብበት ቀን

Qeerrooo	ወጣት ወንድ

Qarree	ወጣት ሴት

Tambooshillaa	ከእንሰት የሚቆረጥ ዕርጥበት ያለዉ (የእንሰት ኩባ የያዘ)

Qalchaa	ከእንሰት አምቾ ቀጥሎ ያለ (የሚፋቅ)

Gaachana	ጋሻ

Eeboo	ጦር

Barcuma	ወንበር

Maqaa	ስም

Daasii	የሳር ቤት

Boochisaa	የለቅሶ ቀንና ስርዓት

Warqee	የእንሰት ዉጤት

Eebba	ምርቃት

Oofan	በቡድን ሆኖ የሚያስለቅሱ ግጥሞች ማቅራብ

Mucaa urgeessaa hincabsine ሴት ከሆነች ተወልዳ አራት (4) ቀን ያልሞለት ወንድ ከሆነ ደግሞ አምስት (5) ቀን ያልሞላው ማለት ነዉ፡፡

Kaabii	በቀብሩ ቦታ ላይና ዙርያዉን አፈር በመከመር ከጎርፍ መከላከል

Geeba	ከከብቶች ቀንድ የሚሰራ ለመጠጫ የምያገለግል

Qabee	ከስንደዶና ቅል የሚሰራ የወተት መጠጫ

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

በፎክሎር ጥናት ዘርፍ ውስጥ በርካታ ባህላዊ ስርዓቶችና እሴቶች ይጠናሉ፡፡ ከእነዚህ ባህላዊ ስርዓቶች እና እሴቶች መካከል አንዱ የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎችን በማጥናት የማህበረሰቡን አኗኗር፣ ባህል፣ ማንነት፣ አስተሳሰብ እና የህይወት ፍልስፍና የሚጠቁሙ ጉዳዮችን ማግኘት ይቻላል፡፡ በሀገራችን ሀዘን እንደ ማህበረሰቡ፣ እንደ አካባቢው እና እንደ እምነቱ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በወሊሶ ኦሮሞ ጎሣ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ትንተና ላይ ነው፡፡ ጥናቱ በክዋኔው ወቅት የሚታዩ የፎክሎር ዘሮች ለምሳሌ (ሀገረሰባዊ ልማዶች፣ ስነ ቃሎች፣ በስርዓቱ ክዋኔ ላይ የሚታዩ ቁሳዊ ባህሎች፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን) ይቃኛል፡፡ በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ቀብር የሚደረጉ የለቅሶ ስርዓቶች ክንውን የሚደረጉ ሲሆን በማህበረሰቡ የለቅሶው ስርዓት ጎልቶ የሚታየው በሞት ወቅት፣ በአስከሬን ግነዛና ሣጥን ዉስጥ ማስገቢያ ወቅት፣ በቀብር፣ በሳምንቱ እንዲሁም በማስተዛዘኛ ወቅት በሚደረገው ስነ ስርዓት ላይ ነው፡፡ እነዚህ ጎልተዉ የሚታዩ የለቅሶ ስርዓቶች በጥናቱ ዉስጥ በዝርዝር ተዳሰዋል፡፡

ይህ ጥናት አምስት ምዕራፎችን የሚይዝ ሲሆን፡- በመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አብይና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ፣ የመስክ ተሞክሮ፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸዉን የሚካተቱ ሲሆን፤ በምዕራፍ ሁለት ጽንሰ ሀሳባዊ እና ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች እንዲሁም የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ይገለጻሉ፡፡ ምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ እና የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ መንገድን ሲያካትት፤ ምዕራፍ አራት የመረጃዎች ትንታኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ በምዕራፍ አምስት ደግሞ የጥናቱ ማጠቃለያ የሚቀርብ ይሆናል፡፡ ባጠቃላይ ይህ ጥናት ከምዕራፍ አንድ እስከ አምስት ያሉትን የሚያካትት ሲሆን በተጨማሪም አባሪዎች እና ፎቶዎች እንዲሁም ዋቢ መፃሕፍትን አካትቷል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ሞት በህይወት ውስጥ ያለና አብሮን የሚኖር ነገር ቢሆንም በተከሰተ ጊዜ በሰው ልጅ ላይ የሚያሳድረው ከፍተኛ የሀዘን ስሜት አለ፡፡ Hertz (1960:27) ይህን ስሜት "ሞት የማይቀርና የተለመደ ክስተት እንዲሁም ደግሞ ስሜትን የሚነካ ነዉ" በማለት የገለጸ ሲሆን ይህ ሃዘን ደግሞ ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ለቅሶ ነው፡፡

በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚከወነው የለቅሶ ስርዓት እንደየ ባህሉና እንደየ አካባቢው ይለያያል፡፡ ነገር ግን የለቅሶ ስርዓቱ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ እና ከባህል ባህል የሚለያይ ቢሆንም በዓለም ላይ ተመሳሳይ የሆኑ ክንውኖች እንዳሉ በተለያዩ ጥናቶች ተገልጸ እናገኛለን፡፡ *World Book Encyclopedia(vol.7, 1978, 483).*

ይህ እንደሚያመለክተው ተመሳሳይ ከሆኑ ክዋኔዎች መካከል ሟች መሞቱን ማሳወቅ፣ መገነዝ፣ ሃይማኖታዊ ስርዓት መፈጸም፣ ሬሳውን መቀበር እና ለሟች ማልቀስ አብዛኛዉ የዓለም ህዝቦች የሚያከናወኗቸው ድርጊቶች እንደሆኑ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋንኛ ትኩረት የወሊሶ ኦሮሞ ጎሣ የለቅሶ ሥርዓተ ክዋኔን መግለጽ ነው፡፡ የወሊሶ ኦሮሞ በርካታ ባህላዊ እሴቶች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ መካከል አንዱ የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡ ይህ ስርዓት የተለያዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር አያይዞ የሚከውናቸው ክዋኔዎች ብዙ ናቸው፡፡ በለቅሶው ስርዓት ላይ ድምቀትን የሚሰጡና የሟችን ክብርና ማንነት ለመግለጽ የሚጠቀሙባቸው ስነ ቃሎች (ሙገሳዎች፣ ፉከራ፣ ቀረርቶ እንዲሁም የሙሾ ቃል ግጥሞች) አሏቸው፡፡ ስርዓቱ ሲከወን የሚታዩት ፉከራዎች እና እሱን ተከትለው የሚመጡ እንቅስቃሴዎች ለክዋኔው ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ የሟች ዘመዶችና ቤተሰቦች በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ለማልቀሻነትና ለፉከራዉ ይዘዋቸው የሚወጡት እንደ ጦርና ጋሻ፣ የፈረስ ላይ ፉከራና ወ.ዘ.ተ ቁሳዊ ባህል እና የለቅሶ ስርዓቱን ለማከናወን የሚደረጉ ዝግጅቶች የምንመለከታቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሌላው በለቅሶ ስርዓት ላይ የሚከወኑ ልማዳዊ ተግባራት በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ የእነዚህ ክዋኔዎች ተግባር ሟችን ለማስታወስ፣ ማህበረሰቡ ያበጀውን ስርዓት ለመፈጸም እንዲሁም ማህበራዊ ህይወታቸውን ለማጠናከር የሚረዱ ናቸው፡፡ ይህ ስርዓት ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍበት መንገድ ደግሞ ክዋኔ ነው፡፡ በክዋኔው ወቅት የሚታዩ ስነ ቃሎችን፣ ቁሳዊ ባህሎችን እና ልማዶችን ከክዋኔው ጋር በማያያዝ በጥናቱ ተገልጸዋል፡፡

ከዚህ በፊት በወሊሶ ኦሮሞና አካባቢዉ ማህበረሰብ ላይ በፎክሎር ዙሪያ የተደረጉ ሦስት የኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቶችን አግኝቻለሁ፡፡ እነሱም ኡርጌሳ ጥላሁን በ2009 ዓ.ም "በፈረስ

አጠቃቀም ወቅት የወሊሶ ኦሮሞ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና"፣ ለማ ከበደ በ2010 ዓ.ም "የወሊሶና አካባቢዉ ሽምግልና (ጃርሱማ) ስርዓት አፈጻፀም ትንተና" እና ደጀኔ ገመቹ በ2002 ዓ.ም "የምስራቅ መጫ ወሊሶ ኦሮሞ በጉማ ላይ ያተኮራ ግጭት አፈታት" በሚል ርዕስ የሰሯቸው ጥናቶች ናቸው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው የእኔ ጥናትም ቀዳሚዎቹ ጥናቶች ባተኮሩበት ማህበረሰብ ላይ አትኩሮ፤ ነገር ግን በተለየ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚሰራ ጥናት ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በዚህ ርዕስ ጥናት ለማድረግ ካነሳሱኝ ምክንያቶች የመጀመሪያው በማህበረሰቡ ባህላዊ ጉዳዮች የተለያዩ ጥናቶች ተደርገዋል፣ ነገር ግን የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ባለማግኘቴ ነው፡፡ ይህን ርዕስ ለትምህርት ክፍሉ ከማስገባቴ በፊት ተሰርቶበት ይሆን በሚል ስጋት ጅማ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በሚገኙ ቤተ-መፅሐፍት ውስጥ ባደረኩት ዳሰሳ ያልተሰራበት ርዕስ መሆኑን አጣርቻለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኢንተርኔት በመጠቀም ብፈልግም በሌሎች ፎክሎራዊ ርዕሶች እንጂ በዚህ ጉደይ ላይ በአካባቢዉ የተሰራ ጥናት ማግኘት ስላልቻልኩ ይህ ጥናት ይሄንን ክፍተት ለመሙላት አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብዬ በማመን በርዕሱ ልሰራ ወሰንኩ፡፡ ሁለተኛዉ ይህ ጥናት አካባቢውን፣ ማህበረሰቡን እንዲሁም ባህሉን ከማስተዋወቅ አንጻር የራሱ የሆነ ድርሻ አለው ብዬ በማሰቤ ነው፡፡

ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ የከተማው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባወጣቸው ጽሁፎች ላይ እንዲሁም ከአካባቢዉ ሽማግሌዎች እንደተረደሁት ማህበረሰቡ ቀድሞ የነበረው የለቅሶ ባህል እና የክዋኔ ስርዓት እየቀነሰና እየተቀየረ በመሆኑ የለቅሶ ስርዓቱን እና ከስርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አሁን ባሉበት ደረጃ ለመሰነድና ለትዉልድ ለማስተላለፍ ካለኝ ጉጉት አንፃር ነው፡፡ አራተኛዉ የተለያዩ ተመራማሪዎች እንዲሁም የተለያዩ ተቋማት ይህን ጉዳይ መነሻ አድርገው ቢያጠኑ ባህሉን ይበልጥ ያጠነክረዋል ከሚል መነሻ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በወሊሶና ሌሎች የአካባቢዉ ማህበረሰብ ፎክሎር ጥናት ላይ የሚስተዋለውን ክፍተት በመሙላት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክት ዘንድ የራሱን መሰረታዊ የምርምር ጥያቄዎች መሪ በማድረግ ተካሂዷል፡፡

### 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

በጥናቱ ምላሽ ያገኛሉ ተብለዉ የታሰቡ የምርምር ጥያቄዎች የወሊሶ ኦሮሞ ጎሣ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ምን ይመስላል፣ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚያዙ የቁሶች ትዕምርት ምንድን እንደሆነ እና በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚቀርቡት ስነቃሎች ይዘቶች ምን ላይ ያተኩራሉ የሚሉ ናቸዉ፡፡

### 1.4. የጥናቱ አብይና ንውሳን ዓላማዎች

በዚህ ርዕስ ስር ሁለት ዋና ዋና ነጥቦች የተዳሰሱ ሲሆን እነሱም የጥናቱ ዓብይ እና ንውሳን ዓላማዎች ናቸው፡፡

#### 1.4.1. የጥናቱ አብይ ዓላማ፡-

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የወሊሶ ኦሮሞን የለቅሶ ሥርዓተ ክዋኔ መተንተን ነው፡፡

ይህን አብይ ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ የሚከተሉት ንውሳን ዓላማዎችን ለማካተት ተሞክሯል፡፡

#### 1.4.2. የጥናቱ ንውሳን ዓላማዎች፡-

የጥናቱ ንውሳን ዓላማዎች ደግሞ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ በቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞት እና ድህረ ሞት የሚታዩትን ክዋኔዎች መግለጽ፤ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚያዙ ቁሶችን ትዕምርት መግለጽ እና በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚነገሩ ስነቃሎችን ይዘት መተንተን ናቸዉ፡፡

### 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱ ያስገኛል ተብሎ የታሰባዉ ጠቀሜታዎች ከዚህ ቀደም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በአካባቢዉ የተጠና ጥናት ካለመኖሩ የተነሳ ለሌሎች ተዛማጅ ጥናቶች እንደመነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል ተብሎ ስለታመነ፤ የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን ለሌሎች ያስተዋውቃል ከማለት አንፃር፤ የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚያሳየውን አንድነትና ማህበራዊ ህይወት ሊያሳይ ይችላል በማለት፤ የለቅሶ ስርዓቱን እና ከስርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አሁን ባሉበት ደረጃ ለመሰነድና ለትዉልድ ለማስተላለፍ ይረዳል ከሚል መነሻ እና የተለያዩ ተመራማሪዎች እንዲሁም የተለያዩ ተቋማት ይህን ጉዳይ መነሻ አድርገው ቢያጠኑ ባህሉን ይበልጥ ለመረዳት የሚያስችሉ ግኝቶች ላይ እንደሚደርሱ ለመጠቆም ጭምርም ነዉ፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረት የወሊሶ ኦሮሞ ጎሣ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን በትንተና ማሳየት ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው፡፡ ምክንያቱም ካለኝ ጊዜና አቅም አንፃር የተጠቀሰውን ርዕሰ ጉዳይ ሥርዓት ክወናና የቃል ግጥሞቹን ይዘት ተንትኖ ማሳየት ላይ ብቻ ትኩረት አድርጋለሁ፡፡

ከቦታ አንፃር ደግሞ ይህ ጥናት በአጥኚዋ የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት ዉስንነት ምክንያት ሰፊዉን የኦሮሚያ ክልል ማዳረስ ስለማይቻል በወሊሶ ከተማና አካባቢዉ ብቻ ተወስኗል፡፡

## 1.7. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ

የወሊሶ ከተማ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሰት፣ በደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን ከአዲስ አበባ በ114 ኪሜ. ርቀት በጅማ መንገድ ላይ ይገኛል፡፡ ወሊሶ በስተ ምዕራብ በወንጪ ወረዳ፤ በስተ ደቡብ በደቡብ ክልል፤ በምስራቅ በሰዴን ሶዶ ወረዳ እና በስተ ሰሜን ዳዎ ወረዳ ይዋሰናል፡፡ ከተማዉ በ4 ቀበሌ የተደራጀ ሲሆን ወደ 105,052 (CSA 2007) አካባቢ የሚገመት የሕዝብ ብዛት ይኖርበታል፡፡ የወሊሶ ከተማ አመቺ ወይና ደጋማ የአየር ንብረት እና ሜዳማ የመሬት አቀማመጥ አለው፡፡ ከተማዉን ለእንቬስትመንትና ለቱሪዝም አመቺ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች፤ የወሊሶ ፍልዉሃና የወንጪ ተፈጥሮኣዊ ሐይቅ ይጠቀሳሉ፡፡ (የወሊሶ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ቢሮ ሚያዝያ 2009)::

ወሊሶ እንደ ሌሎቹ የሀገሪቱ ክልሎችና አካባቢዎች ሁሉ የራሱ በሆኑ፣ በባህላዊ፣ በመንፈሳዊ፣ በታሪካዊና በተፈጥሮአዊ ቅርሶች የበለጸገ፣ በተፈጥሮአዊ ገጽታው የታደለ፣ የጋብቻ ሥነስርዓቶቹ፤ የማኅበረሰቡ የአኗኗርና የስራ ባህል ሊጎበኝ፣ ሊታወቅና ሊነገርለት የሚገባው አካባቢነው፡፡ በስራ፣ በደስታ፣ በጫወታ ጊዜ የሚዘወተሩት ባህላዊ፣ በጫዋታዎቹ ሰርክና በበዓላት የሚዋቡባቸው ባህላዊ አለባበሶች፣ የሀዘን መግለጫ ስነስርዓቶቹ፣ ቂጣውን፣ ተቃውሞውንና ቂጭቱን የሚገልጽበት ሥነቃላዊና ሙዚቃዊ እሴት፣ ባህላዊ ምግቦቹና መጠጦቹ፣ የሀገሩን፣ የልጆቹን፣ የከብቶቹን፣ የቤተሰቡን ፍቅር የሚገልጽበት እንጉርጉሮና ቀራርቶ፣ የእርስ በርስ ግጭትና ቅራኔውን የሚፈታበት ባህላዊ የእርቅና የሽምግልና ስርዓት በአጠቃላይ ከትውልድ ትውልድ ሲወርድ ሲያድግና ሲጎለብት የኖረ ባህላዊ ማንነቱ እጅግ የሚያስደስትና ቀልብን የሚገዛ ክዋኔ ነው፡፡ ይህንን የማህበራዊ ክዋኔዎችን ለመፈጸም የአካባቢዉ ማህበረሰብ ከአራቱ የወሊሶ

ልጆች የተዉጣጡ ቡድኖችን ይጠቀማል፡፡ (የወሊሶ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ቢሮ ሚያዝያ 2009)::




ፎቶ 1፡ አራቱ የወሊሶ ልጆች (ቃለ መጠይቅ 10/08/2013 ወሊሶ)

## የወሊሶ ከተማ ገጽታና ታሪካዊ አመሰራረት

ከወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ለመረዳት እንደተቻለዉ አረንጓዴያማዋና ሜዳማዋ ምድር ወሊሶ በ1919ዓ.ም ዉስጥ የተቆረቆረች ስትሆን ከ1923 ዓ.ም ጀምሮ በማዘጋጃ ቤት መተዳደር መጀመሯ ይገለጻል፡፡ ለመቆርቆርዋም ምክንያት የተፈጥሮ ገፀ-በረከት የሆነዉ ፍልዉሃ መኖሩ፣ይህንን ተከትሎ ከተሰሩት ትናንሽ የሣር ጎጆዎች ስብስብ በሂደት የዛሬዉን ገፅታ መያዝ ችላለች፡፡ የዕድሜ ባለጠጋ ከሆኑት አባቶች መረዳት እነደተቻለዉ ወሊሶ ስያሜዋን ያገኘችዉ በአከባቢዉ ይኖር ከነበራዉ **ወሊሶ ሊበን** ከሚባል ታዋቂ ሰዉ ነዉ፡፡ ወሊሶ ከሊበን መጫ ልጆች ኣንዱ ሲሆን ሊበን ሶስት ልጆች ነበሩት እነርሱም አመያ፤ ወሊሶ እና ኩታዬ የሚባሉ ናቸዉ፡፡ ወሊሶ ለአባቱ ሁለተኛ ልጁ ሲሆን አመያ እና ኩታዬ የሚባሉ ወንድማማቾች አሉት፡፡ እነዚህ የሊበን ልጆች አመያ ሊበን በአመያ ከተማ እና አካባቢ፤ ኩታዬ ሊበን በአምቦ ከተማ እና አከባቢዉ የሰፈሩ ሲሆን፣ ወሊሶ ከአባቱ ሊበን ጋር ፍልዉሃ አከባቢ ልዩ ስሙ አዬቱ የሚባል ቦታ ይኖር እንደነበርና በዚያዉ ከተማዋም ወሊሶ ተብላ እንደተጠራች ይናገራሉ፡፡ የጥናቱ መሰረት የሆኑት የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የዘር ግንድን ከኩሽ እስከ ወሊሶ የአካባቢዉ

የእድሜ ባለጸጎች በገለጹልኝ መሰረት እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡(ቃ.መ.11/08/013 ዓ.ም፣ ማሩ ፋቂ ቀበሌ)

ፎቶ2፡ የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የዘር ግንድ




ምንጭ፡ ኡርጌሳ ጥላሁን፡፡ (2009)፡፡

የዛሬ አረንጓዴ‚ያማዋና ሜዳማዋ ምድር ወሊሶን ተከትሎ በአካባቢዉ የሰፈሩ ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ ፍልዉሃ ለመጠመቅ ከተለያየ አከባቢ በሚመጡ ሰዎች የተሰሩ ባህላዊ ጎጆ ቤቶች ቀስበቀስ ወደመንደርነት መቀየር እንደ ጀመረች ታሪክ

አዋቂዎቹ ይናገራሉ:: ከተማዋ ለኑሮ ተስማሚ ከመሆኗ የተነሰ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚኖሩባት ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ኦሮሞ 90% ይሆናል (የወሊሶ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ቢሮ ሚያዝያ 2009):: አማራ፣ ጉራጌ፣ ትግሬ፣ ስልጤ፣ ወለኔ፣ ቀቤና እና ሌሎችም እየተበራከቱ በመምጣታቸዉ ተፈጥሮ በለገሳት ለጥ ያለ ሜዳ ላይ ወደ አራቱም አቅጣጫ የሰፋች መሆኗን ታሪክ ያስረዳል:: አጼ ኃ/ስላሴ በ1952 ዓ.ም ከተማዋን መጎብኘታቸዉን ተከትሎ "ግዮን" ተብላ እንድትጠራ የሰየሙዋት ሲሆን ከደርግ ዉድቀት ማግስት ወደ ቀድሞ ስያሜዋ "ወሊሶ" ዳግም እንደተመለሰች የአካባቢዉ ሽማግሌዎች ይገልፃሉ፡፡

የወሊሶ ከተማ የቆዳዋ ስፋት በሄክታር 2515.25 ሆኖ95 በመቶ ሜዳማ ናት በአስትሮኖሚ እይታ በሰሜን $8^{0}$31"47"፣በምስራቅ $37^{0}$58'59" እንዲሁም በሰሜን $8^{0}$31'59" ከኪሮስ (ላቲትዩድ) እና በምስራቅ $37^{0}$58'59" ከንትሮስ (ሎንጊትዩድ) ላይ ትገኛለች፡፡ ከተማዋ ከባህር ጠለል በላይ በ1900 ሜትር ከፍታ ላይ ትገኛለች፡፡ ወሊሶ ከተማ ክረምት ከበጋ የሚፈሱ ሦስት ወንዞች (ሬቡ፣ ኤጄርሳ እና አዬቱ) መካከል ስትገኝ ወንዞቿ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ የአየር ንብረቷም ወይናደጋ፣ አመታዊ የሙቀት መጠኗም ዝቅተኛ 18 ዲ.ሴ.ግ ከፍተኛዉ 27 ዲ.ሴ.ግ ነዉ፤ የዝናብ መጠን በአማካይ 1200 ሚ/ሊትር የሚደርስ ሲሆን በአመት ከ6 ወራት ላላነሰ ጊዜ ዝናብ የምታገኝ አካባቢ በመሆኗ ዙሪያዋ በዝናብና በመስኖ የሚለማና አመቱን በሙሉ አትክልት፣ ፍራፊሬና የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ለማእከላዊ ገበያ እና ለአከባቢዉ ገበያ ማቅረብ አስችሏታል:: ወሊሶ ከንግድ እንቅስቃሴዎች ባሻገር ለኮንፈረንስና ቱሪዝም ምቹና ተመራጭ እየሆነች መጥታለች፡፡ በጭስ አልባዉ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የወሊሶ ከተማ ከፍተኛ እምቅ አቅም ባለቤት እንድትሆን ካስቻሏት የቱሪስት መዳረሻዎች የተፈጥሮ ፍል ዉሃ ግንባር ቀደም ነዉ፡፡ የተፈጥሮ ፍልዉሃ ዋና አገልግሎት የመኝታ አገልግሎት የሚሰጡ 34 የሀገራችንን ብሔር ብሔረሰቦች እሴት ተላብሶ በተገነቡ ባህላዊ ጎጆዎች፣ የፈረስ ግልቢያ፣ የጎልፍ መጫወቻ ሜዳ፣ የህጻናት መጫወቻ፣ ምቹ ኮንፈረንስ ማእከል እንዲሁም ዘመናዊ የካፌና ሬስቶራንት አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ በሎጁ ዉስጥ የተፈጥሮ ዛፎች፣ የተለያዩ አእዋፋትና፣ የተለያዩ የባህላዊ መገልገያ እቃዎች፣ ለማዳ የዱር አራዊቶችን ትእይንት መመልከቱ የተለየ እርካታን ይሰጣል፡፡ ይህንን ሪዞርት ከሚጎበኙት 81% የዉጪ ዜጎች ሲሆኑ ቀሪዉ 19% የሀገር ዉስጥ ጎብኚዎች ናቸዉ፡፡ ከወሊሶ 36 ኪ.ሜ እንዲሁም ከሀገራችን መዲና አ.አ 150 ኪ.ሜ የሚገኘዉ **ወንጪ ሀይቅ** ከሀገራችን ሐይቆች ለየት ከሚያደርጉት ነገሮች ዉስጥ የዳገት ላይ ሐይቅ፣

ክረምት ከበጋ የዉሃዉ ቅዝቃዜ፣ ጥራቱ ጀልባ ላይ ሆኖ ወደታች መሬትን ማየት የሚቻል መሆኑ እና በጋራ የተከለለ መሆኑ ዉብና ማራኪ ያደርገዋል፡፡ ከሀይቁ መሃል አንድ ደሴትና ጥንታዊ የጭርቀስ ገዳም ይገኝበታል፡፡ ሀይቁ ማራኪ ከመሆኑ የተነሳ የዉጭ ዜጎችና የሃገር ዉስጥ ጎብኝዎች ቁጥራቸዉ ከቀን ወደ ቀን እየተበራከተ መጥቷል፡፡ (የወሊሶ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ቢሮ ሚያዝያ 2009)::




ፎቶ3፡ ወንጪ ሀይቅ (በአጥኚዋ)

ስለወንጪ ሀይቅ አፈጣጠር የሚገልጽ አፈ-ታሪክ ከአካባቢዉ የዕድሜ ባለፀጋ አዛዉንቶች ለመረዳት እንደቻልኩት በአሁን ጊዜ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን፣ ወንጪ ወረዳ የምትገኘዉ ወንጪ በምትባለዉ ደጋማና ለም ስፍራ ይኖሩ የነበሩ ጎሳዎች እጅግ ጥጋበኞች እንደነበሩ ይገልጻሉ፡፡ ከጥጋባቸዉ የተነሳ ብዙ መጥፎ ነገሮችን ይሰሩ ነበር፡፡ የወንጪ ሽማግሌዎች በየጊዜዉ ቢመክሯቸዉም ጥጋበኞቹ ከሚፈጸሟቸዉ አጉል ተግባሮች ሊመለሱ አልቻሉም፡፡ አንድ ጊዜ ከነዚህ ጥጋበኞች መካከል አንዱ በጣም ቆንጆ የሆነች እህቱን ሌላ ሰዉ እንዳያገባት እሱ ሊያገባት ወሰነ፡፡ ዉሳኔዉንም ለጓደኞቹ ነገራቸዉ፡፡ እነሱም እህቱን እንዲያገባት አበረታቱትና የወንድምና የእህት ጋብቻ ተፈጸመ፡፡ በዚህን ጊዜ የአካባቢዉ ሽማግሌዎች ይህን ጉድ አናይም ብለዉ

ከመንደራቸዉ ወጥተዉ ለብቻቸዉ ተቀመጡ፡፡ ጥጋበኞቹም ቀንና ሌሊት እየጨፈሩ መደሰታቸዉን ቀጠሉ፡፡ ቆይቶም ፈጣሪያቸዉ የቅጣት ማዕበል አዘዛባቸዉና ከወንጪ አካባቢ ዉሃ እየፈለቀ አጥለቀለቃቸዉ፡፡ ዉሃዉም ከቁርጭምጭሚታቸዉ አልፎ ጉልበታቸዉ ደረሰ፡፡ እነርሱም ጭፈራቸዉን ቀጠሉ ዉሃዉም ጉልበታቸዉን፣ ከዚያም አንገታቸዉ ላይ ደረሰ፣ በመጨረሻም ራሳቸዉን ሸፈናቸዉና ሰጥመው ቀሩ፡፡ የጥጋበኞቹን ድርጊት በማዉገዝ አናይም ብለዉ ከመንደሩ ርቀዉ የተቀመጡት ሽማግሌዎች የነበሩበት ቦታ ብቻ ደሴት ሆና ስትቀር የወንጪ ምድር በዉሃ ተሸፈነች፡፡ ይህ ደሴትም በአሁኑ ጊዜ የጭርቆስ ገዳም ያለበት ቦታ ነዉ፡፡ የወንጪ ሀይቅ የተፈጠረዉ በእንዲህ ያለ ሁኔታ መሆኑን የአካባቢዉ ሽማግሌዎች ይገልጻሉ፡፡

**ፎቶ4፡ በኦሮሚያ ክልል የወሊሶ ከተማ ካርታ**




ምንጭ: Oromia Urban Planning Institute 2009

## 1.8. የመስክ ተሞክሮ

ይህ ጥናት አተኩሮ ወደሚሰራባቸው የጥናት ቦታዎች የተደረገው ጉዞ በሚከተለው መልኩ የተከናወነ ነው፡፡ ከፍ ሲል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹን ባብራራሁበት ክፍል ላይ እንደገለፅኩት ለዚህ ጥናት የሚበጀኝን መረጃ ለመሰብሰብ መስክ ከመውጣቴ አስቀድሜ በቤተ መፃሕፍት በመገኘት የማጠናበትን ርዕሰ ጉዳይ እና ማህበረሰብ የተመለከቱ ልዩ ልዩ መረጃዎችን አሰባስቤያለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ከአማካሪዬ ጋር በመናበብ በተዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከመስክ መረጃ የምሰበስብበት ጊዜ እየተቃረበ በመሆኑ ለቃለ-መጠይቅ እና ለተተኳሪ ቡድን ውይይት መነሻ የሚሆኑኝን

ጥያቄዎች አስቀድሜ በማዘጋጀት ለዚሁ ተግባር አጋዥ የሚሆኑኝን የቪዲዮ እና ፎቶ ካሜራ እና ልዩ ልዩ የፅህፈት መሳሪያዎችን በግዢ እንዲሁም መቅረፀ ድምፅ በሞባይል በማዘጋጀት መጋቢት 23/2013 ዓ.ም የመስክ ጉዞዬን ጀመርኩ፡፡

መጋቢት 23/013 ዓ.ም ዕለተ ሀሙስ ጠዋት ከጅማ-አዲስ አበባ በሚጭነው ሀገር አቋራጭ አውቶብስ ተሳፈሬ ጉዞዬን ጀመርኩኝ፡፡ 5፡15 ላይ ወልቂጤ ለቁርስ ከነበረን የ30 ደቂቃ ረፍት ውጪ ምንም ጊዜ ሳናባክን 6፡30 ሲል ወሊሶ ገባን፡፡

በነጋታዉ ጠዋት ልክ ከማለዳው 12፡00 ሲል ከወሊሶ ወደ ወንጪ ሀይቅ በሚወስደዉ አውቶብስ ጉዞ ወደ ወንጪ ሆነ፡፡ ጪቱ እና ደርያን አልፈን 1፡40 ላይ የወንጪ ሀይቅ የሚገኝበት ሀሮ ወንጪ ከተማ ደረስን፡፡ ሀሮ ወንጪ ከተማ ዳገት ላይ የተመሰረተች ስትሆን ከዳጋቱ ላይ በመሆን ሀይቁን በጥሩ ሁኔታ መመልከት ይቻላል፡፡ በ24/013 ባደረኩት ጉዞ ስለ ወንጪ ሀይቅ አፈጠጣርና ስለ ሊበን ልጆች አቶ ሞሮደ ቶሌራ እና አቶ ሚደክሳ ጫልችሳ በአከባቢ ዳራ ላይ የገለፅኩትን ዳግም አብራርተዉ ነገሩኝ፡፡ ከከተማ ወደ ሀይቁ በሚወስደዉ መንገድ ፉቴቲ በሚባል ስንሄድ መንገዱ ስለሚያስፈራ በብላንብሌ ወደ ሀይቁ ሄድን፡፡ እኛ በእግር ነበር የሄድነዉ ነገር ግን በማህበር ተደራጅተዉ በፈረስ የሚወስዱም አሉ፡፡ ልክ ሀይቁጋ ስንደርስ እናቶች በጀልባ እህላቸዉን ይዘዉ ወደ ወፍጮ ሲሄዱ አገኘኋቸዉ እኔም በጣም ተገረምኩኝና አንድ እናት አገኘሁኝና ወ/ሮ ሙሉ ዳበሳ ይባላሉ ጥያቄዬን ቀጠልኩ፡- ገብያ፣ ወፍጮ፣ የማገዶ እንጨት እና ዉሀ እንዴት እንደሚያገኙ ጠየኳቸዉ እሳቸዉም እንድህ ብለዉ በመገረም ለጠየኩት ጥያቄ መልስ ሰጡኝ፡፡ እኛ ተወልደን ያደግነዉ እዚሁ ሀይቁ ዙርያ ስለሆና በጀልበ መሄድ በእግር መሄድ እንደለመድን ሁሳ ለምደን ሁሉን ነገር ጀልባዉን የከተማ ሰዉ ጋሪን እንደሚጠቀም ከዝያም በላይ እንጠቀማለን፡፡ ልጆቻችን በእሱ ነዉ ትምህርት ቤት የሚሄዱት ብለዉ ካስረዱኝ በኋላ እኔም አመስግኜ አቶ ሞሮዳን እና አቶ ሚደክሳን ይቅርታ ጠይቄ ስለ ጨርቆስ ቤተክርስትያን ጥያቄ አቀረብኩላቸዉ፡፡ የቤተክርስትያኑን አፈጠጣር ሲነግሩኝ እኔም እያየሁ በሀይቅ ተከበ ደሴት ላይ ነዉ ያለችዉ ደሴቷ እንዴት እንደተፈጠረች ስጠይቃቸው ሽማግሌዎቹ የነበሩበት ቦታ እንደሆነ ነገሩኝ፡፡ በቤተክርስትያን ዙሪያ የሚኖሩ ሰዎች በወር ዉስጥ አምስት ቀን ብቻ ነዉ ማሳቸዉን የሚሰሩት በዝያዉ አምስት ቀን በሚሰራዉ ስራ ሠለሳ ቀን የሚሰራዉን በንብረት በልጠን እንኖራል ብዙውን ጊዜ በምግብነት የምንጠቀመዉ “ቆጮ” እንሰት እና ገብስ ሲሆን ልጆቻችን ለበሽታም አይዳረጉም ሌላ ቦታ በሽታ ይበዛል እኛጋ የለም ብለዉ ከነገሩኝ በኋለ የወሊሶ አባት ሊበን እዚያ ይኖር ነበር የሚል ታርክ ስለ ሰማሁ ጠየቅኳቸው፤ አዎ ሦስቱን ልጆች አመያን፣ ወሊሶን እና ኩታዬን ይዞ በዚሁ ቀበሌ

ዉስጥ “ጎሮ” የሚባል ቦታ ነዉ የነበራዉ ብለዉ ነገሩኝ፡፡ በኋለ ጥናቴም ትኩረቱን ያደረገዉ ከሊበን ልጆች አንዱ በሆነዉ ወሊሶ ላይ ስለሆነ በጣም ደስ አለኝና ወሊሶ እንዴት ወሊሶ የሚባል ቦታ እንዳገኘ ጠየቅሁ፡፡ ከአባቱ ከሊበን ጋር ፍል ዉሃ ጠበል ለመታጠብ ሄዶ እዚያ ቀረ ካሉኝ በኋለ በሀይቁ ዙሪያ ያሉ ጎጦችን ሲነግሩኝ፣ ከምሻሼ፣ መርፎ፣ ዴራ፣ እላላ ጎራ፣ ከላ፣ ሀሮ ጋራ እና አለንጋ ብለዉ ከነገሩኝ በኋለ ወንጪ ወረዳ ዉስጥ የሚኖሩ ጎሳዎች አስራ ሁለቱ የጨቦ ጎሳ እና አራቱ የወሊሶ ልጆች ናቸዉ ብለዉ ነገሩኝ፡፡ ስለ ወሊሶ የወሊሶ ሽማግሌዎች አራት ናቸዉ፡፡ ከአቡ አንድ ከወሌ አንድ ከሌማን አንድ እና ከሙኞ አንድ ስላሉ ስለ ወሊሶ ባህልና ወግ እነርሱን ከጠየቅሽ ታገኛለሽ ብለዉ የቤተክርስትያን ሰዓት ስለ ደረሰባቸዉ ተሰናበትን፡፡ ከሀይቁ ወደ ላይ በሚወስደዉ መንገድ ስሄድ እዚያዉ ሀይቁ አጠገብ ትምህርት ቤት አገኘሁ፡፡ ትምህርት ቤቱ ዉስጥ ገብቼ መምህር ገላና አንጋሱ እዚያዉ ትምህርት ቤት ዉስጥ አገኘሁት፡፡ የጅማ ዩንቨርስቲ ተማሪ እና አሁን መረጃ ለመሰበሰብ መሄዴን የሚያሳይ የድጋፍ ደብዳቤዬን ካሰየሁ በኋለ የትምህርት ቤቱን ሁኔታ ጠየቅኩት፡፡ መምህሩም ትምህርት ቤቱ የወንጪ ገዳም ትምህርት ቤት እንደሚባል ከ1-8 እንደሚያስተምር ትምህርት ቤቱ በግልም በመንግስትም ድጋፍ እንደሚደረግለት ለትምህርት ቤቱ ሀይቁ ሀብቱ እንደሆነ እንዲሁም ተማሪዎቻቸዉ በጊዜ በጀልባ ትምህርት ቤት ዉስጥ እንደሚገኙ ያስረዳሉ፡፡ መጋቢት 25/13 ዓ.ም 12፡00 ሰዓት ላይ ከወንጪ ተነስቼ ጉዞዬን መረጃ ወደምሰበስብበት ወሊሶ ከተማ አደረኩ፡፡ ወሊሶ የደረስኩት ረፋድ 4፡00 ሰዓት አካባቢ ሲሆን ከትምህርት ክፍሌ የተፃፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ ይዤ ወደ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን አስተዳደር ፅ/ቤት ሄድኩ፡፡ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ መገርሳ ድርብሳ በትህትና ከተቀበሉኝ በኋላ የመጣሁበትን ጉዳይ እንዳስረዳ እድል ሲሰጡኝ፡፡ የያዝኩትን ደብዳቤ በመስጠት የጥናቴን ርዕስ እና ዓላማ በማብራራት ለዓላማዬ ስኬት ምን አይነት መረጃ፣ ከነማን እና እንዴት እንደማገኝ በአግባቡ አስረዳኋቸው፡፡ አስተዳዳሪው በፅሞና ካደመጡኝ በኋላ በባህል ላይ ለመስራት በመወሰኔ የተሰማቸውን ደስታ ገልፀውልኝ ከምፈልጋቸው መረጃዎች ላይፈቀድልኝ የሚችል እንዳለ ያላቸውን ስጋት በመጠቆም ደብዳቤዬን ለዞኑ ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት መርተውልኛል፡፡ የዞኑ ባህል እና ቱሪዝም ፅ/ቤት ኃላፊ ደብዳቤዬን ተቀብለው ወደሚመለከተው ባለሙያ መሩልኝ፡፡ ወ/ሮ ታደለች አራርሳ የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ ስትሆን ደብዳቤዬን ካሳየኋት በኋላ የጥናቴን ዓላማ እና አንዳንድ መሰረታዊ ነጥቦችን በዝርዝር አስረድቼአት በጉዳዩ ዙሪያ መነጋገር ጀመርን፡፡ ይህን አስመልክቶ የተሻለ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉትን አካላት ዝርዝር ሰጠችኝ፡፡ በዞኑ ከርእሰ ጉዳዬ ጋር እና

ከአንዳንድ ባህላዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ መረጃዎች ካሉ እንዲያውሰኝ ስጠይቀት ምንም አይነት የተደራጀ መረጃ አለመኖሩን በመጥቀስ በፅ/ቤታቸው ቀደም ሲል የተዘጋጁ ሁለት መፅሔቶችን ሰጥታኝ  ለወሊሶ ከተማ እና ወረዳ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ የትብብር ደብዳቤ ጽፋልኝ ለሌላ ቀን ቀጠሮ በመያዝ ተለያየን፡፡ ለወረዳ እና ለከተማ የተፃፈልኝን ደብዳቤ በመያዝ ቀደም ብዬ ስለ ርእሰ ጉዳዩ አሳውቄያቸው ስለነበር የተሻለ መረጃ አላቸው የሚሏቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ከወንጪ ሽማግሌዎች በመያዝ ከጥቂት እረፍት በኋላ ከተጠቀሱት መረጃ አቀባዮች አንዱ ወደ ሆኑት አቶ ሽፈራ አሰፈ ቢሮ ሄድኩ፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ አቶ ሽፈራን ቢሮ ስላገኘኋቸው የጠበቀ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ እንድቀመጥ ጋበዙኝ፡፡ አቶ ሽፈራ የመጣሁበትን ጉዳይ ጠይቀውኝ በአጭሩ ካብራራሁላቸው በኋላ የላቸዉን እዉቀት ያለመቆጠብ አንድ በአንድ ካስረዱኝ በኋለ እነማን በዙሪያው የተሻለ ዕውቀት እንዳላቸው ዝርዝር መረጃ በመቀበል አመስግኜ ተለያየን፡፡ ከ26/07/2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ቀን 18/08/2013 ዓ.ም ድረስ በርዕሰ ጉዳዬ ዙሪያ ሰፊ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ አካላት ተብለው በተለያዩ ሰዎች ከተጠቀሱልኝ ጋር ተገናኘሁ፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል አቶ ነገሱ አምዲሳ በወሊሶ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያና በወሊሶ ዙሪያ አንድ መፅሓፍ የፃፉ ይገኙበታል፡፡ በቀን 18/08/2013 ዓ.ም በሶንቆሌ ቀበሌ የሚገኙ አንዲት አዛውንት በህመም ምክንያት ህይወታቸው በማለፉ እዚያው ተገኝቼ የመጀመሪያ ምልከታዬን ያከናወንኩበት ጊዜ ነበር፡፡ ሟች ባለቤታቸው ቀደም ብለው ያረፉ በመሆኑ የሚኖሩት ከልጅ ልጆቻቸው ጋር ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ስርዓት ላይ ተገኝቼ መመልከት ችዬለሁ፡፡ ስለሆነም የነበረኝ ብቸኛ አማራጭ የምመለከታቸውን ልዩ ልዩ ትዕይንቶች በሚገባ በማጤን በየዕለቱ ማታ ማታ ሰፋ ያለ ማስታወሻ በመያዝ ያጋጠመኝን ችግር በተቻለ መጠን ለመቅረፍ ችያለሁ፡፡

በቀን 19 እና 20 አስቀድሜ ያዘጋጀሁትን መነሻ ጥያቄ እና በምልከታው ወቅት የጠፈጠሩብኝን ጥያቄዎች በማከል ከሁለት ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ ጋር ሰፋ ያለ ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ መጋቢት 25/013 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 02/013 ዓ.ም ድረስ ሌላኛውን ምልከታዬን ያካሄድኩበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ምልከታ በቀደመው ምልከታዬ ያላስተዋልኩት ተጨማሪ ነገር እና በዚያን ወቅት የሳትኳቸውን መሰረታዊ ነጥቦች ያገኘሁበት ነበር፡፡ ፍቃድ በመጠየቅ አንድ አንድ ፎቶ እና ቪድዮ የወሰድኩባት ቀን ነዉ፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ ሟች ወንድ በመሆኑም ከፆታ ስብጥር አንፃር መመልከት የሚጠበቅብኝን መሰረታዊ ነጥቦች አግኝቼበታለሁ፡፡ በሁለተኛው ምልከታዬ ወቅት ባገኛኋቸው የተወሰኑ የእረፍት ጊዜዎች እና በቀጠሮ ከያዝኳቸው ሦስት ያህል ቁልፍ

መረጃ አቀባዮቹ ጋር ቃለ-መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ ሁለተኛ ምልከታዬን እንዳበቃሁ በቀን 10 እና 11/08/013 ዓ.ም እንዲሁ ከሌሎች ሁለት ቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ ጋር ሰፋ ያለ ጊዜን አሳልፌያለሁ፡፡ ሚያዝያ 12/013 ዓ.ም ከምልከታ እና ከቃለ መጠይቅ ያገኘኋቸውን መሰረታዊ ነጥቦች ያረጋገጥኩበት እና ከሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቼ ያመለጡ ቁም ነገሮችን ያገኘሁበትን የተተኳሪ ቡድን ውይይት ያደረኩበት ቀን ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በነበሩኝ የተወሰኑ ቀናት በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት በድምፅ የቀረፅኳቸውን መረጃዎቼን ወደ ፅሁፍ ስገለብጥ እና ሳደራጅ ነው የቆየሁት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መረጃዎቼን በትኩረት በምመረምርበት ወቅት የተፈጠሩብኝን ጥያቄዎች እና የተወሰነ ክፍተት ይስተዋልባቸዋል ያልኳቸውን የተወሰኑ መረጃዎች ከአንዳንድ መረጃ አቀባዮቹ ጋር ዳግም በመገናኘት ሳሟላ ቆይቼለሁ፡፡

## ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸዉ

በዚህ ጥናት ክንውን ወቅት ያጋጠመኝ ከፍ ያለ ችግር በማህበረሰቡ ባህል መሰረት በለቅሶ ስርዓት ላይ ምንም አይነት የድምፅም ሆነ የምስል ቀረፃ እንዲደረግ የሚፈቀድ አለመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም የተነሰ ትብብር እንዲደረግልኝ ከትምህርት ክፍሌ ለደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን አስተዳደር ፅ/ቤት የተፃፈልኝን ደብዳቤ ይዤ የዞኑ አስተዳዳሪ የሆኑት አቶ መገርሳ ፊት በመቅረብ የመጣሁበትን ዓላማ እና መረጃዎቼን በምን መልኩ እንደምሰበስብ ሳስረዳ "ቀረፃውን እንኳ የሚፈቅዱልሽ አይመስለኝም!" አሉኝ፡፡ ይህን እውነት ከተለያዩ አካላት ካጣራሁ በኋላ አባ ገዳዎችንና የአካባቢ ሽማግሌዎችን በማሳመንና በማስፈቀድ ፎቶ እና ቪድዮ በፍቃድ እየወሰድኩ በጣም የሚያስቸግረኝን ቦታ ደግሞ ተግባሩን የሚፈፅሙ ሽማግሌዎቹን ቀጥታ በመጠየቅ መረጃዎቼን ለማጠናከር ችዬዋለሁ፡፡ ሌላዉ ዘመኑ የኮሮና በመሆኑ ከመራጃ አቀባዮች ጋር ከሁለት ሜትር በላይ መቀራረብ አይሆንም፡፡ ሰዉም መረጃ ለመስጠት የሚፈራበት ዘመን ነዉ፡፡ እኔ ግን ወሊሶ ተወልጄ ያደኩበት ስለሆነ ብዙ የመራጃ አቀባዮቹ ቤተሰቤን የሚያዉቁ በመሆናቸዉ የምፈልገዉን መረጃ ለማግኘት ችያለሁ፡፡ በ2013 በአገር አቀፍ ስድስተኛዉ ዙር የምርጫ ጊዜ ስለሆነ ብዙ መራጃ አቀባዮቹ ሳይረዱኝ በፊት ለምርጫ ቅስቀሳ መስሎዋቸዉ ፊት የሚነሱኝም ነበሩ፡፡ በአጠቃላይ እነዚህንና ሌሎች ያጋጠሙኝን ችግሮች ለመረጃ አቀባዮቹ የጥናቴን ምክንያት እና እያንዳንዱ መረጃ ለእኔ ያለውን ዋጋ በማስረዳት ፍቃደኝነታቸውን በመግኘት መረጀዬን በመሰብሰብ ጥናቴን አጠናቅቄዋለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል ሶስት አበይት ጉዳዮች ትኩረት የተደረገባቸው ሲሆን የመጀመሪያው ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝት ሁለተኛው ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ሲሆን ሦስተኛው ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የሚሉ ናቸው፡፡ ሶስቱም ጉዳዮች በዝርዝር እንደየ ቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

ይህ ንዑስ ክፍል ስለ ለቅሶ ስርዓት የተፃፉ እሳቤዎች የሚዳሰሱበት ሲሆን ሞት፣ ለቅሶ፣ የለቅሶ ስርዓትና የሙሾ ስርዓት ምንነት የሚሉት ነጥቦች ትኩረት ተደርጎባቸዋል፡፡

### 2.1.1. የሞት ምንነት

የሞትን ምንነት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993፣ 85) ያዘጋጀው መዝገበ ቃላት "የነፍስ ከስጋ መለየት፣ የህይወት ፍፃሜ፣ እልፈት፡፡" ሲል ይገልፀዋል፡፡ በዚህ አገላለፅ መሰረት አንድ ሰው (ማንኛውም ፍጡር) ሞተ ሊባል የሚችለው እስትንፋሱ ከስጋው ስትለይ መሆኑን እንረዳለን፡፡

በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ (1992፣ 62) በተዘጋጀው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ ደግሞ ሞት የሚለው ቃል "የነፍስና የስጋ መለየት ወይም ህይወትን ማጣት፡፡ ይህም በስጋዊም በመንፈሳዊም ሊሆን ይችላል፡፡" የሚል ብያኔ ተሰጥቶት እናገኛለን፡፡ ይህኛው ብያኔ ከቀደመው ብያኔ ጋር የሚመሳሰል ነገር ቢኖረውም መዝገበ ቃላቱን እንዳዘጋጀው ተቋም አስተምህሮ የሚለይ ነገርም አለው፡፡ ይኸውም በዚህኛው አገላለፅ ሞት የሚከሰተው በስጋም በነፍስም ላይ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ይህም ማለት በክርስትናው እምነት መሰረት "የስጋ ሞት" የሚባለው አንድ ሰው ነፍሱ ከስጋው ተለይታ "ሰው" ከሚለው መጠሪያው ተፋቶ "ሬሳ" ተብሎ ሲጠራ ነው፡፡ በክርስትናው ሃይማኖት መሰረት "የስጋ ሞት" ስጋ ከአፈር ስለተሰራ ከነፍስ ሲለይ ወደ ተፈጠረበት አፈር ይመለሳል የሚል ዕምነት አለ፡፡ "የመንፈስ ሞት" የሚባለው ደግሞ ነፍስ የአምላክ እስትንፋስ ስለሆነች ከስጋ እንደተለየች ወደ ፈጣሪዋ እንደምትሄድ ይታመናል፡፡ አንድ ሰው የኃይማኖቱ ቀኖና እና ዶግማ ከሚፈቅደው ውጪ በመሆን ልዩ ልዩ ተግባራትን ፈፅሞ ሲገኝ ነው፤ ከመንፈሳዊ ህይወቱ ተገልሏል፣ ነፍስ የዘራለት ፈጣሪውን አስቀይሟል፣ በመሆኑም እሱ ያለው በአካል እንጂ በመንፈሱ ሞቷል ተብሎም ይታመናል፡፡

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሱት ሁለቱ መዝገበ ቃላት ለመረዳት እንደተቻለዉና ሁሉንም ሰዉ የሚያስማማዉ የሞት ፍቺ አንድ ሰው ሞቷል ተብሎ የሚታወቀው የልብ ትርታው/ምቱ ሲቆምናእስትንፋሱ ሲያቋርጥ፤ ነፍሱ ከስጋዉ ስትለይና እንቅስቃሴ ሲያቆም መሆኑን እንረዳላን፡፡ በዚህ ጉዳይ የወሊሶ አካባቢ የእስልምና እምነት ተከታዮችም ከክርሰትና እምነት ተከታዮች ጋር በተመሳሳይ መልኩ አንድ ሰዉ ስሞት ነፍስ ወደ ፈጣሪዋ (አላህ) እንደ ሄደች ያምናሉ፡፡ (ቃ.መ. መሃመድኑር 10/8/2013)፡፡

የወሊሶ ኦሮሞዎች የሰዉ ልጅ የተወለደ ዕለት ነዉ የሞተዉ የሚል አባባል ወይም አስተሳሰብ ኣላቸዉ፡፡ ይህም ማለት ህይወት ያለው ነገር በመጀመሪያ ይወለዳል፣ ያድጋል ከዛም ይሞታል፡፡ ሞት እና ልደት በተቃራኒ ጽንፍ የቆሙ ክስተቶች ናቸውና ልክ እንደ ኣንድ ሳንትም ሁለት ገጽታ ቁርኚት እንዳላቸዉ ይገልፃሉ፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ የሚሆን ነው፡፡ከአካባቢዉ ማህበረሰብ አንዳንዶች በተለይም ዘመናዊ ሃይማኖቶችን የማያጠብቁት የሞትን ክስተት ሲገልጹ የሚቹን ጦስ የሚወስድለት ሌላ ነገር በማጣቱ ምክንያት ሞተ ብለውም ያምናሉ፡፡ በሌላ አገላለጽ በቤት ካሉት ከብቶች ወይም ሌሎች ህይዎት ካላቸዉ እንስሳት ውስጥ ኣንዱ ቢሞት “ለባለቤቱ የመጣው ሞት/ጦስ/ ለእንስሳው ሆነ” ይባላል፡፡ ባጠቃላይ የሞት አገላለጽ እንደየአካባቢው ሁኔታ ይለያያል እንጂ ሞት ለማንኛው ሰው የማይቀር ዕዳ መሆኑን ከማህበረሰቡ እንረዳለን፡፡ (ቃ.መ. መሃመድኑር 10/8/2013)፡፡

Hertz (1960:27). ሞት ከተኖረበት፣ በአእምሮም፣ በህሊናም፣ በአካልም ከሚሰማው፣ ከሚታየው ተነጥሎ መሄድ ነው፡፡ ሞት ለሰው ልጅ የተለመደ ክስተት እና ውስጣዊ ስሜቶችን በከፍተኛ ሁኔታ ሊቀሰቅስ የሚችል መሆኑን ስለምናምን እኛ ሁላችንም የምንረዳበት መንገድ ነው በማለት ያስረዳል፡፡

### 2.1.2. የለቅሶ ምንነት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት ውስጥ ለቅሶ “ሃዘን፣ ሙሾ፣ ዋይዋይታ፣ መሙሁ፣ ማንባት፣ የእንባ መመንጨት፣ መውረድ፣ መፍሰስ” (1993፣17) በሚል ተገልጾ እናገኛለን፡፡ ሞት ሁሌም ከፍተኛ የሆነ የሀዘን ስሜትን ይፈጥራል፡፡ ይህ ስሜት ደግሞ እንባ በማፍሰስ፣ በጩኸት ወ.ዘ.ተ ሊገለጽ ይችላል ይህም ደግሞ ለቅሶ ይባላል፡፡

### 2.1.3. የለቅሶ ስርዓት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ (1993፣ 17) ባዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት "ለቅሶ" የሚለውን ቃል "ሀዘን፡፡ ሙሾ፣ ዋይ ዋይታ፡፡ መጮህ፣ ማንባት፡፡ የእንባ መመንጨት፣ መውረድ፣ መፍሰስ፡፡" ሲል ይበይነዋል፡፡ ይህ ጥቅስ እንደሚነግረን አንድ ሰው ሲሞት ህብረተሰቡ ሀዘኑን በተለያዩ መንገዶች የሚገልፅ መሆኑን ነው፡፡ ሀዘንተኛው ሀዘኔን ያስታግስልኛል ብሎ የሚያምንባቸውን ማናቸውንም አይነት ተግባራት በሰዓቱ የሚፈፅም መሆኑንም እንረዳለን፡፡

እንደባህሉ እና እንደ አካባቢው የተለያዩ የለቅሶ ክንውኖችና ስርአቶች ይደረጋሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ደግሞ ማህበረሰቡን የሚገልጹ ናቸው፡፡ የተለያዩ ማህበረሰቦች ሰው ሲሞት በተለያዩ መንገዶች ስርዓተ ክዋኔውን ይፈፅማሉ፡፡ ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992፡22-23) "በአንዱ የለቅሶ ስነስርአት ሙሾ እየተደረደረ ደረት ይደለቃል÷ ይዘለላል፡፡ በሌላው ደግሞ የሟች የቅርብ ዘመዶች ፊታቸውን ይቧጥጣሉ÷ ፀጉራቸውን ይነጫሉ፡፡ በቀረው ደግሞ ከበሮ ይዞ በመጨፈር የልቅሶ ክዋኔ ይደረጋል፡፡ በሆታና በድልቂያ ሙታቸውን የሚሰናበቱም አሉ" በማለት ይገልፁታል፡፡

ይህ ሀሳብ እንደሚያመለክተው በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚከወነው የለቅሶ ስርዓት እንደባህሉና እንደ አካባቢው የሚለያይ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን የለቅሶ ስርዓቱ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ እና ከባህል ባህል የሚለያይ ቢሆንም በዓለም ላይ ተመሳሳይ የሆኑ ክንውኖች እንዳሉ በ World Book Encyclopaedia *(vol.7, 1978, 483).*ላይ ተገልጾ እናገኛለን፡፡

> *Funeral customs vary from society to society, but many of the same practices are found throughout the world. These practices include public announcement of the death; preparation of the body; religious ceremonies or other services; a procession; a burial or other form of disposal; and mourning.*

ጽሁፉ እንደሚያመለክተው ተመሳሳይ ከሆኑ ክዋኔዎች መካከል ሟች መሞቱን ማሳወቅ፣ መገነዝ፣ ሃይማኖታዊ ስርዓት መፈጸም፣ ወደ ቀብር ቦታ ጉዞ ማድረግ፣ ሬሳውን መቅበር እና ለሟች ማልቀስ የዓለም ህዝቦች የሚከናወኗቸው ድርጊቶች እንደሆኑ ነው፡፡

### 2.1.4. የሙሾ ስርዓት ምንነት

ሙሾ ሟች በህይወት ዘመኑ የፈጸማቸውን በጎ ተግባራት እያወሱ ቤተሰቦች እንዲሁም ወዳጅ ዘመዶች ሀዘናቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው፡፡ ክዋኔው ተጨባጭ የሚሆነው ሙሾዉ ብቻውን ቀርቦ ሳይሆን በስርዓቱ ላይ ከሚቀርበው አጠቃላይ ክዋኔ ጋር ተዋህዶ ነው፡፡

ደስታ ተክለወልድ(1962፥1016) ሙሾን እንደገለጹት "ለቅሶ፣ ቅንቀና፣ ኸመራ፣ ግጥም፣ ዜማ፣ ቁዘማ፣ እንጉርጉሮ፣ ረገዳ፣ ጭብጨባ ያለበት "ሰቆቃው" ነው ብለውታል፡፡ ሙሾ የሟች ቤተሰቦች የበለጠ እንዲያለቅሱ ሀዘናቸውን እንድገልጹ ለማድረግ ማህበረሰቡ የፈጠረው የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡ በሙሾ ያለፈ ታሪክ፣ ጀግንነትን፣ የአያት ቅድመ አያቶች ጉብዝና፣ ታታሪነት እየተነሳ ይደረደራል፡፡ ሙሾ ደርዳሪው በለቀስተኛው ፊት እያዜመ ሀዘኑን የበለጠ ለማድመቅ የሚያደርገው ስነ ቃላዊ ገለጻ ነው፡፡(ቃ.መ.10/8/13)

በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ በሙሾ ስርዓት (ቦችሳ) ለቀስተኞች የተለያዩ ቁሳቁሶችን (የሟች ልብስ፣ የሟች ፎቶ፣ ጋሻ፣ ጦር፣ ቀጭን ዱላና የመሳሰሉትን) በመያዝ በፈረስ ወይም በእግር በመንቀሳቀስ በግል ወይም በቡድን በመሆን በመፎከር የሟችን ጀግንነት፣ ሩህሩህነት፣ ቸርነት፣ ደግነት፣ የሚገልጹበት ነዉ፡፡ ሁሉም ተመልካች ብቻ ሳይሆን እንባ እያወረዳ፣ እየቆዘመ፣ እየረገዳ (ኦፈን ኦፈን) እያለ በግጥምና ዜማ እየተቀባበለ፣ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ በቅብብሎሽ ሀዘኑን ይገልጻል፡፡ (ቃ.መ.10/8/13)

## 2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

ይህ ጥናት ከፎክሎር ዘውጎች መካከል በሀገረሰባዊ ልማድ ስር በሚጠቃለለው "በለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ትንተና" ላይ ያተኮረ ነው፡፡  ክዋኔ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የሚተገበር ኪናዊ ጉዳዮችን ሁሉ አጠቃሎ የሚይዝ ነው፡፡ እንዲሁም ሰዎች በተግባቦት ሂደታቸው ውስጥ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮቻቸውን የሚገልፁበት መንገድ ነው፡፡ ክዋኔ በራሱ የማህበረሰቡን የእርስ በርስ ትስስር የሚፈጥር ነው፡፡ የአንድ ፎክሎር ክዋኔ እንደየማህበረሰቡ እና ባህሉ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ ክዋኔ ከትንሽ አጋጣሚ እስከ ከፍተኛ ዝግጅት የሚያስፈልገው አጋጣሚ ድረስ ማህበረሰቡ የሚገለገልበት እና ራሱን የሚገልጽበት መንገድ ነው፡፡ Finnegan (1992:95) "ክዋኔ የሚተገበረዉ በከፍተኛ ሁኔታ ተደራጅቶ እና በታቀደ ወይም ባልታቀደ ሁኔታ ነዉ" በማለት የክዋኔን መከሰቻ አጋጣሚዎች ገልጸዋል፡፡

በክዋኔ መሰረታዊ ጉዳዮች የሚባሉት በዋናነት ከዋኝ፣ ታዳሚ እና አውድ ናቸው፡፡ ይህን ቁርኝት Bauman (1992፡4) "ክዋኔ ማለት ጥበባዊ ድርጊት ሆኖ የክዋኔውን ድባብ ከዋኞቹንና በውስጡ ያለውን እምቅ ጥበቡን ታዳሚውን እና መቼቱን የያዘ መሆኑን ወይም ክዋኔ በውስጡ በርካታ ነገሮችን የያዘ እና አንድ ክዋኔ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ የከዋኙን የአከዋወን ብቃትና የመድረክ አያያዝ ችሎታ ያሳያል" በማለት ይገልጹታል፡፡

**ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ፡-** በዋናነት በመስክ ጥናትና ምርምር ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ስለ ተጠኚው ማህበረሰብ ወይም ቡድን ዝርዝር መረጃ ከነባራዊ ሁኔታዎች መሰብሰብን ይጠይቃል፡፡ Bauman (1975) እንዲህ በማለት ገልጸውታል፡፡ የአንድ ድርጊት ክዋኔ ከዋኙ ለተመልካች ኃላፍነት በመዉሰድ መልእክትን የሚያስተላልፍበት መድረክ ነው፡፡ ተመልካችም ከቀረበለት ሀሳብ በመነሳት የቀረበው ርዕስ እና የአቅራቢ ችሎታ እውቀት በመገምገም ምላሽ የሚሰጥበት መድረክ ነው፡፡

> *Performance involves on the part of the performer an assumption of accountability to an audience for the way in which communication is carried out, above and beyond its referential content. From the point of view of the audience, the act of expression on the part of the performer is thus marked as subject to evaluation for the way it is done, for the relative skill and effectiveness of the performer's display of competence (Bauman: 1975:293).*

ስለ ከዋኝ፣ ታዳሚ እና አውድ አጠር ኣድርገን ለማየት ስንሞክር፡- **ከዋኝ** በተለይ በለቅሶ ስርዓት ላይ ሟችን የሚመለከቱ ጥሩ ተግባራት እያነሳ (በሙሾ፣ በፉከራ ወይም በቀረርቶ) ሊሆን ይችላል እየገለጸ ወዳጅ ዘመዶች ሃዘናቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፡፡ **ታዳሚ** በክዋኔ ውስጥ የሚነሳ ሌላው ጉዳይ ሲሆን ለክዋኔው ህልውና ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ታዳሚዎች የሚጫወቱት ሚና እንደፎክሎሩ አይነት ቢለያይም በአድማጭነት፣ በማጨብጨብ፣ በመቀበልና በመሳሰሉት ለክዋኔው አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ በአንዳንድ ባህሎች በተለይ በሙሾ ክዋኔ ወቅት በሙሾ ደርዳሪ (አልቃሽ) እና በሙሾ ተቀባይ መካከል የሚደረገው መስተጋብር ታዳሚው በክዋኔው ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ሚና የሚያሳይ ነው፡፡ በክዋኔው ወቅት ሙሾ በመቀበል፤ ደረት በመምታት፣ በመዝለል፣ በማልቀስ ወዘተ ይሳተፋሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሙሾው ክዋኔ ወቅት የሚፈጠረው መስተጋብር ወይም ቅብብሎሽ በአንድነት መከወኑ የሚታይበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

በመሆኑም የክዋኔው ውጤታማነት እና ግብ መቿነት የሚወሰነው በከዋኞች እና በታዳሚዎች ብቃት፣ እድሜ፣ ጾታ፣ ባህርይና ሚና ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች በወቅቱ የሚከሰቱ ወይም ባሉ ዓውዳዊ ነገሮች ላይ የተመሰረቱ እንደሆኑ ምሁራን ያስረዳሉ (Sims and Stephens, 2005:132)፡፡

**አውድ** ለአንድ ክዋኔ ቅርጽና መዋቅር እንዲሁም የሚተላለፈው መልእክት መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም አውድ ክዋኔዉ በሚከወንበት ጊዜ የሚፈጠረውን አጠቃላይ የከዋኙ ማንነት፣ የታዳሚው ፈጠራና ተሳትፎ የሚከወነው ነገር ጊዜና ቦታ ቁሳቁሶች በቅንጅት ተደራጅተው ገላጭና ጥበባዊ በሆነ መንገድ የሚቀርብበት የእርስ በርስ ግንኙነትና መስተጋብር የሚቀርብበት ተፈጥሯዊ መቼትና ማህበራዊ አውድ ነው (Dundes 1980)፡፡

Bauman (1986፡363) አውድን ሲገልጽ ባህላዊ አውድ እና ማህበራዊ አውድ በማለት ከፍሎአቸዋል፡፡ **ባህላዊ አውድ**፡- በውስጡ ልማዳዊ ተግባራትን እና የሰዎቹን አኗኗር፣ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ እምነት በፎክሎር ውስጥ የተቀረፀበትን መንገድ የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም እንደ ዝምድና፣ ጉርብትና ከበራ ወዘተ ያሉ ተቋማትን እንዲሁም የመስተጋብር መንገዳቸውን ያመላክታል፡፡ ማህበረሰቡ የመፈቃቀርን የመተሳሰብን ገጽታ እንዲሁም ለእያንዳንዱ የፎክሎር አይነት በየባህሉ የሚሰጠውን ትርጉም እና ትዕምርታዊ ግንኙነቶችን ይገልጻል፡፡ ባህላዊ አውድ የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ እንዲሁም የህልውና መሰረት የሆነ ማህበረሰቡ ራሱ የሚፈጥረው፣ የሚተገብረው፣ የሚከውነው፣ የሚያከብረውና የሚገዛለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ባህላዊ አውድ የፈጠራና የአዳድስ ግኝቶች ምንጭና የሀገር በቀል ዕውቀቶች ትብብር የመሰረት ድንጋይ የዕውቀት መገለጫናማስተላለፊያ መንገድ በመሆን የነገን ተግዳሮቶች ለመቋቋምና የማህበረሰቡን ልማድ ለማጥበቅ የሚያስችል ነው፡፡

**ማህበራዊ አውድ**፡- ማህበራዊ አውድ የምንለው ደግሞ የከዋኙን እና የታዳሚን ማንነት፣ ጾታ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ሀይማኖት የሚመለከት ነው፡፡ በአንድ ክዋኔ ላይ የሚታዩ የከዋኝን እና የታዳሚን ስብጥር፣ በክዋኔው ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ፣ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር ያላቸውን ግንኙነት የምናይበት ነው፡፡ በአንድ የፎክሎር ክዋኔ ውስጥ የክዋኔውን መጀመርና መጠናቀቅ እንዲሁም እየተከወነ መሆኑን የሚያሳውቁ ጠቋሚዎች መኖራቸውን Sims & Stephens(2005፡141) "… devices or actions mark the ends and beginnings of performances." በማለት ይገልጻሉ፡፡

እነዚህ ጠቋሚዎች በከዋኙና በታዳሚ መካከል ያለ መስተጋብር እንዲሰምር የሚያደርጉ፣ የክዋኔውን ስርዓት መልክ የሚያሲዙ፣ የከዋኙንና የታዳሚን የክዋኔ ቅደም ተከተል የሚያሳውቁ እንዲሁም ማህበረሰቡ ይሁነኝ ብሎ ተስማምቶ የፈጠራቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ስምምነቶች በክዋኔው ወቅት ምን መደረግ እንዳለበት ወይም የእያንዳንዱን የስራ ድርሻ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን ከተለመደው የማህበረሰቡ የአከዋወን ስልት እንዳይወጣ የክዋኔ ጠቋሚዎች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የታዳሚና የከዋኝ እንቅስቃሴ፣ መከወኛ ቁሳቁሶች በአንድ ክዋኔ ውስጥ ክዋኔ ጠቋሚዎች ሊሆኑ  ይችላሉ፡፡ እነዚህ ጠቋሚዎች ታዳሚዎች  በክዋኔው በንቃት እንዲሳተፉ፣ እረፍት እንዲወስዱ፣ እንዲሁም ከአንዱ ድርጊት ወደ ሌላ ድርጊት እንዲሸጋገሩ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

ጥናቱ የሚከተለው ንድፈ ሃሳብ የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሃሳብ የተመረጠበት ምክንያት ጥናቱ ክዋኔ ተኮር በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ንድፈ ሃሳብ ክዋኔውን፣ የሚከወንበትን አጋጣሚ፣ ታዳሚን፣ የክዋኔ ቦታና ማህበራዊ አውዶችን፣ መልዕክትና ጠቅላላ አቀራረቡን የሚመለከት በመሆኑ ነዉ፡፡ በዚሁ መሰረት ይህን ንድፈ ሃሳብ ከሞት በፊት፣ በጊዜ ሞት፣  ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ የሚከወኑ ክዋኔዎችን ለመተንተን ተጠቅሚያለሁ፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው የኤም ኤ ዲግሪ ጥናቶች የተዳሰሱበት ነው፡፡ በዳሰሳው የጥናቱ አላማ ምን እንደሆነ እና ምንምን ነጥቦች ላይ እንደሚያተኩሩ እንዲሁም ጥናቶቹ ያላቸዉን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ተመልክቻለሁ፡፡ በዚህ ክፍል ትኩረታቸውን በለቅሶ ስርዓት ክዋኔና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ያደረጉ ስድስት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፎችን ቃኝቻለሁ፡፡ ጥናታዊ ጽሁፎቹ በቀረቡበት ዘመን ቅደም ተከተል የቀረቡ ሲሆን በአንድ ዘመን የተገኙት ጥናቶች ደግሞ በአጥኚዎቹ ስም ፊደል ተራ ቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

በመጀመሪያ የተቃኘው ህይወት አበሩ (በ2003 ዓ.ም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) "የመኢኔት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" በሚል ርዕስ ያቀረበችው ነው፡፡ የህይወት ጥናት አላማ የመኢኔት ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔውን ከመግለጽ በተጨማሪ በስርዓቱ ላይ የሚቀርቡ ትዕይንቶችን ትርጉምና ተግባር ይገልጻል፡፡ ጥናቱ የመስክ ምርምርን መሰረት አድርጎ የተካሄደ ሲሆን መረጃዎቹ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም በቡድን ውይይት የተሰበሰቡ

ናቸው፡፡ መረጃዎቹም ስለ ባህሉ እውቀት አላቸው ከተባሉ አዛውንቶች፣ ከሃይማኖት መሪዎች፣ ከጎሳ መሪዎች፣ ከቤት እመቤቶችና ከባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ሃላፊዎች የተገኙ ናቸው፡፡ ጥናቱ በሁለት ማህበራዊ ደረጃና በአሟሟት ሁኔታ ተከፍሎ፣ በቀብር ስርዓት አፈጻጸም፣ በግንዘት፣ በቀብር ቦታ መረጣ እና በስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ድርጊቶች አንጻር ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ እነዚህም ስርዓቶች የሞተውን ሰው ማህበራዊ ደረጃ የሚገልጹና በማህበረሰቡ ዘንድ የሚሰጠውን ከበሬታ የሚያሳዩ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚከወኑትን ድርጊቶች ከማሳየት በተጨማሪ የስርዓቱን ማህበራዊ ፋይዳ እና ተግባራት አጥኚዋ ገልጻለች፡፡ ስርዓቱ ለብሄረሰቡ ታሪክን ከማቆየት አንጻር ያለው ፋይዳ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ተቋማትን ከማስጠበቅ አንጻር ያለው ፋይዳ፣ የማህበረሰቡን  አመለካከት፣ እምነት ከመግለጽ አንጻር እንዲሁም የለቅሶ ስርዓቱን ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚያደርገው የማህበረሰቡ ትጋት ምን እንደሚመስል መፈተሸ በጥናቱ የተተኮረባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በስርዓተ ክዋኔው ትንተናም በዕድሜ ከህጻንነት እስከ አቅመ አዳም/ሄዋን ለደረሱ እና ለዕድሜ ባለጸጋዎች፣ በስልጣን ለባለቃልቻዎች እና ለጎሳ መሪዎች እንዲሁም ከአሟሟት ሁኔታ አንጻር በሰው ለተገደለ የሚደረጉ ስርዓቶችን ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ሞት ያለውን ክዋኔ አቅርባለች፡፡ በተለይ ጥናቱ የሚያተኩረው የ"ኔይሬን" ባህላዊ እምነት ተከታዮች ላይ ነው፡፡ ከላይ የታዩት ጥንካሬዎች እነዳሉ ሆነዉ አጥኚዋ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ የሌላ ሀይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ለምን አላሳየችም? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ በተጨማሪም በክዋኔው ወቅት የሚታዩ ስነ ቃሎችን ጥናቱ አለማካተቱ ሌላ ጉድለት ነው፡፡

ዘላለም ፋንቱ (2004 ዓ.ም ) "የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ" ሲል ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ፅሁፍ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፉን አቅርቧል፡፡ የዘላለም ጥናት ዋንኛ ዓላማዎች ሁለት ናቸው፤ የመጀመሪያው የብሔረሰቡን የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ምን እንደሚመስል ማሳየት የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በለቅሶ ስርዓት ክዋኔው ወቅት የሚስተዋሉ ችግሮችን መግለፅ ነው፡፡ አጥኚው እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ተፈጥሯዊ መቼት ላይ ተገኝቶ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት አድርጓል፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተጠቅሞ ያገኛቸው ግብዓቶች "ብሔረሰቡ የተለያዩ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔዎችን በሟች ማንነት እና ምንነት ላይ ተመስርቶ የሚያካሂድ መሆኑን" እንደጠቆሙት ይገልፃል፡፡ አጥኚው እዚህ ማጠቃለያ ላይ እንዲደርስ ያስቻሉትን ልዩ ልዩ መረጃዎች "የቅድመ ሞት ዝግጅት"፣ "ጊዜ ሞት"፣ "ድህረ ሞት የሚደረጉ

ስርዓቶች"፣ "ጉዞ ወደ ቀብር"፣ "በቀብር ወቅት የሚደረጉ ስርዓቶች"፣ "ድህረ ቀብር ክንዋኔዎች" እና "የቀጠሮ ለቅሶ" በሚሉ ንዑሳን ክፍሎች ከፋፍሎ ዘርዘር በማድረግ አቅርቧል፡፡

ዘላለም የመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ መሳሪያዎቹን በተገቢው መንገድ አልገለፀም፡፡ ይህም ማለት ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን እንዴት እና በምን መልኩ እንደተጠቀመ ካለመግለፁም በላይ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምን ስለ መሆናቸው እና እንዴት ጥቅም ላይ መዋል እንዳለባቸው የምሁራንን ሀሳብ በመጥቀስ ሊያስረግጥ አልቻለም፡፡

አየሁሽ ቶማ (2005 ዓ.ም) "የወላይታ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ" በሚል ርዕስ የኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቷን ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አቅርባለች፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ "የወላይታ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ያለውን ገጽታ በማሳየት ትዕምርታዊ ለሆኑ ጉዳዮች ማህበረሰቡ የሚሰጠውን ባህላዊ ፍቺ መመርመር" የሚል ነው፡፡ አየሁሽ ይህንን ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ ከ12 ሰዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ፣ በአንድ የዕድሜ ባለፀጋ የለቅሶ ስርዓት ላይ በመገኘት ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት አካሂዳለች፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅማ ያገኘቻቸውን መረጃዎች በክብረ በዓላት እና በክዋኔ መር የትወራ ማዕቀፍ ቅንብር ውስጥ ሆኖ ገላጭየምርምር ዘዴን ተገልግላ ትንተናዋን አቅርባለች፡፡ አየሁሽ በጥናቷ ግኝት ማህበረሰቡ በባህላዊ የለቅሶ ግጥሞቹ ሞትን መናቁ፣ በሞት ህይወትን ማስታወሱ፣ ሟች በአካል እንጂ በመንፈስ እንደማይሞት መታሰቡ፣ ለቅሶ የማህበራዊ ትስስር መፍጠርያ ወይም ማፍረሻ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ እንዲሁም ዘመነኛው የለቅሶ ስርዓት ከነባሩ የለቅሶ ስርዓት ጋር ሲነፃፀር በርካታ ለውጦች እንደሚስተዋሉ አመላክታለች፡፡ በመጨረሻም የለቅሶ ቃል ግጥሞቹ ተሰብስበው ቢጠኑ ከመሰነ ድም ባለፈ የህብረተሰቡን ማንነት እና አመለካከት የበለጠ ለመረዳት የሚያስችሉ መሆናቸውን ጠቁማለች፡፡ አጥኚዋ በጥናቷ ሰፊና ዝርዝር ጉዳዮችን በማንሳት ትንታኔ ያቀረበች ሲሆን በጥናቱ ውሰጥ በሰፊው የትዕምርቶች ትርጉም የሚታይ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የአካባቢውን ባህል እና ቋንቋ ማወቋ ሳይጠቅማት እንዳልቀረ መገመት ይቻላል፡፡ አንዳንዶቹን የሙሾ ግጥሞች ከሚቀርቡበት አውድ ጋር አጣምራ ማቅረብ ብትችል ኖሮ ስራው ይበልጥ የተዋጣለት ይሆን ነበር ብዬ አስባለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መረጃዎቿን የሰበሰበችባቸውን አካባቢዎች በግልፅ አለማስቀመጧም እንደችግር ሊታይ የሚችል ነው፡፡

ውቤ ታደገ (2005 ዓ.ም) "የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" ሲል የኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቱን ለኢ.ትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አቅርቧል፡፡ ውቤ "የቤንች ብሔረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ"ን በስፋት ዳሷል፡፡ አጥኚው የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን ትኩረት ሰጥቶ ተመልክቷል፡፡ በዚህም "የባለቃልቻዎች የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ"፣ "የባላባት እና የባለሚያንግ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ"፣ "የእድሜ ባለፀጎች የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ"፣ "የወጣቶች የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" እና "የሕፃናት የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" እንዴት እንደሚከወን የእያንዳንዱን አካላት የለቅሶ ስርዓት ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ በሚል በሰፊው ተንትኖ አቅርቧል፡፡

ውቤ የጥናቱን ዘዴ እና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምንነት፣ እንዴት ከጥናቱ ጋር እንደሚገናኝ እና በምን መልኩ ሊጠቀምበት እንደሚፈልግ ከምሁራን ሀሳብ አጣቅሶ በግልፅ ማሳየቱ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅት አገልግሎት ላይ ስለሚውሉ ቁሶች ትርጓሜ መስጠቱ እንዲሁም በስርዓቱ ወቅት የሚደረደሩትን የሙሾ ግጥሞች በስፋት ተንትኖ ማቅረቡ የጥናቱን ጥንካሬ ያሳያል፡፡

በውቤ ጥናት ውስጥ እንደ ክፍተት ከሚታዩ ነገሮች መካከል ውቤ ጥናቱ በ"ክዋኔ መር" የትወራ ማዕቀፍ መሆኑን በአግባቡ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ይህንኑ የትወራ ማዕቀፍ በሌላ መልኩ የጥናቱ ዘዴ አድርጎ ለመጥቀስ መሞከሩ አግባብ መስሎ አልታየኝም፤ ክዋኔ መር የትወራ ማዕቀፍ አንዴ እንደ ንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደ ዘዴ ባይገለጽ የተሻለ ይሆናል፡፡

ደስታ ወ/መስቀል (2006 ዓ.ም )ጥናታዊ ፅሁፉ "የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረው በዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ ሲሆን የጥናቱ አላማ የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ ገላጭ ትንተና በማድረግ ስርዓቱን ማሳየት ነው፡፡ አላማውን ለማሳካት በዋናነት ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተካሂዷል፡፡

በሶስት ተፈጥሯዊ የለቅሶ መቼቶች ላይ በመገኘት መረጃው ተሰብስቧል፡፡ በተገኘው መረጃ መሰረት የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት በአራት ተከፍሎ እንደሚከወን ታውቋል፡፡ በዲዚ ብሄረሰብ በእድሜ፣ በጾታና በማህበራዊ ደረጃ አንፃር የተለያዩ የለቅሶ ክዋኔዎች መኖራቸው ተገልጧል፡፡ ከማህበራዊ ደረጃ አንጻር ሟች የጎሳ መሪ፣ የሐገር ሽማግሌ፣ የእምነት መሪ ወዘተ ከሆኑ የሚከወንላቸው ስርዓት የሟችን ተግባርና ማንነት የሚያመለክቱ ሲሆን የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔውን ከዕድሜ እንዲሁም ከጾታ አንጻር ስንመለከተው የሴት እና የወንድ በቀብር ቦታ አቆፋፈር እና የቀብር አቅጣጫን

እንደሚወስኑ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ የጥናቱ ግኝት የለቅሶ ስርዓቱ የባላባት ስርዓት ሽግግርን የሚያጠናክሩበት እና የሚገነቡበት ማህበራዊ አንድነታቸውን የሚያጠናክሩበት እንዲሁም የማህበረሰቡን ታሪክ፣ እምነትና አመለካከት የሚገልጹበት መንገድ መሆኑን ያሳያል፡፡ በክዋኔ ውስጥም የሚተላለፉ መልዕክቶች እና ትርጓሜዎች በጥናቱ ውስጥ ተካትተዋል፡፡

በጥናቱ ገላጭ የምርምር ዘዴን እንደተጠቀመ እንዲሁም የመረጃ አተናተን ዘዴዉም አይነታዊ የመረጃ አተናተን ስልት እንደሆና ቢገልጽም እነኚህን ዘዴዎች ለምን እንደመረጠ በምሁራን ሀሳብ ቢያጠናክርና የተጠቀመዉን ሀሳብ ምንጩን በመጥቀስ እዉቅና ቢሰጥ ጥሩ ይሆን ነበር፡፡ ሌላዉ ጉዳይ መረጃዎች ከሚሰበሰቡበት ዘዴ ዉስጥ አንዱ የሆነዉን ምልከታን ተጠቅሟል፡፡ከምልከታ አይነቶች ውስጥም ለጥናቱ የተጠቀመዉ ኢተሳትፏዊ ምልከታን (non participatory observation) ሲሆን ይህ ደግሞ የማህበረሰቡን ባህል እና ቋንቋ በማወቅ ከማህበረሰቡ ጋር በስርዓቱ ዉስጥ በቀጥታ በመሳተፍ ክዋኔዉን ሙሉ በሙሉ ለመረዳት ስለማያስችለዉ እንደክፍተት ተመልክቼዋለሁ፡፡ ስለዚህም በእንድህ አይነት ሀገረሰባዊ ልማድ ላይ ጥናት የሚሰራ አጥኚ ምልከታዉን የሚያካሄዳዉ ተፈጥሮአዊ መቼቱን መሰረት በማድረግ በተሳትፏዊ ምልከታ ስልት ቢሰራ የተሻለ ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡ በስተመጨረሻ በጥናቱ ዉስጥ እንደ ክፍተት ያየሁት ጉዳይ ጥናቱን በሚያጠናበት እና መረጃዎችን በሚሰበስብበት ጊዜ የተለያዩ ችግሮች እንዳጋጠሙት በመግለጽ ከእነዚህም ችግሮች መካከል ለተወሰኑት መፍትሄ በመፈለግ ለማቃለል እንደቻለ ቢገልጽም በጥናቱ ወቅት ሌሎች (የቋንቋ፣ የመጓጓዣ እጥረት፣ እና ለባህሉ እንግዳ መሆን፣ ወዘተ) ያጋጠሙት ተጨማሪ ችግሮች መሆናቸዉን ከመግለጽ ዉጪ መፍትሄ መስጠቱን አልገለጸም፡፡ ይህ ደግሞ የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ እንዲሁም ግኚቱ እንዴትና ምን ያህል እንደተሳካ ጥያቄ ይፈጥራል፡፡

ሚሮን ሞላ (2011 ዓ.ም) ጥናቱ "በጭልጋ ወረዳ በቅማንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የጥናቷ ዋና ዓላማ በጭልጋ ወረዳ በተመረጡ አራት ቀበሌዎች በሚኖሩ የቅማንት ማህበረሰብ የሚከወነውን የለቅሶ ስርዓት መግለጽና በገላጭና ተንታኝ ዘዴ በስርዓቱ የሚፈፀሙ ድርጊቶችን፣ የሚባሉ የሙሾ ቃል ግጥሞችን እንዲሁም የሚያዙ ቁሳቁሶችንና ምርቃትን መተንተን ነው፡፡

ጥናቱ ያተኮረው በገላጭና ተንታኝ የአጠናንዘዴ ነው፡፡ መረጃዎች የተሰበሰቡት በተፈጥሮ መቼት ላይ ሲሆን ዘዴዎቹም ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር

ውይይት ናቸው፡፡ በመረጃ ሰጪነት የተሳተፉትም ባህሉን፣ ወጉን፣ ልማዱን የሚያውቁት መረጃ ሰጪዎች እንደሆኑና መረጃው በድምጽና በፎቶ ግራፍ ተሰብስቧል፡፡ ጥናቱ ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ እና ስርዓት ንድፈ ሀሳብን የተከተለ ነው፡፡ ጥናቱ ለመረጃ የሞት ክስተት በተከሰተበት በመገኘት በተሳትፏዊ መረጃ አሰባሰብ በቦታዉ በመገኘት ስርዓቱን በመመልከት መሰብሰቡን እንደ ጠንካራ ጎን ተመልክቼዋለሁ፡፡ በጥናቱ ዉጤትም በቅማንት የለቅሶ ስርዓት ላይ የሙሾ ቃል ግጥሞች፣ የሚያዙ ቁሳቁሶች የሚችን ማንነትና ያከናወኗቸውን ተግባራት የሚያንፀባርቁ ሆነው መገኘታቸዉ ተገልጧል፡፡ሚሮን ከመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች አንዱ የሆነዉን ምልከታን መጠቀሟን ገልፃለች ይሁን እንጂ ምን አይነት የምልከታ ዘዴን እንደተጠቀመች ለይታ አለመጥቀሷን እንደጉድለት አይቼዋለሁ፡፡ ሌላዉ ደግሞ የመረጃ አተናተኗ ጥሩ ሆኖ እያለ ግን በብዛት ከዝርዝር አላማዎቿ በህይማኖት ጉዳይ ዙርያ ላይ ሰፊ ትኩረት በማድረግ ሌሎችን እምብዛም ሳትገልጻቸዉ አልፈዋለች፡፡

በአጠቃለይ ከዚህ በላይ የተዳሰሱት የተዛማጅ ጥናቶች ክለሳ ስድስት ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የተጠኑ ጥናቶች ናቸው፡፡ የእኔ ጥናት ከእነዚህ ጥናቶች ጋር ሙሉ በሙሉም ባይሆን በከፊሉ የሚያመሳስለው የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን የሚነኩ መሆናቸው እና በከፊሉም ቢሆን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቻችን ናቸው፡፡

ከእነዚህ ጥናቶች የእኔ ጥናት እንዲለይ የሚያደርገው ዋናዉ ጉዳይ ደግሞ የተጠናበት ማህበረሰብ መለያየት ሲሆን ሌሎች የጥናቱ ዘዴ እና የጥናቱ ሂደትም እንዲሁ የሚለያዩበት ሁኔታ ስላለ ከላይ ለእያንዳንዳቸዉ በዳሰሳዉ ወቅት እንደ ጉድለት ያየሁትን ክፍተት በማሟለት እንዲሁም ደግሞ በዳሰሳዬ የተካተቱት አጥኚዎች በተመሳሳይ መልኩ በጥናታቸዉ ዉስጥ ጥናታቸዉ ምን አይነት ክፍተት እንዳለዉ ለሌላ ቀጣይ አጥኚ (ተመራማሪ) አለመስቀመጣቸዉንም እንደ ጉድለት ስለገመገምኩኝ እኔ ደግሞ ጥናቴን እነኚህን ክፍተቶች በመሙላት ያጠናሁ መሆኔ የተለያ ያደርገዋል፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ የዋለው ገላጭ የምርምር ንድፍ (descriptive research method) ነው፡፡ ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ ገለፃ በትንታኔ ወቅት የምናስቀድመው ተግባር ሲሆን እኛ ያየነውን ክዋኔ ያላዩት ሰዎች በአእምሯቸው እንዲቀርፁት ማድረግ ስለሚያስችል ነው፡፡ በተጨማሪም በተፈጥሮአዊ መቼቶች በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ትንታኔ ለመስጠት ስለሚረዳ ነው፡፡ "የገላጭ የምርምር ዘዴ ሂደት ተፈጥሯዊ መልክ ያለው ሲሆን ምልከታ በማካሄድም ያዩትን መመዝገብ፣ የመዘገቡትን በተገቢው መንገድ መግለፅን ያካትታል" (ያለው፣1998፣21)፡፡

ከዚህም በመነሳት በተካሄደው ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ዉይይት የሚነገሩ ስነ ቃሎችን፣ የተያዙ ቁሶችንና የሚደረጉ ስርዓቶችን እንዲሁም የክዋኔ /performance/ እና የስርዓቱ /Ritual/ ሂደት መረጃ ተሰብስቧል፣ የተሰበሰባዉም መረጃ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ጥናቱ የተከተለው ንድፈ ሃሳብ የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ እንደመሆኑ መጠን ማህበረሰቡ በለቅሶ ላይ ሀገረሰባዊ ልማድን እንዴት እንደሚገልፅ፣ በጊዜ ሞት ክዋኔ፣ በቅድመ ቀብር ክዋኔ፣ የቀብር ጊዜ ክዋኔ እና በድህረ ቀብር ክዋኔ በመግለጽና በመተንተን ባህላዊ ስርዓቶችን በማሳየት ተካሀዷል፡፡

### 3.1. የመረጃ ምንጮች

ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ መረጃዎች ከቀዳማይ መረጃ ምንጮችና ከካላይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡

ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የጥናቱ ትኩረት የሆኑት የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ሲሆኑ፤ በመስክ ስራ ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከካላይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ከዚህ ቀደም በርእሰ ጉዳዩ ላይ የተሰሩ ጥናቶችን በመቃኘት፣ የተለያዩ መጻሕፍትን፣ ጆርናሎችን፣ የመረጃ መረቦችን እና መዛግብትን በመጠቀም የተገኙ ናቸው፡፡

### 3.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች

በዚህ ጥናት በአጠቃላይ ወሳኝ (Nonprobability sampling) የናሙና አመራረጥ ዘዴን ተግባራዊ አድርጌያለሁ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ከጥናቱ አላማ አንጻር ናሙናዎቹን የሚፈለገውን መረጃ ይሰጡኛል ብዬ ያመንኩባቸውን መረጃ አቀባዮች ለመምረጥ እድል የሚሰጡ የናሙና አመራረጥ ስልቶችን በውስጡ የያዘ በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት

ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች የሚያቀብሉ መረጃ ሰጪዎች ባህሉንና የማህበረሰቡን ታሪክ እና ወግ ጠንቅቀው የሚያውቁና የሚገልጹ መሆን ስለሚገባቸው ነዉ፡፡ እንድሁም ክዋኔዉን በቦታዉ በመገኘት በምልከታ መረጃ ስለተሰበሰባ እነዚህን መረጃዎች በተገቢው መንገድ የሚሰጡኝን ሰዎች ለመምረጥ በማስቻሉ አላማ ተኮር የንሞና ዘዴ (purposive sampling method) ተጠቅሜያለሁ (ያለው 1998፤ 132)፡፡

በዚህ ሂደት በወሊሶ ከተማ አራት ቀበሌዎች እና በአካባቢዋ ከሚኖሩት ነዋሪዎች ዉስጥ ሃያ አምስት መረጃ አቀባዮች የተመረጡ ሲሆን፤ በዕድሜ ከፍ ያሉ የእድሜ ባለጸጋ የሆኑ ሁለቱም ጾታዎች፣ የሀይማኖት መሪዎች፣ አባገዳ፣ ሃደሲቄ፣ የእድር መሪዎችና ወጣት (ፎሌ) የሆኑትን አከቷል፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ይህ ርዕሰ ጉዳይ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች የሚሰበሰቡበትን ዘዴ የሚመለከት ሲሆን በዋናነት የሚከተሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡ እነርሱም፡ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና የቡድን ተኮር ዉይይት ናቸዉ፡፡ እነዚህ ሶስቱ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተመረጡበት ምክንያት፡ እያንዳንዱ የመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን ስላለዉ ነዉ፡፡ በመሆኑም የአንዱን ድክመት የሌላዉ ጥንካሬ እንዲሸፍንልኝ ለማድረግ ነዉ፡፡

### 3.3.1. ምልከታ

ምልከታ ቀዳማይ መረጃ ከሚሰበሰቡባቸው መሳሪያዎች መካከል ኣንዱ ሲሆን አጥኚዋ የማህበረሰቡን ስርአትና ባህል አውዱን መሰረት አድርጎ የተለያዩ የስሜት ህዋሶቹን በመጠቀም የሚገነዘብበት ነው፡፡ ምልከታ ተመራማሪዋ ተጠኚዎቹ (እያወቁም ሆነ ሳያዉቁ) በሚገኙበት ቦታ በመሆን በዚያ ወቅት ምን እንደምሰሩ፣ እርስ በርሳቸዉ እንዴት እንደሚግባቡ፣ ምን እንደሚናገሩ በሚመቸዉ መንገድ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነዉ፣ (ያለው፣ 2004 ዓ.ም፣183)፡፡ በተጨማሪም ከምልከታው በመነሳት የተለያዩ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች መንደፍ የሚያስችል በመሆኑ ምልከታውን ማካሄድ ያለው ጠቀሜታ ላቅ ያለ ነው፡፡

ከምልከታ አይነቶች ውስጥ ለጥናቴ የተጠቀምኩት ተሳትፏዊ ምልከታን (participatory observation) ነው፡፡ ይኸውም የማህበረሰቡን ባህል እና ቋንቋ ስለማዉቅ ከማህበረሰቡ ጋር በስርዓቱ ዉስጥ በቀጥታ በመሳተፍ ክዋኔዉን ሙሉ በሙሉ ለመረዳት

ስለሚያስችለኝ ነው፡፡ ስለዚህም ምልከታዉ የተካሄዳዉ ተፈጥሮአዊ መቼትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ምልከታውን የተሟላ ለማድረግ በምልከታው ወቅት በፎቶግራፍና በቪዲዮ በመቅረፅ ትክክለኛውን መረጃ ለትንታኔው ተጠቅሜያለሁ፡፡

### 3.3.2. ቃለ-መጠይቅ

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በምልከታ ወቅት ያልተመለሱልኝን ጥያቄዎች ለመመለስ እና በምልከታ ወቅት ያየኋቸው እና ማህበረሰቡ እንዲመልስልኝ የፈለኳቸውን ለማጠናከርያ የሚጠቅሙኝን ጥያቄዎች ለማቅረብ የረዳኝ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡

ቃለ መጠይቅን የሚለየዉ ጉዳይ በመላሽና በጠያቂው ሰው መካከል የፊት ለፊት የቃል ምልልስ መኖሩ ነው፡፡ አለም (2001፣16) ቃለ መጠይቅን ሲገልፁ "ቃለ መጠይቅ ጠያቂ ከተጠያቂው ጋር በግንባር ተገናኝተው በቃል ምልልስ መረጃ የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡"

ያለው (2004 ዓ.ም፣178)፡፡ ስለ ቃለመጠይቅ አጠቃቀም ሲገልጹ "አንድ ተመራማሪ ከዉስን ቃለመጠይቅ (Structured interview)፣ ከፊል ነፃ ቃለመጠይቅ (Semistructured interview) እና ከነፃ ቃለመጠይቅ (Unstructured interview) ዉስጥ በአንዱ፣ በሁለቱ ወይም በሦስቱም መጠቀም ይችላል" ባሉት መሰረት መረጃውን ከመረጃ አቀባዮች መሰብሰብ ይቻል ዘንድ ቃለ መጠይቁ በሁለት መንገድ የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው መረጃ አቀባዮችን ከመጠየቄና ከማግኘቴ በፊት ቀድሜ ዉስን ቃለመጠይቅ አዘጋጀሁ፡፡ ይህም ሰፋ ያለ ውይይት ለማድረግ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር ተገናኝቼ ቃለመጠይቅ በማደርግላቸው ወቅት ከማያቸውና ከምሰማቸው መረጃዎች በመነሳት ለምን? እንዴት? ከዚያስ? ወዘተ በማለት ለመጠየቅ ተጠያቂዎችም እንዲሁ በነፃነት መልስ ይሆናል ብለዉ የሚገምቱትን እና ያመኑትን መረጃ የሚሰጡበት ነፃ ቃለመጠይቅ አካሀጄዋለዉ፡፡

ለቃለ-መጠይቅ የተመረጡት ተሳታፊዎች በአላማ ተኮር ናሙና አመራረጥ ዘዴ አማካይነት በወሊሶ ከተማ አራት ቀበሌዎች እና በአካባቢዋ ከሚኖሩት ነዋሪዎች ዉስጥ አስራ ስድስት መረጃ አቀባዮች የተመረጡ ሲሆን፤ የእድሜ ባለጸጋ የሆኑ ሁለቱም ጾታዎች፣ የሀይማኖትና የእምነት መሪዎች፣ አባገዳ፣ ሃደሲቄ፣ የእድር መሪዎችና ወጣት (ፎሌ) የሆኑትም ተካተዋል፡፡

ቃለ መጠይቁ የተካሄደው በአማርኛ ቋንቋ እና በኦሮምኛ ቋንቋ ሲሆን መቅረጸ ድምጸችን ለመረጃ መሰብሰቢነት ተጠቅሚአለሁ፡፡ መረጃው የተሰበሰበባቸው ቦታዎችም ለቅሶ ቤት፣ የቀብር አካባቢና መኖርያ ቤቶች ናቸው፡፡

### 3.3.3. የቡድን ተኮር ውይይት

በዚህ ጥናት አንድ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አካሄጄለሁ፡፡ የቡድን ዉይይት ጥናቱ ትኩረት በሚያደርግበት ጉዳይ ላይ እውቀት አላቸው የሚባሉ ሰዎች ተሰብስበው አጥኚው/ዋ/ ባዘጋጀቻቸው የውይይት መነሻ ጥያቄዎች ላይ ውይይት እንዲያደርጉ የሚያስችል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ በጉዳዩ ላይ ጥልቅና ዝርዝር መረጃ እንዲኖረን ከማገዙም በላይ ለምርምሩ የውሳኔ ሀሳብ ለማፍለቅ ያግዛል፡፡ (ያለው፣2004ዓ.ም፣192)

ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የመረጥኩበት ምክንያት ከላይ በተጠቀሰው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ያልተገኙ መረጃዎች ሲኖሩ እና የተለየ መረጃ እንደማገኝ እርግጠኛ የሆንኩባቸውን ጥያቄዎች ለማዘጋጀት ታስቦ ነው፡፡ በቡድን ማዋቀሩ ወቅት የተለያዩ የማህበረሰቡን አካላት ለማሳተፍ በማሰብ የቡድኑ አባላትም ሶስት የእድሜ ባለፀጎች ከሁለቱም ጾታዎች፣ ሁለት የሀይማኖትና የእምነት መሪዎች፣ ኣንድ አባገዳ፣ ኣንዲት ሃደሲቄ፣ ሁለት የእድር መሪዎችና ኣንድ ወጣት(ፎሌ) ተካትተዋል፡፡ በመሆኑም ዘጠኝ ሰዎችን የያዘ የቡድን ውይይት ያካሄድኩ ሲሆን ዘጠኝ ሰዎችን የመረጥኩበት ምክንያት Kruegor (1994፡79) ተተኳሪ የቡድን ውይይት ለማድረግ አባላቱ ከ8-10 ቢሆኑ የተሻለ እንደሚሆን በገለጹት መሰረት ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች በሚከተለዉ ሁኔታ ተደራጅተዉ እና ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 3.4. የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ስልት

### 3.4.1. የመረጃ አደረጃጀት

ይህ ጥናት አምስት ምዕራፎችን የሚይዝ ሲሆን፡- በመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አብይና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ፣ የመስክ ተሞክሮ፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸዉን የሚካተቱ ሲሆን፤ በምዕራፍ ሁለት ጽንሰ ሀሳባዊ እና ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች እንዲሁም የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ይገለጻሉ፡፡ ምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ እና የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ መንገድን ሲያካትት፤ ምዕራፍ

አራት የመረጃዎች ትንታኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ በምዕራፍ አምስት ደግሞ የጥናቱ ማጠቃለያ የሚቀርብ ይሆናል፡፡ ባጠቃላይ ይህ ጥናት ከምዕራፍ ኣንድ እስከ አምስት ያሉትን የሚያካትት ሲሆን በተጨማሪም አባሪዎች እና ፎቶዎች እንዲሁም ዋቢ መፃሕፍትን አካትቷል፡፡

የተሰበሰበው መረጃ ለትንታኔ ያመች ዘንድ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ በቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞት እና ድህረ ሞት የሚታዩትን ክዋኔዎች መነሻ በማድረግ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚያዙ ቁሶችን ትዕምርት በመግለፅ፣ ስነቃሎችን በመመደብ የተደራጀ ነዉ፡፡ የአመዳደብ ሂደቱም በምዕራፍ ሁለት ላይ የቀረባዉን ንድፈ ሀሳብ መሠረት በማድረግ ነዉ፡፡ የተመረጠዉ ንድፈ ሀሳብ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ ነዉ፡፡ የአዋቂዎች ለቅሶ ስርአት ክዋኔ እና የህፃናት ለቅሶ ስርዓት ክዋኔ፣ አውድ (ባህላዊ አውድና ማህበራዊ አውድ) ለመረጃ አደረጃጀት ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡

### 3.4.2. የመረጃ አተናተን

ከላይ በቀረቡት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መረጃዎችን እያቀናጀሁ ለመጠቀም ሞክሬለሁ፡፡ የአንደኛውን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ክፍተት በሌላኛው በሚሟላት የተሟላ መረጃ ለማግኘት ጥረት ኣድርጌያለሁ፡፡ መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ የጥናቱ ዘዴ ገላጭ እንደመሆኑ መጠን መረጃዎችን በአይነታቸው በመመደብ በዓይነታዊ መረጃ ትንተና (Qualitative Data Analysis) በክዋኔ ተኮር ንድፈ ሁሳብ መርህ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ትንተና

በዚህ ርዕስ ስር የጥናቱ አቢይ ጉዳይ የሆነው "የወሊሶ ኦሮሞ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ትንተና" ከተለያዩ ገፅታዎች አንፃር ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ትንተናው የተካሔደው ከቃለ-መጠይቅ፣ ከምልከታ እና ከተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

## 4.1 የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ምንነት

የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ሞት የሚከሰተው በአደጋ፣ በሰዉ፣ ራስን በማጥፋት፣ በመብረቅ ወይም በበሽታ ምክንያት እንጂ በእርጅና ምክንያት ብቻ አይደለም ብሎ ያምናል፡፡ በእርጅና የመጣዉን በአግባብ የመጣ ነዉ ብሎ ሲቀበል በአደጋና በህመም ምክንት ያለ እድሜ የሚመጣውን ሞት ተገቢ አይደለም  ብሎ ያምናል ፡፡

የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ልዩ ልዩ ገፅታዎች ያሉት እና ማህበረሰቡ ከየትኛውም ባህላዊ ክዋኔዎቹ ይልቅ ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ ይህን ሀሳብ አቶ ገመቹ ታመነ እንደሚከተለው በስፋት ያብራሩታል፡፡ እንደ እኛ ማህበረሰብ እምነት ኣንድ ሰው ሲሞት ሟቹን ወይም የሟቹን ቤተሰብ የሚያውቅ ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል በአካባቢው በመገኘት አልቅሶ የመቅበር ማህበራዊ ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም በተለያየ አካባቢ የሚገኙ የህብረተሰቡ አባላት ሞት መከሰቱን ሊሰሙ የሚችሉባቸውን የተለያዩ አማራጮችን ማለትም በስልክ፣ በደብዳቤ፣ በጥሩምባ ነፊ ማለዳ ላይ በማወጅ፣ የሰማ ሰዉ ላልሰማው በማስተላለፍ እና በመሳሰሉት ዘዴዎች በመጠቀም መልዕክት እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡ መልዕክቱ የደረሰው ላልደረሰው በማዳረስ ቀብሩ እንዲፈፀም የማህበረሰቡ አባላት በቦታው ተገኝተው የሚጠበቅባቸውን ማህበራዊ ግዴታ ይወጣሉ፡፡ በመሆኑም አንዳንድ ሰዎች ተቀባይነት በሌላቸው ምክንያቶች አሳበው ቀብር ላይ ካልተሳተፉና የሟችን ቤተሰብ ቀርበው ካላጽናኑ በመተዳደሪያ ደንባቸዉ እንዲቀጡ ይደረጋል፤ አብዛኛው የህብረተሰብ አባላት ያገኟቸዋል፤ የደስታቸውም ይሁን የኃዘናቸው ተካፋይ ቁጥር ይቀንሳል በማለት ገልጸዋል፡፡ (ቃ.መ.08/08/2013 ዓ.ም፣ ወሊሶ)

ከፍ ሲል በአቶ ገመቹ ታመና የተሰነዘረውን ሀሳብ አቶ ነገሱ አምዲሰ ይህንኑን በተለየ አገላለፅ ያጠናክሩታል፡፡ አቶ ነገሱ አምዲሰ መገለሉ በምን በምን ተግባራዊ እንደሚሆን እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

*ከቤተሰባቸዉ ሰዉ ቢታመምባቸዉ ሀኪም ቤት ለመዉሰድና ለመጠየቅ ፍቃደኛ አይደሉም፤ችግር ደርሶባቸዉ ለድረሱኝ ቢጮሁ የሚደርስላቸዉ አይኖርም፤ ወንድየው እህል ለመዉቃት ወይም እርሻ ለማረስ የሚያቀናጀው በሬ ቢፈልግ ለቅሶ አለመድረሱን የሚያውቁ የአካባቢው ሰዎች አያውሱትም፣ በአካባቢው በሚኖሩ የልማት ስራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆን አይጋበዝም፣. . .ወዘተ፡፡ ሴቷን በተመለከተም ማንም በአረምና በኩትኳቶ አይሳተፍላትም፤ ማንም ሰው ቆሎ አያፋፍቃትም፣ ለቆሎ የሚሆን እርሾ (ገማ) ማንም አይሰጣትም፣ ዕቃ አያውሳትም ብድርም አይሰጣትም፤ ቡና እንድትጠጣ አትጋበዝም፣ ሴቶች ተሰባስበው የሚያከናውኗቸው ማህበራዊ ግዴታዎች በሚኖሩበት ጊዜ ተካፋይ እንድትሆን አይደረግም፣. . .ወዘተ* በሚል ገለጻ አጠናክረዋል፡፡ ( *ቃ.መ* 11/08/2013 *ዓ.ም፣ ማሩ ፋቂ ቀበሌ*)

ከፍ ሲል የጠቀስኳቸው መረጃ አቀባዬ መገለሉ እስከምን ድረስ እንደሚቀጥል እና ይቅር የሚባለው መቼ እንደሆነም ሲገልጹ "አንድ ሰው በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ለቅሶ ሳይደርስ ቀርቶ የደረሰበትን መገለል ይቅር ሊባል የሚችለው በአካባቢው ባሉ ታዋቂ ሽማግሌዎች ፊት ቀርቦ የሰራው ነገር ጥፋት መሆኑንና በስራውም መፀፀቱን በሚገባ አምኖ የሚችን ቤተሰቦች፣ የእድር ዳኞችንና የአካባቢ ሽማግሌዎችን ይቅርታ በመጠየቅ ቅጣትም ተወስኖባቸዉ እንደሆነ በመክፈል አቅሙ በፈቀደ ልክ የሚችን ቤተሰብ በማጽናናት ሲክሱ ብቻ ነው፡፡" በማለት ያስረዳሉ፡፡ (*ቃ.መ*.11/08/013 *ዓ.ም፣ ማሩ ፋቂ ቀበሌ*)

በመሆኑም ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል ለቅሶ መቅረት የሚያስከትለውን ጣጣ በውል ስለሚያውቅ ያለበቂ ምክንያት ከለቅሶ አይቀርም፡፡ ስለሆነም የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ አባላት ከሰርግና ከልዩ ልዩ በዓላት ይበልጥ በለቅሶ ስርዓት ወቅት ከወዳጅ ዘመዶቻቸው ጋር በስፋት ይገናኛሉ፡፡

የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ (በኦሮምኛ "ስርነ ቦእቻ" ይባላል)፡፡ ይህንንም ማህበረሰቡ ከሚያስቀምጣቸው የልዩነት ነጥቦች አንፃር ከፋፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ *እንደ ተተኳሪ ቡድን ተወያዮቹ እምነት ከሌሎቹ የማህበረሰቡ አባላት የተለየ የሚባለው የለቅሶ ስርዓት የሚፈፀመው ጥርስ ሳያበቅሉ በሞት ለሚነጠቁ ህፃናት የሚደረገው የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡ በቀብሩ ሳምንት የጎሳ መሪና ሽማግሌዎች ልጅ የሞታባቸዉ ቤተሰብ ቤት "ቡና ቀላ" እና "ዲባዩ" አዘጋጅተዉ ያለአግባብ የመጣዉን ሞት ዳግም እንዳይመለስ ፀሎታቸውን ለፈጣሪ ያሰማሉ፡፡ ሌላዉ ደግሞ ለጎሳ መሪዎች፣*

*ለአባገዳዎች እና ሃደስቄዎች የሚደረገው የለቅሶ ስርዓት ኣንድ ባለፀጋ ሲሞት በሚደረገው የለቅሶ ስርዓት ላይ የተወሰነ የሚጨምረው ነገር ቢኖረውም አብዛኛው ገፅታው ተመሳሳይ ነው፡፡ እንዲሁም ከፆታ አንፃር ለሴቶቹም ሆነ ለወንዶች የሚደረገው የለቅሶ ስርዓት አብዛኛው ገፅታው ተመሳሳይ ሆኖ በተወሰኑ ክዋኔዎች ላይ ግን ልዩነት ይስተዋልበታል፡፡ ለእያንዳንዱ አካላት የሚደረገው ለቅሶ እንዲደምቅ አሊያም እንዲደበዝዝ ዋንኛውን ሚና የሚጫወተው ሟች ወይም የሟች ቤተሰቦች ያላቸው ኢኮኖሚያዊ አቅም እና ስልጣን መሆኑንም ተወያዮቹ አያይዘው ይጠቅሳሉ፡፡ (የተ.ቡ.ው. 12/08/13 ዓ.ም፣ ወሊሶ)*

በመሆኑም የማህበረሰቡን የለቅሶ ስርዓት የአከዋወን ሂደት "ለህፃናት የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት" እና "ለአዋቂዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት" በሚል ሁለት አበይት ጎራ ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ ሲሆን የአዋቂዎችን የለቅሶ ስርዓት ለመግለፅ በሚደረገው ጥረት ውስጥ *ገመቹ ታመና (ቃ.መ 8/8/2013) እንደገለጹት ኣንድ ሰዉ ራሱን የገደለ እንደሆነ "0fiinuu duutii maaf of huuti"* በቀኑ መሞት ኢያለ ራሱን ለምን ይገላል? የሚል ትርጉም አለዉ፡፡ ነፍስ የፈጣሪ ስጦታ ናት፤ በነፍሱ ለይ ሞትን ያለቀኑ እንዲመጣ በማድረጉ በቅዱስ ቦታዎች ቀብሩ አይደረግም፡፡ የተዝካር ስነ ስርዓትም አይካሄድለትም፡፡ እራስን በራስ መግደል ማለት ይህችን የተቀደሰች ህይወት መጥላትና ከተሰጠው ማህበራዊ ግዴታና ኃላፊነት መሸሽ ስለሆነ ኦሮሞዎች ከሁሉም የከፋና ማህበራዊ ድርጊትን የሚያፋልስ መሆኑን ያምናሉ፡፡

### 4.2. የህጻናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ልጅ ሲወለድ የሚኖረው ደስታ እና ፈንጠዝያ ከፍ ያለ ነው፤ በተለይም የተወለደው ወንድ ልጅ ከሆነ አባት ከማንም በላይ ደስ ይለዋል፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ሀምቢሳ መርጋ "አባት ወንድ ልጅ ሲወለድለት ወራሼን ኣገኘሁ፣ ወንበሬን (በርጩመኮ) የሚወርስና ስሜን (መቃኮ) የሚያስቀጥል ተወለደልኝ እያለ ደስታውን ይገልፃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወንድ የወለደለችለትን ባለቤቱን ከወትሮውም በተለየ ላቅ ያለ እንክብካቤ ያደርግላታል፡፡ የተወለደችው ሴት ከሆነች ደግሞ ይበልጥ የምትደሰተው እናት ነች፡፡ ምክንያቱም የቤት ውስጡን ስራ የምታግዛት ረዳት በማግኘቷ ነው፡፡" በማለት ያስረዳሉ፡፡ (ቃ.መ.04/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ) ፡፡ ይሁን እንጂ እንዲህ በደስታ የተቀበሏቸው የአብራካቸውን ክፋዮች በአንዳች ምክንያት በሞት ከተነጠቁ ሀዘናቸውን የሚገልፁበት መንገድ ከአዋቂዎቹ የተለየ ነው፡፡

የተወለደው ልጅ የሞተው ከሶስት ወር በታች ከሆነ ነፍሱ ባለፈችበት ቅፅበት ቤተሰብ እና ጎረቤት ብቻ እርምን ለማውጣት ያህል ብዙም ከፍ ባላለ ድምፅ አልቅሰው ሟችን ይሰናበታሉ፡፡ የቀብር ስርዓቱም በሌላው የዕድሜ ክልል ውስጥ ካሉ የህብረተሰቡ ክፍሎች ፈፅሞ ይለያል፡፡ ሟች ከቤተሰቡ አልፎ ለጎረቤት መላላክ፣ በግና ፍየሎችን ማሰማራት፣ ከብት መንዳት፣ ቀንበር መሸከም፣. . .ወዘተ በአጠቃላይ ለአቅመ አዳም/ ሔዋን እየደረሰ ባለበት ወቅት ከሆነ የሞተው በቤተሰቡም ሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እጅግ መረር ያለ ለቅሶ ነው እሚሆነው ሲሉ አቶ ምህረቱ ኩመለ ያስረዳሉ፡፡ (ቃ.መ 03/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ)፡፡

ወ/ሮ ስሜነሽ ቶሌራ የቀደመውን ሀሳብ “እናት ልጇ ጥርስ ሳያበቅል ከሞተባት የሚሰማት ሀዘን ከፍተኛ ቢሆንም እንኳ ልጇን የሰጣትን ፈጣሪ አስቀይማ ቀጣይ ልጅ እንዳይከለክላት ስትል የሆዷን በሆዷ ውጣ ትንሽ አልቅሳ ነው ዝም የምትለው፡፡” በማለት ያጠነክሩታል፡፡ (ቃ.መ 04/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ)

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ሁለት የህፃናት ሞት ውስጥ እዚህ ትኩረት ሰጥቶ ማቅረብ የተፈለገው ማህበረሰቡ ጥርስ ሳያበቅል ለሞተ ህፃን የሚያከናውነውን የለቅሶ ስርዓት የተመለከተ ነው፡፡ ይህም እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት ኣስቀድሞ ለ መጠቆም እንደተሞከረው በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ (ከ0 እስከ 1 ዓመት) ያለ አንድ ህፃን ሲሞት በሌሎች የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚሆነው የለቅሶ ስርዓት የተለየ በመሆኑ ነው፡፡ ለአቅመ አዳም/ ሔዋን በመድረስ ላይ እያለ ለሞተ ወጣት የሚደረገውን የለቅሶ ስርዓት በዝርዝር ለማቅረብ ያልተፈለገበት ምክንያት ስርዓቱ በሌሎቹ የዕድሜ ክልሎች ውስጥ ከሚከወነው ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል በመሆኑ ነው፡፡ ይልቁንም የትልልቆቹ ለቅሶ ከወጣቶቹ ለቅሶ የሚጨምረው ያለ በመሆኑ አንዱን በሌላው ውስጥ ማሳየት ይቻላል በሚል እምነት ነው፡፡ ስለሆነም ጥርስ ሳያበቅሉ ለሞቱት ህፃናት ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ የሚከወኑ ስርዓቶችን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 4.2.1. የህጻናት ቅድመ ቀብር ክዋኔ

አንድ ህፃን የእናቱን ጡት እየጠባ፣ ከእናቱ እቅፍ ሳይወርድ በተለየ ምክንያቶች ቢሞት በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ባህል መሰረት ቀብሩ የሚፈፀመው በመኖሪያ ቤት ውስጥ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የተፈለገበትን ምክንያት አቶ ምህረቱ ሲገልፁ “እንደ ማህበረሰቡ እምነት ጥርስ ሳያበቅል የሞተውን ህፃን ልጅ በነጣላ ከገነዙ በኋለ የእንሰት አካል ከሆነዉ “ቀልቻ” በሚባል ዉስጥ በማስቀመጥ በሸክላ ዉስጥ በማድረግ መኖሪያ ቤት ዉስጥ ቦታ ይመረጥና ትንሽ ጉድጓድ ይቆፈርና የቀብር ስርአት ይፈፀማል፡፡

"ቀልቻ" የሚባለዉ ለማቀዝቀዝ የሚጠቀሙበት መሆኑን ይናገራሉ፡፡ አዋቂዎች በሚቀበሩበት ቦታ አይቀበርም፤ ምክንያቱም ከማህበረሰቡ ጋር አለመቀላቀሉን የሚገልፅ ባህላዊ ድርጊት ነዉ፡፡" (ቃ.መ. 04/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ)፡፡

ህፃን ልጃቸውን በሞት የተነጠቁት ሴት ቤተሰቦች እና ጎረቤቶች በጋራ በመሆን አጠር ያለ ለቅሶ በማልቀስ እርማቸውን ያወጣሉ፡፡ ከዚህን በኋላ ከቤተሰቡ ወይም ከጎረቤቱ መካከል በዕድሜ ጠና ያሉ አዛውንቶች ወደ አልቃሾቹ በመጠጋት "ማልቀስ ተገቢ አለመሆኑን፣ ፈጣሪን ማስቀየም እንደሆነ" በመግለፅ ከለቅሶው እንዲታቀቡ ይገስጿቸዋል፡፡ ልጁ የሞተባትንም ሴት ነጠል በማድረግ ካፅናኗት በኋላ መሃል አናቷን ቅቤ በመቀባት "ፈጣሪ ከዚህ የተሻለ፤ የሚያድግ ልጅ" በቅርብ እንደሚሰጣት በማግባባት የለቅሶው ፍፃሜ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

ከዚህ በኋላ የሚከናወነውን ባህላዊ ስነ-ስርዓት የውይይቱ አባላት እንደ ሚከተለው በዝርዝር ይቀርባል፡፡ "ቀልቻ" እንዲሆን መመረጡ የእናት ማህፀን እንዲረጥብ፣ የአባትም የዘር ፍሬ እንዲያፈራ በመመኘት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ከተፈፀሙ በኋላ አስከሬኑ ከቤት ዉስጥ እንዲቀበር ይፈቀዳል፡፡ (የተ.ቡ.ው. 12/08/013 ዓ.ም፣ አባገዳ ተስፋዬ፣ ወሊሶ)፡፡

### 4.2.2. የህጻናት የቀብር ጊዜ ክዋኔ

*"ቀልቻ" ለመገነዝ የሚሆን ነጠላ እንዲሁም እስከሬኑ የሚቀመጥበት ሸክላ ይዘጋጅና በእድሜ ባለፀጋ የሆኑት አባቶች ተጠርተዉ ይገኝላሉ ከዚያ በኋላ ወጣት ወንዶች ቤት ዉስጥ ቦታዉ ተነግሯቸዉ በተነገራቸዉ መሰረት ጉድጓድ እንድቆፍሩ ይደረጋል፡፡ ጉድጓዱ ከተቆፈረ በኋላ የቀብር ስነ ስርአቱን ለመፈጸም እናት እና ሌሎች ሴቶች ሰብሰብ ብለው እንደቀደመው ሁሉ ዝቅ ባለ ድምጽ እያለቀሱ ለመጨረሻ ጊዜ ሟችን ይሰናበታሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የሟች እናትም ሆነች ሌሎች ሴቶች እንዲሁም ህፃናት ሬሳውን ተከትለው እንዲሄዱ የማይፈቀድላቸው በመሆኑ በቀብሩ ቦታ እንዳይገኙ ይደረጋል፡፡ ይህም የሚሆነው እነዚህ አካላት እንደ ወንዶቹ ችግርን መጋፈጥ ሊከብዳቸው ይችላል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ የሟችን ቀብር በሚያዩበት ጊዜ አምርረው ያለቅሳሉ ተብሎ ስለምታመን ነዉ፡፡ በማልቀሰቸዉም ደግሞ ፈጣሪን አስቀይመው የሟች እናት ሌላ ልጅ እንዳትወልድ ፈጣሪ ይጨክንባት ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን መሆኑን አቶ ዳበሳ (ቃ.መ. 03/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ) ያስረዳሉ፡፡*

**በልጆች የለቅሶ ስርዓት ላይ የሚደረደሩ የሙሾ ግጥሞች**

| በኦሮምኛ | በአማርኛ |
| --- | --- |
| Ya kichuukoo | የእኔ ጨቅላ |
| Hinkaane sitti dukkanaa'e | አልኖርክም ጨለመብህ |
| Duudaa waan itti bahu hinbeekne | ምን እንደሚሆን የማይታወቅ ልጅ |
| Haadhaf abbaakeef dhukkuba taatekaa | ለእናትህ/ሽ እና አባትህ በሽታ ሆንሽባቸው |
| Mucaa lataa/ttuu | ታደጊ ልጅ |
| Karaa deebi'e/te | ከመንገድ ነው የተቀጨኸው |
| Mucaa urgeessaa hincabsine | አምስት ወይም አራት ቀን የልሞላ ልጅ |
| Mucaa manaa bahu | ከቤት በመዉጣት ላይ ያለ ልጅ |
| Guddataa/ttuu | ታደጊ |
| Barateera/baratteerti | ተምሯል/ራለች |
| Guyyaa du'aa hin oolani | ከሞት ቀን አያመልጡም |
| Nama keessaa deebi'e yaa biyyaa | ወዳጆቼ ከሰው ነው የተመለሰው |
| Ilmoo tokko dhabne yaa biyyaa | አንድ ልጅ አጣን |
| Yaa mushirraakoo | የኔ ሙሽራ |
| Yaa dorrobaakoo | የኔ እንቡጥ |
| Yaa jibichakoo | የኔ ወንድ ልጅ |
| Yaa jibichakoo | የኔ ወንድ ልጅ |
| Kun siif hinmalu yaa dorrobaakoo(2) | ይሄ አይመጥንህም የኔ አበባ (2) |

### 4.2.3. ድህረ ቀብር ክዋኔ

*ወ/ሮ ሸዋዬ እንደሚያስረዱት "ከቀብር በኋላ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው እናትየዋን አፅናንቶ ለቀጣይ ዓላማ ዝግጁ እንድትሆን ማስቻል ነው፡፡ ይህ ይሆን ዘንድም ዋንኛው ኃላፊነት የሚጣለው በአካባቢው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ሌላ ልጅ መውለድ የቻሉ ሴቶች ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሴቶች እንዴት ባለ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ሌላ ልጅ መውለድ እንደቻሉ በመንገር የሟች እናት ቀጣይ ልጅ ለመውለድ እራሷን ዝግጁ*

እንድታደርግ ያነሳሷታል፡፡" ሌላው ልጇ በሞት በሳምንቱ "ቡና ቀላ" ይዘጋጃል፤ የኦሮሞ ጠላ "ፈርሶ ኦሮሞ" ይጠመቃል፤ "ዳባዩ" ይዘጋጀል፤ የጎሳ መሪና ሽመግሌዎች ተሰብስበዉ ሰዎቹን እንድህ ብለዉ ይመርቃሉ "እግዚአብሄር ልጅ ሰጥቶ ማህጸናችሁን ይፈዉስ (ዋቀዮ ኬኔ ገራ ኪሰን ሃፈይሱ)" በማለት ይመርቃሉ፡፡ ፈጣሪም ፀሎታቸዉን ይሰማል ብለዉ ይገልፃሉ፡፡ (ቃ.መ. 13/08/013 ዓ.ም፣ አብ ኮጂ ቀበሌ እና ቃ.መ. 13/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ)

### 4.3. ለአዋቂዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ባህል መሰረት በዕድሜ ገፋ ላሉ ሰዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት ልዩነት የሚኖረው ሟች ወይም የሟች ቤተሰቦች ባላቸው ኢኮኖሚያዊ አቅም፣ በማህበረሰቡ ዘንድ እንዳላቸው ተቀባይነት እና ሟች የባህላዊ ስልጣን ባለቤት የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ማለት ሟች በህይዋት ዘመኑ ያከማቸው ሀብትና ንብረት ያለው ከሆነ የለቅሶ ስርዓቱ የዚያኑ ያህል በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ ያልፋል፡፡ ነገር ግን የሟች የኢኮኖሚ አቅም ዝቅተኛ ከሆነ እምብዛም የደመቀ ለቅሶ እና ሰፋ ያለ ስርዓት ላይኖር ይችላል፡፡ በሌላ አንፃርም ሟች በህይወት ዘመኑ ከማህበረሰቡ ጋር የነበረው መስተጋብር ዝቅተኛ ከሆነ በዚያው መጠን የለቅሶ ስርዓቱ ሊደበዝዝ ይችላል፡፡

በቀደመው ምዕራፍ እንደተጠቀሰው የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የራሱ በሆነ የመሰተዳድር ሥርዓት ማለትም "በገዳ" ስርአት የሚመራ ነበር፡፡ በዚህ "የገዳ" ስርዓት ውስጥ በተዋረድ ካሉ የባህላዊ ስልጣን ባለቤቶች መካከል አንዱ ቢሞት የለቅሶ ስርዓቱ ስልጣን ከሌላቸዉ የህብረተሰብ ክፍል የለቅሶ ስርዓት የሚለይበት የራሱ የሆነ ገፅታ ያለው ቢሆንም ያን ያህል ጉልህ ነው ተብሎ የሚገለፅ ልዩነት አይስተዋልም፡፡ (ቃ.መ. አቶ ፋርገሰ ሁንዴ 03/08/ 013 እና ወ/ሮ ሙሉ 04/08/013፣ ወሊሶ)

የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የአዋቂዎች የለቅሶ ስርዓት የጋራ የሆኑ ገፅታዎችን በስፋት በማንሳት ልዩነት የሚስተዋልባቸውን ነጥቦች በመጠቆም እንደሚከተለው ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው ምን እንደሚመስል ለማሳየት ይሞከራል፡፡ ለአቀራረብ ያመች ዘንድም በቅድመ ፣ ጊዜ ሞት እና ድህረ ቀብር ወቅት የሚታዩት ልዩ ልዩ ገፅታዎች ተዘርዝረው ይተነተናሉ፡፡

#### 4.3.1. ቅድመ ሞት ክዋኔ

በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ባህል መሰረት አንድ ሰው በፀና ከታመመ መታመሙን የሰሙ የአካባቢው ሰዎች ሁሉ ወደ ታማሚው ቤት በመቅረብ "እግዜር ይምረው ዘንድ"

መልካም ምኞታቸውን መግለፅ ቀዳሚ ተግባራቸው ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ዳበሳ ከፈኒ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

አንድ ሰው በጣም ታሞ ከቤት መውጣት ያቃተው መሆኑ ሲታወቅ በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች በቡድንም ሆነ በተናጠል ወደ ሰውየው ቤት በመቅረብ ሰውየውን ያበረታቱታል፣ ፈጣሪ እንዲምረውም ይፀልዩለታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የታማሚው የቅርብ ዘመድ እና የጎሳው አባላት ለበሽተኛው ይስማማል ብለው ያሰቡትን ምግብ እና መጠጥ በመያዝ ተመላልሰዉ መጠየቅ በኛ ባህል እንደግዴታም የሚቆጠር ነው፡፡ (ቃ.መ. 09/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ)

በሽተኛውን እየተመላለሱ ከሚጠይቁት ሰዎች መካከል ከዘመናዊው ህክምና በተጨማሪ ለህመሙ ይበጃል የሚሉት ባህላዊ መድኃኒት የሚያውቁ ከሆነ ወይም ከሚያውቅ ሰው በመጠየቅ አምጥተው በሽተኛው እንዲፈወስ የማድረጉም ጥረት በሰፊው የሚከናወን መሆኑንም የቀደሙት መረጃ አቀባዬ ይጠቅሳሉ፡፡

ህመምተኛው ያለበት ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን እስጊ ደረጃ ላይ መድረሱን በእድሜ ከፍ ያሉ የታማሚው ዘመዶች እና የአካባቢው ሽማግሌዎች እንደተረዱ በዚህ ወቅት የሚፈፀመውን ሌላኛውን ተግባር አቶ ደበሰ ከፈኒ ሲያስረዱ "በሽተኛው አንደበቱ ከመዘጋቱ በፊት ልጆች ከቅርብ ዘመዶቹ ጋር ተሳባስበዉ በሽማግሌዎች አማካይነት ማር ተዘጋጅቶ ልጆቹ እንድመረቁ ይደራጋል፡፡ የሰዉ ንብረት በእጁ ካለ ይናገረል፤ የሱም ከሰዉ ላይ ካለ እንደዚያዉ ይናገራል፡፡ ቂም በሆዱ ካለ ይቅር እንዲባበሉ ይደራጋል፡፡ ሀብት እና ንብረቱ እንዴት እንዲሆንለት እንደሚፈልግ ለማወቅ በቤተሰቡ አባላት የጋራ ስምምነት ለተመረጡ ሦስት ሽማግሌዎች እንዲናዘዝ ይደረጋል፡፡ ዛሬ ዛሬ ኑዛዜውን መፃፍ የሚችል አንድ ሰው ከሽማግሌዎቹ ጋር አብሮ እንዲሆን የሚደረግ ቢሆንም ቀደም ባለው ጊዜ ግን ሽማግሌዎቹ የሰሙትን በቃል እንዲያስተላልፉ ነበር የሚደረገው፡፡" (ቃ.መ. 09/08/013 ዓ.ም) በማለት ያብራራሉ፡፡

የኑዛዜው ተግባር ከተፈፀመ በኋላ ታማሚው ያለበት ሁኔታ ከቀድሞው የባሰ መሆኑ የበሽተኛውን ሁኔታ በንቃት በሚከታተሉት ሽማግሌዎች ሲረጋገጥ በአካባቢው ያሉ የተወሰኑ ሰዎች ተሰባስበው ነፍስ ያወቁ ቤተሰቦቹን እንዳለ በማስጠራት ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ በየተራ አይኑን አይተው እንዲሰናበቱ እና በድሎኛል የሚሉት ነገር ካለም ይቅር እንዲሉት ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ ባያደርጉም ሁሉም ስንብቱን በለቅሶ ነው የሚቋጩት (ምልከታ12/08/013 ዓ.ም፣ በልበላ ቀበሌ)፡፡

አቶ ደበሰ ከፈኒ ቤተሰቦቹ ታማሚውን ከተሰናበቱ በኋላ ስለሚፈፀሙ ነገሮች እንደሚከተለው በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡

በሽተኛውን ለመንከባከብ የመመገቢያ ዕቃም ሆነ ምግብ አዘጋጅቶ የሚያቀርቡ አካላት ከቤተሰብ፣ ከዘመድና ከጎረቤት በታማሚዉ ፍላጎት ላይ በመመርኮዝ ከበሽተኛው ጋር እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ለታማሚው ካላቸው መውደድ የተነሳ በራሳቸው ፍላጎት የሚመደቡ ሴቶች እና ጠንከር ያሉ ወንዶች እንዲሁም የግንዘት ስርዓቱን መፈፀም የሚችሉ የታማሚው ጎሳ አባል የሆኑ ሽማግሌዎች ናቸዉ፡፡ ግብዓተ መሬት ከተፈፀመ በኋላ ቤቱ ዉስጥ የተሰሩ ነገሮች ለምሳሌ ሊጥ ካለ ይደፋል እንጂ አይጋገርም፤ ወጥ ጠላና ሌሎች ነገሮችም ለምግብነት የተዘጋጁ ሁሉ ይጣላሉ እንጂ ማንም ሰዉ አይጠቀምባቸውም፡፡ ምክንያቱም ከሟቹ ጋር ልጠቀሙበት የተዘገጀዉን ምግብና መጠጥ ለብቻቸዉ መጠቀም ምቾት የሚነሳና የሚያስጸይፍ ተግባር ተደርጎ ስለምታመን ነዉ (ቃ.መ. 04/08/013 ዓ.ም፣ወሊሶ)፡፡

በዚህ ወቅት ከሚከወኑ ሌሎች አበይት ጉዳዮች መካከል የሬሳ ሳጥን “ሳጥኒ ሬንፋ” ዝግጅት አንዱ ነው፡፡ በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ባህል መሰረት የሬሳ ሳጥን የሚዘጋጀው አራት ጣውላዎችን በሚስማር በማገናኘት ነዉ፡፡ ለዚሁ ዓላማ ሲባል የእድር አባላት እያንዳንዱ አባወራ ጣዉላ 50ሰ.ሜ ወይም 40ሰ.ሜ በእድር አባላት በተወሰነ መልኩ ይሰበሰባል፡፡ አንድ ሰዉ ቤተሰቡ ከሞተበት ከዚያዉ እድር ይወስድና በነፍስ ወከፍ ተጠቅሞበት ለቅሶዉ ካለፈ በኋለ የወሰደዉን ያህል ለእድሩ ይመልሳል፡፡ የወሰደ ጣውላም በባለሞያ ለአስከሬኑ የሚሆነዉ ተለክቶ ይሰራል፡፡ አሁን አሁን ግን የተሰራዉን ከእድር ብር ተመድቦ ሲገዙ ይታያል፡፡ አንድ የማህበረሰቡ አባል የጤንነቱ ሁኔታ በእጅጉ አስጊ ደረጃ ላይ ከደረሰ በቤተሰቡ ወይም በአካባቢው ሰዎች አስተባባሪነት ባለሙያ ተፈልጎ ለሰውየው ቁመት የሚበቃውን ያህል ጣዉላዉን ቆርጦ በመለየት በባህላዊ መንገድም በአግባቡ ተጠርቦ ይዘጋጃል፡፡



ፎቶ፡5 የወሊሶ ኦሮሞ ጎሣ የሬሳ ሳጥን

## 4.3.2. ጊዜ ሞት ክዋኔ

የታማሚው ነፍስ ማለፏ ከጎን ባሉ የዕድሜ ባለፀጎች እንደተረጋገጠ ወዲያውኑ የሟችን ታላቅ ወንድ ልጅ በማስጠራት (ወንድ ልጅ የሌላቸው ከሆነ ከቤተሰቡ መካከል የቅርብ ዘመድ የሆነ ታላቅ ወንድ ሊሆን ይችላል) ስለ ሁኔታው አስረድተው አስከሬኑን እንዲያጥብ ያደርጉታል፡፡ ከዚያም ሽማግሌዎቹ ወዲያውኑ የግንዘቱን ተግባር ይፈፅማሉ፡፡ እስከሬኑን ቀጥ አድርጎ በጀርባው በማስተኛት አይኑ እንዲሸፈን፣ ጥርሶቹ እንዲከደኑ፣ ከንፈሩ እንዲገጠም ካደረጉ በኋላ ሁለት እጆቹ ብልቱን እንዲሸፍኑ ኣድርገው የእግሮቹን አውራ ጣቶች እና ጉልበትን አጣምረው በክር ያስራሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ኣድርገው ሬሳውን ከመከፈናቸው በፊት በዕድሜ ፀና ያሉ የሟች ቤተሰቦችን ወደ ሬሳ ቤቱ እንዲቀርቡ በማድረግ ሬሳውን ወደ ሳሎን አውጥተው መሞቱን እንዲያረጋግጡ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ድምፅ ጎላ ብሎ እንዳይወጣ የሚከለከል ቢሆንም የሚኖረው ለቅሶ መሪር ነው፡፡ በመቀጠልም ለዚሁ ተግባር

በተዘጋጀ ትልቅ ጋቢ እስከሬኑን ከፍነው ኣሁንም ልምድ ያለዉ ሰዉ ከእንሰት "ተምቦሽላ" የሚሰራ አስከሬኑ የሚቆይበት በአሊጋ መልክ ይሰራል፡፡



ፎቶ፡6 እስከሬን የሚቀመጥበት "ተምቦሽላ"

ይህም እስከሬኑ መጥፎ ሽታ እንዳይኖረዉ ያደርጋል በሳጥን ውስጥ ሳይገበ በፊት አስከሬኑን በጤና አዳምና በዉሃ ሶስት ጊዜ ያጥባሉ፣ ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ሶስት ጊዜ ማጠብ የስላሴዎች ተምሳሌት ነዉ፡፡ "ጤና አዳም ደግሞ ከስሙም መረዳት እንደሚቻለዉ ለጤና ጥሩ መሆኑና ሞት በቤተሰብ ላይ ያለአግባብ እንዳይመጣ ለማድረግ ነዉ" ይላሉ አባ ገደ ተስፋዬ ቱጂ (ቃ.መ.10/08/013) ፡፡

ሬሳ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ሽማግሌዎች እና አስተናጋጆች የሳጥኑን ክዳን ዙሪያ በምስማር በአግባቡ የመምታት ስራ ይሰራሉ፡፡ በመጨረሻም በሬሳ ክፍል ውስጥ እሳት ዳር በእንጨት ፍርግርግ ተሰርቶ በተዘጋጀ የሬሳ ሳጥን ማስቀመጫ ላይ ሬሳውን በማኖር ጥሩ መዓዛ ያላቸው የጭስ እንጨቶች በብዛት እንዲጨሱ ይደረጋል፡፡ መልካም ጠረን አላቸው ተብለው ከሚመረጡት መካከል ጤናዳም፣ የነጭ ባህር ዛፍ ቅጠል፣ አሪቲ፣ ኮሰረት እና የወይራ እንጨት ዋንኞቹ ናቸው፡፡ ጤና አዳም እና የነጭ ባህር ዛፍ ቅጠል ሬሳውን ለማጠብም ይገለገሉባቸዋል፡፡ ይህ ተግባር ጥርስ ካላበቀሉ ህፃናት ውጭ ላሉት የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ተግባራዊ የሚሆን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሟች ሴት ከሆነች የእጥበቱን ስራ የምታከናውነው ቅርብ ዘመድ የሆነች ከሟቿ ጋር ጥሩ ፍቅር ያላት ሴት ነች፤ ወንድ ከሆነም ከሟቹ ጋር ጥሩ የፍቅር ህይወትና የስጋ ዝምድና ያለው ነዉ፡፡ (የተ.ቡ. ው. 12/08/013 ዓ.ም፣ወሊሶ)

### 4.3.3. ቅድመ ቀብር ክዋኔ

እንደ ተተኳሪ ቡድን ተወያዮቹ አገላለፅ በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ወቅት ሰፊውን ድርሻ የሚይዙት ከቀብር በፊት የሚፈፀሙ ዝግጅቶች ናቸው፡፡ ይህ ዝግጅት ሟች አንዳች ማህበራዊ ስልጣን ወይም ኢኮኖሚያዊ አቅም ያለው ከሆነ ደግሞ ከሌላው ይልቅ ሰፋ ይላል፡፡ ከቀብር በፊት ከሚከናወኑ ዝግጅቶች መካከል የምግብ እና መጠጥ ዝግጅት፣ ለቅሶ ነጋሪዎችን ማሰናዳት፣ በሟች ማሳ መፈፀም ያለባቸውን ተግባራት ማከናወን፣ ለእርድ የሚሆኑ ከብቶች ማዘጋጀት፣ የቀብር መሄጃውን መንገድ ማፅዳት እና የቀብሩን ቦታና ቤት ማዘጋጀት፣ የመኖሪያ ቤቱን አካባቢ ማፅዳት እና ዳስ መስራት፣ በቀብሩ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ አልባሳትን እና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት. . .ወዘተ ዋናውን የዝግጅት ስፍራ ይይዛሉ (የተ.ቡ. ው. 12/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ)፡፡

**ኤኬሮ "ኢልሞ ኤኬሮ"**

> *በወሊሶ ኦሮሞ ብቻ የሚታወቅ የኤኬሮ ልጅ የሚባለዉ ኣንድ ሰዉ ትዳር መስርቶ በሚኖርበት ዘመን ልጅ ከሌለዉ ያ ሰዉ ሲሞት ከቅርብ ዘመድ ማለት ከወንድም ከእህት ካልሆነ ከቅርብ ዘመድ ወንድ ልጅ ይፈለግና ቤተሰቦቹ ከተስማሙበት ከሰዉዬዉ አስከሬን አጠገብ ያስቀምጣሉ፡፡ የጎሳ መሪ ይመጣል፤ "ጉለ" የሚባል በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ በጣም ቦታ ያለዉ በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ የሚባል ችግር ሲፈጠር መፍትሔ የሚሰጠዉ ይመጣል፤ ባለቤቷ የሞተባት ሴት ወንድሞቿ ይመጣሉ፡፡ ጦር እና አለንጋ ይመጣል፡፡ በዚህ*

*መልኩ ያ ልጅ የሚቹን ስም ይዞ እንዲቀር ሚስቱንም እንደ ልጁ ሆኖ በህይወት ዘመኗ ያገለግለታል፡፡ እሷ ከሞተች የንብረቱ ወራሽ እሱ ነዉ፡፡ በዚህ ስርዓት ላይ የሚያዙ ቁሶች ራሳቸዉን የቻሉ ትዕምርት አላቸዉ፡፡ ልጁን የወለዱ ሰዎች የራሳቸዉ ኣድርገዉ እንዳያስቡ የሚያደርግ ትርጉም አለዉ፡፡ ለምሳሌ አለንጋ ብንወስድ ዉሳኔ የሚተላለፍበት ቁስ ነዉ፡፡ ጦር ደግሞ ከዉሳኔ ወደኋላ የተመለሰ በማህበረሰቡ ዘንድ ጦሩ ወግቶ እንደሚገድል ይታመናል፡፡ አቶ ነገሱ አምዲሳ የወሊሶ ባህልና ቱርዝም የቅርስ ጥበቃ ባለሙያ (ቃ.መ.06/08/013 ወሊሶ)*




ፎቶ፡7 በስርአቱ ላይ የሚያዙ ቁሶች

**ሰንጠረዥ ሁለት፡ ቁሳዊ ባህሎቹ መቼና የት የት እንደሚያገለግሉ**

| ተ.ቁ | ቁሳዊ ባህል | መቼ | ቁሶቹ የሚያገለግሉበት ቦታ እና የሚታየዉ ነገር |
|---|---|---|---|
| 1 | አለንጋ | ሁል ጊዜ | ለቅሶ ጊዜ እና "ኤኬሮ ልጅ" |
| 2 | ጦር | አራዊቶችን ለማደንና በጦርነት ጊዜ | የ "ኤኬሮ ልጅ" ጊዜ |
| 3 | ፈረስ | ሁል ጊዜ | ጊዜ ቀብር |
| 4 | ጋሻ | በፈረስ ስጫወቱ፣ በጦርነት ጊዜ | ጊዜ ቀብር |
| 5 | ባህላዊ ምግብና መጠጥ | ሁል ጊዜ | ከቀብር በኋለ እና በሳምንቱ |
| 6 | ባህላዊ ቤት "ዳስ" | በለቅሶ ጊዜ | ከጊዜ ሞት እስከ ድህረ ቀብር |
| 7 | የፈረስ እቃዎች | ሁል ጊዜ | ጊዜ ቀብር |

**ፈረስ ቀሚስን በማልበስ "ፈርዶ ቀሚሲ"**

*ይህ ባህል በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ በጣም የሚታወቅ እና በአሁኑ ጊዜ አልፎ አልፎ እንጂ ብዙ ቦታ የማይገኝ መሆኑን ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡ ብዙ ቦታ የማይገኝበት ምክንያትም ትዉልድ ለማንነቱ ቦታ እየሰጠ ኣለመሆኑን ይናገራሉ፡፡ ይህ ፈረስ እንደ ወሊሶ ኦሮሞ ባህል በጣም ታዋቂና ዝነኛ ሰዉ ሲሞት ብቻ ይዘጋጅለታል፡፡ ሰዉየዉ በህይዎት ዘመኑ በኖረበት ማህበረሰብ ትልቅ ዉለታ የዋለለት ስለሆነ ዉለታዉም ኣንድ ሰዉ ቀሚስ የለበሰዉን ፈረስ ጎትቶ ከፊት ለፊት በመሄድ ሌሎቹም እሱን ተከትለዉ በሰልፍ ዉለታዉን እያሰቡ ያለቅሱለታል፣ ስሙንም እያነሳሱ ይነገርለታልም ይላሉ የወንጪ ወረደ ባህልና ቱርዝም ቢሮ በለሞያ አቶ ገመቹ ታመነ (ቃ.መ.08/08/013.ወንጪ ወረዳ)፡፡*



ፎቶ፡8 ፈረስ በቀሚስ “ፈርደ ቀሚሲ”

## የምግብ እና መጠጥ ዝግጅት

የወሊሶ ማህበረሰብ ባህላዊ ምግብ ብዙ ናቸዉ፡፡ በለቅሶ ለይ የሚቀርቡ፡ ቀይ ጤፍ እንጀራ፡ ነጭ ጤፍ እና ቆጮ ሲሆን ጠጅ ወይም ጠላ (ፈርሶ ኦሮሞ) ደግሞ በማህበረሰቡ በግንባር ቀደምትነት የሚመረጡ ባህላዊ መጠጦች ናቸው፡፡ ቆጮ በማህበረሰቡ ዘንድ በበዓላት ቀን አሊያም ለየት ባሉ ዝግጅቶች ላይ ብቻ ለምግብነት የሚውል የምግብ አይነት ሳይሆን ሁሌም ከሌሎች ምግቦች ጋር ለምግብነት የሚውል ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግን በከተሞች አልፎ አልፎም ለከተሞች አቅራቢያ በሆኑ የገጠር ክፍሎችም ዘንድ ቆጮ እንደ አማራጭ በማዕዱ ላይ ይቀርባል፡፡

በቀብሩ ዕለት ከተለያዩ አካባቢዎች ለሚመጡ ለቀስተኞች ከቀብር በኋላ ከሚቀርቡ ባህላዊ መጠጦች መካከል ለዝግጅት ከወር በላይ የሚፈልገው ጠጅ የሚባል ሲሆን በዕውቅ ባለሙያ ከወር እስከ ሦስት ወር ድረስ እንዲቆይ ተደርጎ የሚዘጋጀው ዋነኛውን ስፍራ ይይዛል፡፡ በዋናነት ጠጅ የሚዘጋጀው ከማር እና ከጌሾ ሲሆን ዝግጅቱ የሚካሔደው በዋናነት በሟች ቤት ውስጥ ሆኖ በአካባቢው ያሉ በጠጅ መጥመቅ ስራቸው የተካኑ ሴቶች አስተባባሪነት ነው፡፡ ጠጁ ተጥሎ አንድ ወር ከቆየ በኋለ ዳግም በማርና በውኃ በመበጥበጥ ለሌሎች በርካታ ቀናት የሚቆይበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ይህ ሲሆን ጠጁ ከአስካሪነቱ ይልቅ ለሰውነት የሚሰጠው ጠቀሜታ ይጨምራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከጠጅ በተጨማሪ ከቀይ ጤፍ የሚዘጋጀው “ፈርሶ ኦሮሞ”ም ከቀብር በኋላ በአማራጭነት የሚቀርብ በመሆኑ በዚሁ ወቅት የሚዘጋጅ ነው፡፡

ሌላው በቀብር ዕለት ለምግብነት ለሚቀርበው ቆሎ፣ ንፍሮ እና ቡና ዝግጅት ማሰናዳት በቅድመ ቀብር ወቅት ከሚፈፀሙ የምግብ እና የመጠጥ ዝግጅቶች መካከል ተጠቃሾች ናቸው (ቃ.መ. ወ/ሮ ቦገሌ ባይሳ፣ 10/08/013 ዓ.ም፣ በልበላ ቀበሌ እና ወ/ሮ ደራሬ አበራ፣ 10/08/013 ዓ.ም፣ ወንጪ)፡፡

ለቅሶ ነጋሪዎችን ማሰናዳት በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ባህል መሰረት የማህበረሰቡ አባል ሆኖ ለቅሶ አለመድረስ ከህብረተሰቡ ጋር ከሚያቃቅሩ ጉዳዮች መካከል በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ በመሆኑም ሞት በተከሰተበት አካባቢ ያሉት አዛውንቶች ከቤተሰቡ አባላት ጋር በመሰብሰብ የቀብሩን ቀን እና በቀብሩ ዕለት በዋናነት እንዲገኙ የሚፈልጓቸውን ሰዎች ዝርዝር በጋራ ተነጋግረው ይወስናሉ፡፡ ቀደም ባለው የማህበረሰቡ እምነት መሰረት የቀብር ቀን ሰኞ እና ረቡዕ እንዲውል አይደረግም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ቀናት እህል ቢዘራባቸው እንኳ አያበቅሉም፤ ደረቅ ናቸው ተብሎ የሚታመን ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍ ያለ ድርሻ የሚሰጣቸው የህብረተሰቡ አካላት ሲሞቱ የማህበረሰቡ አባላት ወደሚኖሩባቸው የተለያዩ አካባቢዎች በሙሉ መልዕክተኞችን በእግር፣ በፈረስ እና በመኪና በመላክ የቀብሩን ቀን እና ቦታ በአግባቡ ተናግረው እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን በአብዛኞቹ አካባቢዎች የተንቀሳቃሽ ስልክ አገልግሎት በስፋት ያለ በመሆኑ ሁሉም ለሚያውቀው ደውሎ እንዲናገር በማድረግ ነው የመረጃ ልውውጡ የሚካሔደው፡፡ በመሆኑም ትራንስፖርት ባልተስፋፋበት ወቅት ከወሊሶ - አዲስ አበባ ድረስ በእግር ተጉዘው እንዲናገሩ ይደረግ የነበረው አድካሚ እና ጊዜ ፈጅ የነበረው አሰራር ተሻሽሏል፡፡

ለመልዕክተኛነት የሚመረጡት ሰዎች ጎልማሳ ሆነው የጤንነታቸው ሁኔታ “መልዕክቱን ሳያደርሱ ከመንገድ ሊቀሩ ይችላሉ” የሚል ስጋት ውስጥ የማይከቱ እንደይሆኑ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሚላኩበትን አካባቢ እና ሰው የሚያውቁ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ ይህ ምርጫ የቤተሰቡ አባላት የሆኑ ጎልማሶችን አያካትትም፡፡ ምክንያቱም እነሱ በኃዘን ተጎድተዋል በሚል ነው፡፡ በዚህ መልክ ተመልምለው የተላኩት መልዕክተኞች ወደተላኩበት ሰው ቤት እንደደረሱ በአካባቢው ከሚገኙ ሰዎች ቤቱ በእርግጥ የተላኩበት ሰው መሆኑን፤ አለመቀየሩን በማጣራት በቀስታ ወደ ውስጥ ዘልቀው ሟቹ የሚስት ዘመድ ከሆነ ለባል፣ የባል ዘመድ ከሆነ ደግሞ ለሚስት ስለሁኔታው ቀድመው በማስረዳት ለሟች ወገን በማስተዛዘን እና በቀስታ በመንገር ይላቀሳሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ትንሽ ዕረፍት እንዳደረጉ የቀብሩን ቀን እና ቦታ በጥንቃቄ ነግረው ሌሎች በአካባቢው ለሚገኙ የማህበረሰቡ አባላት ንገሩ መባላቸውን በማሳሰብ የሄዱበት መንገድ ሩቅ ከሆነ እንደ ሁኔታው አንድም ሆነ ሁለት ቀን አርፈው ይመለሳሉ፡፡ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ታልፎ መልዕክቱ ከደረሰው በኋላ ብዙም አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት በቀብሩ ዕለት በማይገኝ የማህበረሰቡ አባል ላይ የሚኖረው መገለል ከፍተኛ ነው (ቃ.መ. አቶ ከበደ ቀልቤሣ፣ 14/08/013 ዓ.ም በልበላ ቀበሌ እና አቶ ሽፈራ አሰፌ 04/08/013 ዓ.ም፣ ወንጪ)፡፡

### በሟች ማሳ መፈፀም ያለባቸውን ተግባራት ማከናወን

የሰው ልጅ ታሞ አልጋ የሚይዝበት ብሎም የሚሞትበት ቀን በውል የማይታወቅ በመሆኑ አንድ ሰው በሚሞትበት ወቅት በጅምር የሚቀሩ ስራዎች፣ ያልተፈፀሙ ዕቅዶች፣ ያልተከፈሉ ዕዳዎች ወይም ያልተመለሱ ብድሮች ወይም ተጀምሮ የላለቀ የቅርሳቅርስ ስራ ይኖራሉ፡፡ የወሊሶ ማህበረሰብ በዋናነት የሚተዳደረው በግብርና ስራ ላይ እንደመሆኑ መጠን በአካባቢው የሚሰሩ ስራዎች ወቅትን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ጊዜው የእርሻ ሆኖ ሳለ በተለያዩ ምክንያቶች የሟች ማሳ ጦሙን ያደረ ከሆነ በአካባቢው የሚገኙ የጎሳው አባላት ተሰባስበው በመመካከር የሟችን ማሳ መንጥረው፣ አርሰው፣ ጎልጉለው እና ዘርተው በማሰናዳት ሟች ወገን ያለው መሆኑን ማስመስከር የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሟችን ማሳዎች ማጠር፣ ከብቶቹን መንከባከብ እና ቆጮውን መኮትኮትም "ወርቂ ድድቂ” በእነዚሁ አካላት በተጓዳኝ ይፈፀማል፡፡

ከዚህ ጋር በተጓዳኝ በሌሎች አካላትም ጭምር የሚከወነው ሌላው ተግባር ለማገዶ የሚሆን እንጨት ማሰናዳት ነው፡፡ ሞት በአካባቢው መከሰቱን የሰሙ በአካባቢው

የሚገኙ ሴቶች በሙሉ በቀብሩ ቀን በነፍስ ወከፍ ኣንዳንድ እስር እንጨት በመያዝ በሟች ቤት እያመጡ መከመር የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ ግን ማሳውን በማሰናዳት ላይ የሚገኙት አካላት በማሳው ውስጥ የሚገኙ ደረቅ ዛፎችን በመጣል በህብረት ፈልጠው በማሳ ያለው ስራ እስኪጠናቀቅ ወደ ሟች ቤት በማጓዝ የማገዶ እንጨት ችግርን ይቀርፋሉ፡፡ በወሊሶ ማህበረሰብ ባህል ለወትሮውም ቢሆን የማገዶ እንጨት የማቅረብ ግዴታ የተጣለው ሴቷ ላይ መሆኑን አቶ ሽፈራ አሰፋ (ቃ.መ. 01/08/013 ዓ.ም፣ ማሩ ፋቄ ቀበሌ) በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡

## ለእርድ ከብቶች ማዘጋጀት

የቀብሩ ዕለት ከተለያዩ አካባቢዎች ተሰባስበው የመጡት ለቀስተኞች የተሻለ ነገር ተመግበው እንዲሄዱ ማድረግ በወሊሶ ኦሮሞዎች ባህል የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የሟች ቤተሰቦች እና የጎሳው አባላት በዋናነት ለዚህ የሚሆኑ ግብዓቶችን የማሟላት ማህበራዊ ግዴታ ይጣልባቸዋል፡፡ የከብቶቹ እርድ የሚፈፀመው ከቀብሩ ቀን አንድ ቀን ቀደም ብሎ አመሻሽ ላይ ሲሆን የሚታረደው የከብት ቁጥር የሚወሰነው ይመጣል ተብሎ በሚገመተው የሰው ቁጥር ልክ ነው (ቃ.መ.አቶ ደበሳ ከፊኒ 08/08/13 ዓ.ም እና አቶ ምህረቱ ኩመላ፣ 03/08/013 ዓ.ም ወሊሶ ወረደ)፡፡

## የቀብር መሄጃውን መንገድ፣ የቀብሩን ቦታና ቤት ማዘጋጀት

የቀብር ቦታ በኦሮምኛ "አዋለ" የሚባል ሲሆን ቀደም ባለው የወሊሶዎች ባህል መሰረት በሁለት የተለያዩ ስፍራዎች ላይ የቀብር ቦታ እንዲዘጋጅ ይመረጣል፡፡ አንደኛው በሟች መኖሪያ አካባቢ ባለ የግል ማሳ (ግቢ) ውስጥ የሚሰናዳ ነው፡፡ ሟች በማሳው (ግቢ) ውስጥ የሚቀበርበት ምክንያት ኣንድ ነው፡፡ እሱም "አባ ገዳ" ሆኖ ልጁ አርባ (40) አመት ከሞላው ነው፡፡ ይህም የአባገዳዉ ጸጋና ስልጣን ከቤቱ እንዳይወጣ ከሚል እምነት የተነሰ ነዉ፡፡

እነዚህ የቀብር ስፍራዎች በአሁኑ ሰዓት ሙሉ በሙሉ ቀርተዋል ለማለት ባያስደፍርም አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በየኃይማኖት ስፍራው ተከልሎ በሚገኘው የቀብር ቦታ መቅበርን ተቀዳሚ ምርጫው ያደርጋል፡፡ ቀጥሎም ልምዱ ያላቸው ሰዎች ተለይተው ቀብሩ እዚህ ጋ ቢሆን የተሻለ ይሆናል የሚሉትን ቦታ በመምረጥ በአራት ማዕዘን ቅርፅ አራት ክንድ ጥልቀት ያለው ጉድጓድ ሰፋ ኣድርገው ይቆፍራሉ፡፡ ከዚያም የሬሳ ሳጥኑ የሚያርፍበትን ዙሪያ ገባ አድርጎ ይቆፍራሉ፡፡ በሙሉ አፈር እያጣበቁ (በአሁኑ ጊዜ በሲሚንቶ ነው የሚያጣብቁት) በጥንቃቄ በአጫጭሩ የተቆራጠዉን የዛፍ ፍልጥ ይደረድራሉ፡፡ በዚህ መልክ ፍልጡን በአግባቡ ከደረደሩ በኋላ ሳጥኑ የሚያርፍበትን

ዙሪያ ይሸፍኑታል፡፡ የኢኮኖሚ አቅማቸው ከፍ ያለ ወይም አንድ አይነት ማህበራዊ ስልጣን ያላቸው ከሆኑ ደግሞ ጉድጓዱ ሙሉ በሙሉ የድንጋይ ካብ ይሰራለታል፡፡ በመጨረሻም ሀዉልት የሚሰራም አለ (ቃ.መ. አቶ ለማ ታሲሳ ፣ 02/08/13ዓ.ም፣ ዱሌሌ ቀበሌ)፡፡



ፎቶ፡9 የቀብር ጉድጓድ

## የመኖሪያ ቤቱን አካባቢ ማፅዳት እና መስራት

አብዛኛውን ጊዜ የመኖሪያ ቤቱን አካባቢ የማፅዳት ኃላፊነት የሚጣለው በወጣት ሴቶች እና ወንዶች ላይ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ወ/ሮ ስሜነሽ ቶሌራ ሲያስረዱ "ሴቶቹ የመኖሪያ ቤቱን አካባቢ "እንጫሪ" በሚባል መያዣ ባለው ሙልጭ አድርገው ሳርና ቆሻሻውን የማስወገድ ተግባራቸውን ሲወጡ ወንዶቹ ደግሞ ከሴቶቹ አቅም በላይ የሚሆነውን በገጀራ በመመንጠር እና በቤቱ ዙሪያ ያለውን አጥር የማጠናከር ድርሻቸውን በትብብር ያከናውናሉ" (ቃ.መ. 05/08/013 ዓ.ም፣ በዴሰ ቆርቻ ቀበሌ)፡፡

ሌላው በጎልማሶች የሚሰራው ተግባር የዳስ ስራ ነው፡፡ ዳሱ የሚጣለው በሟች መኖሪያ ቤት ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የተፈለገበትን ዋንኛ ምክንያት አቶ ሞሮዳ ቶሌራ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

ከአራቱም አቅጣጫ የሚመጡትን ለቀስተኞች በየመጡበት አቅጣጫ ተቀብሎ ለማስተናገድ ሲሆን ዳስ ውስጥ በሚመደቡት የእድር አባል እንዴት ማስተናገድ እንደለባቸዉ ዉይይት ያደርጋሉ፡፡ በእያንዳንዱ ዳስ ውስጥ በዋናነት የሚመደቡት ወንድ እና ሴት አስተናጋጆች ሲሆኑ ከሴቱም ከወንዱም አንዳንድ አስተባባሪ ይሰየማል፡፡ እነዚህ አካላት ከቀብሩ ኣንድ ቀን ቀደም ብለው በመሰባሰብ በያቅጣጫቸው ያሉ ቀበሌዎችን በአግባቡ መለየት፣ ማን ተቀብሎ ቦታ ያስይዝ፣ ማን ምግብ ያቅርብ፣ ማንስ መጠጥ ያሳልፍ፣ . . .ወዘተ የሚሉት ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ነው የሚያድሩት፡፡ በመሆኑም የእነዚህ አካላት ምርጫ በህብረተሰቡ ዘንድ በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈፀም ነው፡፡ በተጨማሪም አቶ ሞሮደ ተሌራ እንደገለጹት ሞት በተከሰተበት አካባቢ የሚገኙ የአካባቢው ሰዎች እና የቤተሰቡ አባላት ቀብሩ አንድ ቀን ሲቀረው ጀምረው ያዘጋጁቸውን የዳስ መስሪያ ቁሳቁሶች ተጠቅመው በየአቅጣጫው በመከፋፈል ከቀብሩ ዕለት አንድ ቀን ቀደም ብለው የዳሱን ስራ በህብረት ይሰራሉ፡፡ አካባቢው በክዳንነት የሚያገለግለውን የስንዳዶ ሳር በርከት አድርጎ ማልበስ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በዚህ መልክ በሚዘጋጀው ዳስ ውስጥ አስከሬን በማስቀመጥ የሟች አማቾች በመጡበት ቀበሌ አቅጣጫ የቀብሩ ዕለትም ሆነ ከዚያ በኋላ ባሉት የሀዘን ቀናት እንዲቀመጡ ይደረጋል አቶ ሞሮደ ቶሌራያስረዳሉ፡፡ (ቃ.መ. 04/08/013 ዓ.ም፣ ጉሩራ ከተማ)፡፡

## እስከሬን ታጅቦ የሚሄድበት ማዘጋጀት

ይህ ዝግጅት የሚከናወነው ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሳይሆን "አባ ገደ" እና "ሃደ ሲቄ" የሞቱ ዕለት ብቻ ነው፡፡ አገልግሎቱም የ "አባ ገደ" እስከሬን ከሌላው ለቀስተኛ ለየት አድርጎ በክብር የመቃብር ቦታው ድረስ ሸፍኖ ማድረስ ነው፡፡

የ "አባ ገዳ" ቀብርም ሌላዉ የማህበረሰቡ ክፍል የሚቀበርበት ቦታ ሳይሆን ልጁ አርባ አመት (40) ሆኖ አባቱን ማለት አባ ገዳን ከቀበረ የቀብር ቦታዉ ግቢ ዉስጥ ይሆናል፡፡ መቃብሩ ላይ "ኦዳ" ይተከላል "ኦዳ" ማለት ትልቅ ዛፍ ኦሮሞዎች በጥላዉ ስር ተሰብስበዉ ብዙ ዉሰኔዎች የሚያስተላልፉበት ማለትም ከማህበረሰቡ የተጎደ ካለ ለማዳን (ካሳ ለመክፈል) የጎዳ ካለ ካሳ እንዲከፍል በማድረግ ማህበረሰቡን በእዉነተኛ ዲሞክራሲ በስሩ ተሰባስበዉ የሚያስተዳድሩበት ዛፍ ነዉ (የ.ቡ.ዉ.12/08/013) ያስረዳሉ፡፡

#### 4.3.4. የቀብር ጊዜ ክዋኔ

በወሊሶ ማህበረሰብረሰብ ለቅሶ ማህበራዊ ትስስርን ማጠንከሪያ፣ የሟችን እና የሟች ወገኖችን ማንነት መግለጫ፣ የሀብት መጠን ማሳወቂያ፣ ወዳጅ እና ጠላት መለያ፣ ወዘተ ተደርጎ የሚቆጠር በመሆኑ በተለይም በቀብሩ ዕለት የሚኖረው ዝግጅት ደመቅ ያለ ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው ከሟች ወይም ከሟች ቤተሰቦች ጋር እውቅና ያለው እያንዳንዱ የማህበረሰቡ አባል የትኛውንም አማራጭ ተጠቅሞ በቀብሩ ዕለት የመገኘት ማህበራዊ ግዴታ ያለበት መሆኑን አምኖ የተቀበለ በመሆኑ በቀብሩ ዕለት የሚገኘው ለቀስተኛ ቁጥር በእጅጉ የበዛ ነው፡፡ ይህ ሀቅ ይበልጡን የሚጎላው ደግሞ ሟች አንድ አይነት ባህላዊ የስልጣን ባለቤት ወይም ታዋቂ ግለሰብ የሆነ እንደሆነ ነው ሲሉ አቶ ፉርጋሣ (ቃ.መ. 03/08/013 ዓ.ም) ያስረዳሉ፡፡

የቀብሩ ዕለት ጠዋት፤ ወፍ ከመንጫጫቱ አስቀድሞ በሟች ቤት አቅራቢያ በያቅጣጫው በሚገኙ ኮረብታማ ቦታዎች ላይ በመሆን ጥሩንባ በተደጋጋሚ እንዲነፋ ይደረጋል፡፡ ይህን የሰሙ የአካባቢው ነዋሪዎች እና ከተለያየ አካባቢ የተሰባሰቡት ለቀስተኞች ወዲያው ነቅተው ወደ ሟች ቤት ጉዟቸውን ያደርጋሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦችም ከዚህን ሰዓት ጀምረው በዕለቱ መረር ያለ ለቅሶ እያደረጉ ከለቀስተኛው ፊት ይገኛሉ፡፡ የሚመጡትም ለቀስተኞች እንደቅርበታቸው ልክ ከሰፈር ጀምረው ከፍ ባለ ድምፅ ያለቅሳሉ፣ ደረታቸውን በሁለቱም እጆቻቸው አምርረው ይደቃሉ፣ እየዘለሉ ይወድቃሉ - ይነሳሉ፣ ፀጉራቸውን ይነጫሉ፣. ወዘተ.፡፡ በዚህ መልክ የተጀመረው ለቅሶ እስከ እኩለ ቀን ድረስ ያለሚቋረጥ በደማቅ ሁኔታ ይቀጥላል፤ የመጣው ለቀስተኛ ሁሉ በከባድ የሀዘን ድባብ ውስጥ ሆነው ከሚያለቅሱት፣ እየወደቁ ከሚነሱት፣ ደረታቸውን በኃይል ከሚደቁት፣ ፊታቸውን ከሚቧጥጡት፣. . .የሟች ቤተዘመዶች ፊት ሲደርስ ከደጅ ጀምሮት የነበረውን ለቅሶ በማጠናከር የሚሆኑትን ሁሉ እየሆነ ሀዘናቸው ሀዘኑ፤ ጉዳታቸው ጉዳቱ መሆኑን ለማስመስከር ይጥራል፡፡

በዚህ ሁኔታ ተጀምሮ ያለማቋረጥ እስከ እኩለ ቀን ድረስ የቀጠለው ለቅሶ ይበልጥ የሚፋፋመው እስከሬኑ ከቤት ወጥቶ ጉዞ ሊጀምር ሲል ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አብዛኛው የህብረተሰቡ አባል መረር ያለ ለቅሶ ያለቅሳል፡፡ ሴት የሟች ቤተሰቦች (በተለይም የሟች እናት፣ ሚስት እና ሴት ልጆች) የመውደቅ የመነሳታቸው ሁኔታ ከሌላው ጊዜ ያይላል፡፡ የሟች ሚስት፣ እናት፣ እህቶች እና ሌሎችም ሴቶች በብዛት በወቅቱ የሚለብሱት ነጭ ልብስ ገልብጠዉ ሲሆን በሀይማኖት ምክንያት ደግሞ የማይገለብጡም ይኖራሉ፤ አሁን አሁን ደግሞ ጥቁር የሚለብሱም አሉ፡፡ (ምልከታ 07/08/013 ዓ.ም)



**ፎቶ፡10 ሴቶች ለቅሶ ቤት**

በባህሉ መሰረት ሬሳው ከቤት ወጥቶ ጉዞ ሲጀምር የሚከናወኑ ልዩ ልዩ ስርዓቶችን እንደሚከተለው በዝርዝር እንመልከት፡፡

***መውደቅ መነሳት*** **፡--** በወሊሶ የለቅሶ ስርዓት ላይ ዛሬም ድረስ በዋናነት ከሚፈፀሙት ባህላዊ ተግባራት መካከል ድምፅን ከፍ አድርጎ እያለቀሱ በተደጋጋሚ እየወደቁ መነሳት መሆኑን ወ/ሮ ገነት ከበደ እና አቶ ገዘሃኝ ንጉሴ ጠቅሰው እንደሚከተለው በስፋት ያብራራሉ፡፡ "ይህን ተግባር በዋናነት የሚፈፅሙት ሴት የሟች ቤተሰቦች እና የቅርብ ወዳጆች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሀዘኑ እጅግ የጎዳቸው ወንዶችም ወድቀው ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ሴቶቹ በሚወድቁ በሚነሱበት ሰዓት ደረታቸውን በእጅጉ እየደቁ፣ ፊታቸውን እየቧጠጡ እና ፀጉራቸውን እየነጩ ነው፡፡ ይህንን የሚያደርጉት በዋናነት በተፈጠረው ክፉ አጋጣሚ እጅጉን ማዘናቸውን ለመግለፅ እና ከእሱ/ ከእሷ ይልቅ እኔ ነኝ መሞት ያለብኝ የሚለውን ስሜት እንዲወክልላቸው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሀዘን ስሜታቸውን ለታዳሚው በማጋባት የወገናቸው ለቅሶ የደመቀ እንዲሆን የማድረግ ዓላማም አለው፡፡

መውደቅ መነሳቱ የሚከወነው ቦታ እየተመረጠ ሳይሆን ድንገት በተገኙበት ስፍራ ላይ ስለሚሆን በርካታ ሰዎች ከፍ ላለ ጉዳት የሚጋለጡባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ የሟች የቅርብ ዘመድ ሆነው ነፍሰ ጡር የሆነች ሴት ካለች፣ ህመምተኞች ቢኖሩ፣ እርጅና

የተጫጫናቸው ከሆኑ ወድቀው እራሳቸውን ለጉዳት ከመዳረጋቸው በፊት ቀደም ብሎ ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ሆነው በሚመደቡ ጠንከር ያሉ ሴቶች ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ሴቶች እንዲጠብቋቸው የተመደቡባቸው አካላት የመውደቅ አዝማሚያ ሲያሳዩ ከኋላ ሆነው በፍጥነት ወገባቸውን በመያዝ ከአደጋ ይታደጓቸዋል ወንዶቹም ለብቻ የተሰማቸዉን ሃዘን "አን በዴካ" ማለት እኔ ጠፋሁ በማለት ቅኔ እየጨመሩበት ሰዉን የሚያስለቅሱበት ሁኔታም አለ" (ቃ.መ. 05/08/013 ዓ.ም፣ ኦብ ኮጂ ቀበሌ እና ቃ.መ. 04/08/013 ዓ.ም፣ ዳሙ ቀበሌ) ፡፡

ሙሾ "ቦችሳ" በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ከሴቶችም ሆነ ከወንዶች መካከል ተመርጠው ወዲያ ወዲህ እያሉ ሙሾ በመደርደር በተለይም "ኦፊን ኦፊን" ኢያሉ አልቅሰው በሚያስለቅሱ ሰዎች ኢየተመረ የሚፈጸም ክዋኔ ነዉ፡፡ በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ በሙሾ ስርዓት (ቦችሳ) ለቀስተኞች የተለያዩ ቁሳቁሶችን (የሟች ልብስ፣ የሟች ፎቶ፣ ጋሻ፣ ጦር፣ ቀጭን ዱላና የመሳሰሉትን) በመያዝ በፈረስ ወይም በእግር በመንቀሳቀስ በግል ወይም በቡድን በመሆን በመፎከር የሟችን ጀግንነት፣ ሩህሩህነት፣ ቸርነትና ደግነት የሚገልጹበትም ነዉ፡፡



**ፎቶ፡11 በእግር በግል ሙሾ የሚያቀርቡ ሰዎች**



**ፎቶ፤12 የሟች ፎቶና ልብሶች ለማስለቀሻ**

*ይህን በተመለከተ ወ/ሮ ሸዋዬ ባይሰ "ሙሾ አውራጆች በዋናነት የሚመረጡት ከቤተሰብ አሊያም ከቅርብ ዘመድ መካከል ልምድ ያላቸው ተለይተው ነው፡፡ የሙሾ ደርዳሪዎች ምርጫ ከቤተሰብ አባላት መካከል እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት ከሌላው ይልቅ የሀዘኑ ስሜት በዋናነት የጎዳቸው በመሆኑ የማስለቀስ አቅም ያለው ሙሾ መደርደር ይችላሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው" (ቃ.መ. 06/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ) ሲሉ ያስረዳሉ፡፡*

*ሙሾ አውራጆቹ አብዛኛውን ጊዜ ሙሾ የሚደረድሩባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች አቶ ሀምቢሣ መርጋ ሲያብራሩ "ሙሾ የሚደረደረው የሟችን ደግነት፣ ጀግንነት፣ ለሰው አሳቢነት፣. . .ወዘተ በተመለከተ እና የሞትን ጨካኝነት፣ ሞት የማይቀር፤ የሚገልም ሆነ የሚያድን ፈጣሪ መሆኑን፣. . .ወዘተ በሚዳስሱ ጉዳዮች ዙሪያ ነው (ቃ.መ. 03/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ) ከእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች አንፃር የተወሰኑ የሙሾ ግጥሞችን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡*



ፎቶ፡13 በፈረስ ሙሾ ሲያቀርቡ

**የሟችን ደግነት ለጋስነትን የተመለከቱ የሙሾ ግጥሞች**

| በኦሮምኛ | በአማርኛ |
|---|---|
| Goota arba ajjeese eessa geessu | ዝሆንን የገደለ ጀግና የት ይወሰዳል |
| Sanyii gootaa, sanyii dhiiraa eessa geessu | ጀግናዉ የወንድ ዘር የት ይወሰዳል |
| Goota faacha muru eessa geessu | ጀግናዉ “ፈቻ”ን የምቆርጥ የት ይወሰዳል |
| Abbulee abbaa kormaa | ታዋቂ ከብቶች ያለዉ ጀግና አባት |
| Abbaa fardaa abbaa sangaa | የፈረስና የበሬዎች ባለቤት |
| Abbaa warqii abbaa birriii | የወርቅና የብር ባለ ሃብት |
| Sanyii namaa abbaa firaa | ባለ ብዙ ዘመድ የሰዉ ዘር |
| Abbaa lammii abbaa biyyaa | የሀገርና የጎሳ መሪ |
| Silas du’a hinoolanii | መቼስ ሞት አይቀርም |

| | |
|---|---|
| Sinyaattekaa biyyeen | አፈር በላችህ/ሽ |
| Maal waliif godhu | ምን ይደረጋል |
| Du'aa hinka'anhoo | መቼም ከሞት መነሰት የለም |
| Ka'anii fira hinarganhoo | ተነስቶ ዘመድ ማየት የለም |
| Ka'ii ilaalimee soddaan dhufee | አማቾች መጡ ተነስና እያቸዉ |
| Ka'ii ilaalimee lammiin dhufee | ጎሳዎችህ መጥተዋል ተነስና እያቸዉ |
| Abbaa ilmaa abbaa hintalaa | የወንድና ሴት ልጆች አባት ሆነህ |
| Abbaa firaaf biyyaa eessa deemta | ባለብዙ ዘመድ የህዝብ አባት የት ትሄደለህ |
| Goota goota caalu | ጀግና ጀግናን የሚበልጥ |
| Kan diina haleelu | ጠላትን የሚገለባብጥ |
| Abbaa marii abbaa malaa | የመፍትሄ አባት አባ መላ |
| Dubbiin beekamaa ala oolaa | ሰዉን ለማስተረቅ አደባባይ የዋለ |
| Nama araarsuun beekamaa | ሰዉን የምታስታርቅ ችግርን የምትፈታ |
| Ke'ee bareedaakoo hunda bareechita | ቆንጆ ቁኤ ያለህ ሁሉን የምታበረታተ |
| Abbaa sangaa mirreekoo | ባለ ብዙ በሬ |
| Abbaa gumbii mirreekoo | ባለ ብዙ ጎተራ |
| Abbaa daaleekoo | ዳለቻ ፈረስ ያለዉ |
| Abbaa daamaakoo | ዳማ ፈረስ ያለዉ |
| Leencakoo | የኔ አንበሳ |
| Sanyii nama gaarii | የጥሩ ዘርና ጎሣ |
| Hiriyaa nama gaarii | የጥሩ ዘር ጎደኛ |
| Dhaloota tolee dhalannaan tole | ትዉልዱ የቀና ተወልዶም የሰመረ |
| Araarsaan biyyaa eenyu simalee | ሰዉን የሚያስታርቅ እጅግ የተከበረ |
| Mucaa sanyii bareedu | በጎሳ የተመረጥክ ልጅ |
| Mucaa warra abaluu | የእነ እከሌ ልጅ |

| | |
|---|---|
| Araarsa gaaddisaa hundi jaalatu | የሽማግሌዎች ጥላ በሁሉም የምትከበር |
| Gooftaa gaafa rakkoo namaaf birmatu | ለችግር ጊዜ ለሰዉ የምትደርስ ገር |
| Abbulee bultii bareedaa | በኑሮ ጥሩ የተካንህ |
| Abbaa joorroo bareedaa | ጥሩ በሬ ያለህ |
| Qottuu maanyaa qonxolaa | ነጭ ጤፍን በማረስ የታወቅከዉ |
| Ijaarrataa mana ofii | ጥሩ ቤት ያለህዉ |
| Gooftaa namaa liqeessu | ለሰዉ የሚያበድረዉ |
| Dureessa gootaraabdilbii | ሀብታም ባለ ብዙ ጎተራ |
| Gooftaa mana dhugaa | እዉነት ከቤቱ የምገኝ |
| Gooftaa cooma namaaf laatu | ሎሚን የምያበለ |
| Namticha daadhii nama obaasu | ጠጅ የምያጠጣ |
| Abbaa ijoollee korommii | ጥሩ ልጆች ያሉት |
| Abbaa mundhii shugguxii | ሽጉጥ ከወገቡ የማይጠፋ |
| Abbaa beeljigii mirxii | ምርጥ በልጅግ ያለዉ |
| Dhiira alaa nama galchu | ታዋቂ |
| Ati loltee gumaa baastee seera baaste | ካሳ ከፍለህ ህግን ያስከበርክ |
| Biyya keenya eegee akka eegamu goote | ሀገረችንን የጠበክና ያስጠበክ |
| Karaan fixee mirga horate | የሀገሪቱን ጫፍ የደረስክ |
| Horii booji'e | ከብቶችን የማረክ |
| Ni moote | ያሸነፍክ |
| Eebon waraanee | በጦር የወጋህ |
| Qawween waraanee | በጠብመንጃ የመታህ |
| Fardaan waraanee | በፈረስ የወጋህ |
| Abbaa farda cimaa | ጥሩ ፈረስ ያለህ |
| Maaloo eessa deemtaa | አረ ወዴት ነዉ የሚትሄደዉ? |

የወሊሶ ማህበረሰብ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ በዋናነት ምርጫው የሚያደርገው የጋማ ከብቶችን ነው፡፡ ስለሆነም የቸገረው ሲጠይቅ ፈረሱን የሚያውስ፣ የማህረሰቡ ኑሮ የተመሰረተው በጥምር ግብርና እንደመሆኑ መጠን ለእርሻ የሚያቀናጀው በሬ አጥቶ ሲጠይቅ ፊቱን ሳያጠቁር የሚሰጥ እና ለተቸገረ የሚያበድር ሰው ሲሞት በተራ ቁጥር 1 ላይ በቀረበው መልኩ ሙሾ በመደርደር ማልቀስ የተለመደ ተግባር መሆኑን አቶ ነገሱ አምዲሣ (ቃ.መ. 07/08/013 ዓ.ም፣ ሌመን አንጬቢ ቀበሌ) ያስረዳሉ፡፡

በተራ ቁጥር 2 ላይ የቀረበው የሙሾ ግጥም በይዘት ከቀደመዉ ጋር የሚመሳሰል ሆኖ ይህኛው የሚደረደረው በሴቶች የለቅሶ ስርዓት ላይ ነው፡፡ ሙሾዉ የሚደረደራዉ ወንዶች በግል በመሆን የሟችን ደግነት በግጥም መልክ ድምጽን ከፍ በማድረግ በእግር ወይም በፈረስ እየፎከሩ የሚደረድሩ ሲሆን ሴቶች ደግሞ ከኋላቸዉ እየተከተሉ በታዳሚዉ ፊት እየሮጡ ደረታቸዉን በመድለቅ ሀዘናቸዉን ይገልጻሉ፡፡

| በኦሮምኛ | በአማርኛ |
|---|---|
| Haadha kormootaa | ብዙ ወንድ ልጅ ያላት |
| Giiftii dhaloota tolte | ከትዉልድሽ የተባረክሽ |
| Ishee dhalannaan tolte | ተወልዴሽም የተመቸሽ |
| Laachuuf hinsiisuu kan beektu | የምታበላ የምታጠጣ አዋቂ |
| Ni fuusisu jennaan fuusifte | ወንድ ልጆችሽን ለትዳር ያበቃሽ |
| Ni heerumsiisu jennaan heerumsiiftee | ሴት ልጆችሽን የዳርሽ |
| Maqaaf ke’ee warra dhuftee eegdee | ያገቡሽ ቤተሰብ ስማቸዉን ይዘሽ |
| Kaamettii giiftii dhaqaa gala itti goran | ባለ ሞያ |
| Haadha manaa nama gaarii | የጥሩ ሰዉ ባላቤት |
| Haadoo ebaluu ebaluu | የእከሌ እከሌሌ እህት |
| Laattu obaaftu waan quufan hinseetu | ሰዉ ሲበላ የሚጠግብ የማይመስልሽ |

"ኦፈን"፡- የ "ኦፈን" ን ምንነት አቶ ምህረቱ ኩመላ ሲያስረዱ "በእኛ ማህበረሰብ ባህል መሰረት የሚች ወገኖች ሀዘናቸዉን እራሳቸው ከማህበራሰቡ ጋር በመሆን ኦፈን እያሉ በቡድን ሀዘኑን በሙሾ መልክ አውራጅ ግጥምን በዜማ መልክ ስደረድር ተቀባዮቹ ተቀብለዉ እያዜሙ በለቀስተኞቹና በታዳሚዉ ፊት ለፊት በፈረስም በእግርም እየተመላለሱ ያቀርባሉ፡፡" (ቃ.መ. 18/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ) በማለት ነው፡፡

| በኦሮምኛ | በአማርኛ |
|---|---|
| Oofan oofan | "ኦፈን ኦፈን" |
| Sanyii namaa oofan | የሰዉ ዘር "ኦፈን" |
| Eessa geesu oofan | የት ይወስዳሉ "ኦፈን" |
| Abbaa fardaa oofan | ባለ ፈረስ "ኦፈን" |
| Abbaa karraa oofan | ባለ ብዙ ከብት "ኦፈን" |
| Abbaa sa'aa oofan | ባለ ላም "ኦፈን" |
| Abbaa kormaa oofan | ባለ ወይፈን "ኦፈን" |
| Eessa geessu oofan | የት ይወስዳሉ "ኦፈን" |
| Re'een dhalte oofan | ፍየል ወለደች "ኦፈን" |
| Eessa dhaqxa ke'ee gattee oofa | የት ትሄዳለህ ቀየ ትተህ "ኦፈን" |
| Yaa waleensuu | "የወሌንሱ ኦፈን" |
| Muka gamaa oofan | የወንዝ ዛፍ "ኦፈን" |
| Yaa bareedduu oofan | ቆንጆዉ "ኦፈን" |
| Sanyii namaa oofan | የሰዉ ዘር "ኦፈን" |



**ፎቶ፡14 በእግር/በቡድን ሙሾ (ኦፈን) የሚያቀርቡ ሰዎች**

በዚህ መልክ የተጀመረው ክዋኔ ለሁለት ሰዓት ያህል ያለማቋረጥ ቀጥሎ በሽማግሌዎች በቃ ባይነት እንዲቆም ይደረጋል፡፡ ልክ የኦፈን ስርዓቱ እንዳበቃ ጉዞ ወደ ቀብር ስፍራ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ሟች ኣንድ አይነት ማህበራዊ ስልጣን ያለው ከሆነ ቀብሩ የሚፈፀመው ለእነዚህ አካላት ታስቦ በተዘጋጀ አካባቢ ልክ የቀብር ቦታው ሲደርሱ ቀደም ሲል አስከሬኑ ከቤት ሲወጣ በነበረው ልክ አምርረው ማልቀስ ይጀምራሉ፡፡ የቀብር አፈፃፀም ሂደቱን በሚገባ የሚያውቁት አካላት አስከሬኑን ከመሸከሚያው አውርደው ወደ ተዘጋጀለት ጉድጓድ ውስጥ በጥንቃቄ የማስገባቱን ተግባር ይፈፅማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ከቀደሙት ጊዜያት በበለጠ መልኩ ከፍ ባለ ድምፅ እና በምሬት ማልቀሱ፣ መውደቅ መነሳቱ፣ ደረት መድቃቱ፣ ፊት መቧጠጡ፣ . . .ወዘተ በስፋት ይከወናል፡፡ ከሟች ጎሳ አባላት መካከል በዕድሜ ገፋ ያሉት አዛውንት ወይም ኣንጋፋዉ ወንድ ልጅ የመጀመሪያውን አፈር ወደ አስከሬኑ በመጨመር አፈር የማልበሱን ሂደት ያስጀምራሉ፡፡ ወንዶቹ በመተጋገዝ አፈር በመጨመር ጉድጓዱን ከሞሉት በኋላ በስተመጨረሻ በድንጋይ ጥቅጥቅ አድርገው በመድፈን ግብዓተ መሬቱን ይፈፅማሉ፡፡ (የተ.ቡ.ው. 12/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ)

### 4.3.5. ድህረ ቀብር ክዋኔ

የወሊሶ ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ አቅሙን እና ማህበራዊ ትስስሩን ከሚገልፅባቸው አጋጣሚዎች መካከል ልደት፣ ሰርግ እና ሞት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን

የለቅሶ ስርዓት በማህበረሰቡ ዘንድ ለእነዚህ ሁነቶች ደምቆ መታየት ዋንኛ አጋጣሚ ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ የለቅሶ አጋጣሚ ላይ የሚችን ኢኮኖሚያዊ አቅም እና ማህበራዊ መስተጋብር መሰረት አድርጎ ሰፋ ያለ ቅድመ ዝግጅት ሊደረግ የሚችልበት ቀደም ሲል ዝግጅታቸውን አስመልክቶ በቅድመ ቀብር ጊዜ ክዋኔ ወቅት በዝርዝር የተመለከትናቸው ምግብ እና መጠጦች ለታዳሚው የሚቀርቡበት በዚሁ ከቀብር በኋላ ባሉት ጊዜያት የምርቃትና የመሰናበቻ ጊዜ ይሆናል፡፡

#### 4.3.5.1. የማሳረጊያ /የምርቃት/ ስርዓት "ኤባ"

የማሳረጊያ ምርቃት ስርዓት ለቀብር ስነ ስርዓት የመጣውን ዘመድ የሚመርቁበት እና የሚችን ነብስ ይማር የሚሉበት ጊዜ ነው፡፡ ይህም የሚፈጸመዉ የቀብር ስርዓቱ እነደተጠናቀቀ ቀብሩ በተፈጸማበት ቤተ እምነት ፊት ለፊት ወይም እዝያዉ በቀብሩ አካባቢ በትላልቅ ዛፎች ስር በመሰብሰብነዉ፡፡ ምርቃቱን መጀመርያ የሚፈጽሙት የሀይማኖት አባቶች ሲሆኑ በመቀጠል ከሚች ቤተሰቦች አንጋፋዎች ይመርቃሉ፡፡ ምርቃቱ ሲደረግ መራቂዉቹ ከህዝቡ ፊት ለፊት በመቆም ሲመርቁ ታዳሚዎቹ ተቀምጠዉ ጭንቅላታቸዉን ዝቅ በመድረግ አሜን/ይሁን (ሃተኡ) ኢያሉ በመቀበል ይፈጸማል፡፡ ምርቃቱንም በሚች ንጉሴ ማሞ ቀብር ላይ እንደተመለከትኩት ከሽማግሌዎች ቅርብ ዘመድ ወይም ወንድ ልጅ የሚከተለውን ብሎ ይመርቃል (ምልከታ 16/08/013)፡፡

| በኦሮምኛ | በአማርኛ |
| --- | --- |
| Biyyi keenya nagaa haata'u | ሀገራችን ሰላም ይሁን |
| Rabbi isaaf/isheef haadhisu | እግዜር ይቅር ይበለዉ |
| Allii manni isaa/ishee nagaa haata'u | ቤቱና ደጆቹ ሰላም ይሁኑ |
| Maatin isaa nagaa haata'u | ቤተሰቦቹ ሰለም ይሁኑ |
| Maatiifi firaaf rabbi daangaa yaa godhuuf | ሞት በዚህ ይብቃ |
| Ebalu illee gaafa xiiqii lolee gaafa tolaa tolee | ቆራጥ ነዉ ሩህሩህ ነዉ |
| Har'a itti galgalaa'ee dukkana hinbariine seenee | ዛሬ ጨልሞበታል እነጂ |
| Heerumsiisee fuusisee har'a itti galgalaa'e | ድሯል ዛሬ ቢጨልምበትም |
| Kanumaan daangaa firoota isaaf haata'u | ሞት በዚህ ይብቃ |
| Inni jibbitu kunoo ilma qabaa itti fufi | የምትጠላዉ ወንድ ልጅ አለዉ ቀጥል |

Inni jaalattu immoo hin na'inii jaaladhu     የምትወደዉ አትደንግጥ

Ke'ee kana rabbi nagaa haataasisu     ይሄን ቀየ እግዜር ሰላም ያድርገዉ

Kanumaan rabbi daangaa isiniif haataasisu     እግዜር በዚሁ በቃ ይበላችሁ

Faana nama kanaa rabbi nagaa isin haataasisu     ያለ ጊዜ ሞት አያግኛችሁ

Rabbi obsa isiniif haa kennu     ትግስቱን እግዜር ይስጣችዉ

ብለዉ ከመረቁ በኋላ በቀብሩ ላይ ጉድጓድ ለቆፈሩ እስከሬኑን ለተሸከሙት እንዲህ ብለዉ ይመርቃሉ፡፡

Firri mana nagaatii baatan mana nagaatti galaa     ሰላም ያለዉ ቤት ግቡ
Jabbii burraaqxu ijoollee taphattutti galaa     ወደሚቦርቁ ጥጆችና ልጆች በሰላም ግቡ

Gateettii ittiin nuuf baattan dirriba uffadhaa     በተሸከማችሁበት ትከሻ ድርብ ጋቢ ልበሱ

Kan akkanaa keessa hintaa'inaa     ይሄን የሚመስል ዉስጥ አትቀመጡ

Kolfaaf gammachuu keessa taa'aa     ሳቅና ደስታ ያለበት ቤት ዉስጥ ኑሩ

Du'a akka malee isin haa oolchu     ያለ አግባብ ሞት አያጋጥማችሁ

Mana nagaatii baatanii mana nagaatti galaa     ሰላም ወዳለዉ ቤት ግቡ

Ee warri gaddi itti gale kun jajjabina haa argatan     "ኤ" መፅናናትን እግዜር ይስጣቸዉ

Duuti kun asumaan daangaa isinii haata'u     ከእንግድህ ያለግዜ ሞት ቤታችሁ አይግበ

Inni boochu jajjabaadhu inni gadditus dhiisi     አታልቅሱ አትዘኑም

በማለት ይመርቃሉ፡፡



ፎቶ፡15 የመራቂዎችና ታዳሚዎች ፎቶ

የምግብ እና የመጠጥ ስርዓቱን በተመለከተ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላት እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

እያንዳንዱ ለቀስተኛ የመጣበትን አቅጣጫ መሰረት አድርጎ በተዘጋጀለት ሰፋ ያለ ዳስ ውስጥ በአስተናባሪዎች አማካይነት እጅ እና ፊቱን እየታጠበ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ ከዚያም በአስተናጋጆች አማካኝነት እንጀራ እና ቆጮውን አስቀድሞ ሲያሲዙ ሌላ ወጥ ጨላፊዎች ለእያንዳንዱ እያደረጉ ያልፋሉ፡፡ ተከታዩ አስተናጋጅ ደግሞ ከከብቶች ቀንድ በተዘጋጀ "ዋንጫ" በተሰኘ ባህላዊ መጠጫ ጠጅ/ ጠላ እየቀዳ ማደሉን ይያያዛል፡፡

ሁሉም ሰው የሚበቃውን ያህል ከበላ እና ከጠጣ በኋላ ቡና ለሚፈልግ ቡና ለማይፈልግ የገብስ ወይም የስንዴ ቆሎ እንዲቀርብለት ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም በሽማግሌዎች አስተባባሪነት ሁሉም “kan du’e namsii haa maaru” (ፈጣሪ ነፍሱን ይማር) ብለው የፕሮግራሙ ፍፃሜ ይሆናል፡፡ ከዚህ በኋላ ከሩቅ የመጡት እና የቅርብ ዘመዶች እዚያው እንዲያድሩ ሲደረግ ሌሎች ግን ወደ ቤታቸው ሄደው በተመቻቸው ሰዓት እየመጡ ያስተዛዝናሉ (የተ.ቡ.ው. 12/08/013 ዓ.ም፣ ወሊሶ)፡፡

ከቀብር በኋላ ትኩረት ተሰጥቶት ስለሚፈፀመው ሌላኛው ተግባር አቶ ሽፈራ አሰፈ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

በባህላችን በሦስተኛው ቀን በደማቅ ሁኔታ ነው የሚከበረው፡፡ በዚህ ቀን ዘመድ አዝማድ፣ ጎረቤት እና ጓደኞች ወፍ ሳይንጫጫ ከያሉበት በሟች ቤት ተሰባስበው ወንዶች ማረሻ ይዞ ወደ ቀብሩ ስፍራ ይጓዛሉ፡፡ እዚያ እንደደረሱም ሁሉም ከ30 ደቂቃ ላላነሰ ጊዜ በጣም አልቅሰው "ካቢ" የሚባለዉን አፈር በዙርያዉና በቀብሩ ላይ የመከመር ሥራ ይሰራሉ፡፡ ከአንድ ሳምንት በኋላ በቀብሩ ዋዜማ የተሰራዉ "ዳስ" ይፈርስና "ቡና ቀላ" እና ዲባዩ ተዘጋጅቶ ሽማግሌዎች ተሰባስበዉ እንዲህ በማለት ይፀልያሉ "ati kan du'aan buluun nu bulchi yaa rabbi nu'i kan jiraan buluun nu bulchi" አንቴን ሙታን በሚኖሩበት ፈጣሪ ያኑሪህ እኛን እንደ ህያወን የኑራን ብለዉ የተዘጋጀዉን እህል ይቀምሱና ከግቢ ዉጭ ወደ ግቢ ይጋባሉ፡፡ ከሁለት ሳምንት በኋላ አሁንም የጎሳ መሪ ወይም ሽማልሌዎች ይመጡና ወተት በሞተላበት "ቀቤ" ዉሃ ይዘጋጅና ከሽማግሌዎቹ በጎሳ መጀመሪያ የተወለደዉ ለምሳሌ ከወሊሶ ልጆች መጀመሪያ "አቡ"፣ "ወሌ"፣ "ሌማን" እና "ሙኞ" እያሉ ይመርቃሉ ማንም ይህን በኩርነት አይከለክላቸዉም፡፡ ምርቃቱን እንዲህ በማለት ይመርቃሉ "ኑት ቀበኔፈኔ ያረብ ኑፍ ቀበኔሲ" እኛ ሀዘኑን ትተናል ፈጣሪ አንተም ድንበር አድርግልን ብለዉ ዉሃዉን እንደሚጠጣ ሰዉ አድርዉ ይደፋሉ፡፡ "ዲባዩን" ደግሞ "አት ከን ዱአን ቡሉን ቡል" አንተ ሙታን በሚኖሩት ያኑሪህ ብለዉ ይደፋሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ቤት ይገቡና መጥቶ የሚጠይቅ ዘመድ ቤት ይጠይቃል ማለት ነዉ፡፡ መጥቶ የሚያለቅስ ካለ "qabbaneeffanneerra" አቀዝቅዘናል እያሉ ሰዉ መጥቶ እንዳያለቅስ ይደረጋል፡፡ (ቃ.መ.08/08/013)

#### 4.3.5.2. የሙት ዓመት አከባበር ስነ ስርዓት (ዲባዩ)

በወሊሶ ማህበረሰብ "ሙት ዓመት" ሲከበር በባህሉ መሰረት ራሱን የቻለ ስነስርዓት አለዉ፡፡ ይህ የሙት ዓመት መታሰቢያ የለቅሶ ስነ ስርዓት ሟች ከቀብር ስነ ስርዓት በኋላ በአስራ ሁለተኛው ወር ላይ የሚደረግ ስነ ስርዓት ነው፡፡ ይህን በዓመት አንድ ጊዜ የሚደረግ ስነ ስርዓት የሟች ባላቤት ወይም ልጆች የሚያከናውኑት ነው፡፡ የቡድን ተወያይ እንደገለጹልኝ ይህ ስርዓት ግን ለሁሉም አይደረግም፡፡ ከህጻናት ጀምሮ እስከ አዋቂዎች ድረስ የማይደረግ ስነ ስርዓት ነው፡፡ ይህ ስነ ስርዓት ካገቡት ጀምሮ እስከ አዛውንት ወይም "gadamoojjii" ድረስ የሚከወን ስርዓት ነው፡፡ ለህፃናት እና ላለገቡት የማይደረግበትም ምክንያት "ህፃናት" እንደተወለዱ በንፅህና ያሉ እና ኃጢያት

የላቸውም በማለት ሲሆን ለወጣቶች/ላላገቡ/ ደግሞ ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን አልደረሱም በማለት ነው፡፡ በዕድሜያቸው ሲገለጽ ከ8-17 ዓመት ያሉት ናቸው /የቡድን ተወያዮች፣ 12/08/2013 ወሊሶ/፡፡

ይህ ሙት ዓመትም ሟችን ለመርሳትና ግብዓተ መሬት ከተፈፀመ በኋለ ነፍሱ ወደ መንግስተ ሰማያት ይገባል ተብለዉ ሙሉ በሙሉ ይታመናል፡፡ በወሊሶ ኦሮሞ እምነት የሙት ዓመት ፍትሃት ስነ ስርዓት እስከ ኣሁን ድረስ ያልተረሳና ያልቀረ መሆኑን /የቡድን ተኮር ተወያዮች 12/08/2013) ገልፀውልኛል፡፡

በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ደግሞ የሙት ዓመት ቀን ታስቦ ፍትሃት /ቅዳሴ/ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ለሙት ዓመቱ መታሰቢያ ተዝካር ይዘከራል፡፡ በዝግጂቱ ላይም ምስኪኖችና ልጆችን ጨምሮ ሁሉም የአካባቢ ሰዎች እንዲሁም ዘመድ አዝማድ ተገኝተዉ ከበሉና ከጠጡ በኋለ ነፍስ ይማር እያሉ ይሄዳሉ፡፡ /ቃ.መ አቶ ብሊሱማ ምደክሳ 10/08/2013/ ወንጪ፡፡ ይህ የሙት ዓመት "ዲባዩ" የሚደረገዉ የሟች ቤተሰቦች አስቀድመው ለሚበላውም፣ ለሚታረደውም እና ለሚጠጠው በጀት ያስቀምጣሉ፡፡

ሌላው በወሊሶ ኦሮሞ የሚታወቅ "ዲባዩ" ስሆን በሙት አመት በሰኞ ሌሊት ብቻ "ጉያ ኤኬራ" የሚዘጋጅ የ "ድባዩ" ስርኣት ኣለ፡፡ በዚህ ስርኣት ላይ የኦሮሞ ጠላ "ፊርሶ ኦሮሞ"፣ "ቡና ቀላ" እንድሁም የሚበላው የሚጠጣው ይዘጋጀል፡፡ ጎረቤት እና ዘመድ አዝማድ ሁሉ ይጠራል፤ ሁሉም ተሰብስበዉ ባሉበት ሽማግሌዎች እንዲህ ብለዉ የተዘጋጀዉን "ድባዩ" ይደፋሉ "ati kan du'aan buluun nu bulchi yaa rabbi nu'i kan jiraan buluun nu bulchi" አንተ/አንች ሙታን በሚኖሩበት ኑር/ሪ እኛን ህይወት ካለዉ ሰዉ ጋር ኣኑረን "biqila kana fudhu" የተዘጋጀልህን ዉሰድ፡፡ "biqila namaa, biqila sa'aa, biqila midhaanii gadi dhiisi" የሰዉን፣ የእንስሳትን እና የእህልን ቡቃያ ልቀቅልን ብለዉ የተዘጋጀዉን "ዲባዩ" የሰዉ እግር የማይደርስበት ቦታ መርጠዉ ይደፋሉ ምክንያቱም ሟቹ ይወስዳል ጤነኛ ሰዉ ከረገጣ ለበሽታ ይዳረጋል ብለዉ ስለምያምኑ ነዉ፡፡ (ቃ.መ 22/08/13 ወሊሶ)



ፎቶ ፡ 16 "ቡና ቀላ"

### 4.3.5.3. ሐዘንተኞችን ለማጽናናት የሚደረግ ክዋኔ

የወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ሐዘንተኞችን ለማጽናናት ብዙ የሚከውናቸዉ ነገሮች ኣሉ፡፡ ክወኔዎቹ ኣንድ ሰዉ ከሞተ ጎራቤት፣ እድርተኞች፣ ጓደኞች፣ ዘመድ አዝማድ እንዲሁም ወጣት ወንድና ሴት የሚከውኑት ክዋኔ አለ:: (ቃ.መ 05/08/13)

1. ጎረቤት

ኣንድ ሰዉ ጎረቤት ሆኖ ሰዉ ከሞተበት መርዶ ከሆነ ለቅሶዉ ቦታ አብሮ በመሄድ ከቀብር በኋለ ወደ ቤቱ ይዞ በመመለስ ምሽቱን ደግሞ ልጅ ያላት እናት ወይም በአቅም ምክንት ወደቤታቸው መመለስ የማይችሉትን እቤት ያስቀሩና ቡና እና እራት እንዲዘጋጅ ይደራጋል፡፡ አብሯቸዉ የወጣዉ ጎረቤት ሁሉ ቤቱ ድረስ ኣብሮ ይሄድና የተዘጋጀዉን ቡና እና እራት በልቶ ማታዉን እዚያ ያመሻል፡፡ ለሁለት ሳምንት ምንም አይነት ስራ አይሰሩም፡፡ ተራ በተራ ከቤታቸዉ ቡና እና የቡና ቁርስ በማምጣት ቤት ዉስጥ ይጠቀማሉ፡፡ ቡና በሚቀርብበት ሰዓት በተረት በምሰሌያዊ አነጋገር ትምህርት አዘል ቁምነገሮችን ያስተምራሉ (ቃ.መ 05/08/13) ፡፡

ለቅሶዉ ደግሞ ቤት ዉስጥ ከሆነ እስከ ኣንድ ወር ቤቱ ዉስጥ ምንም አይነት ስራ አይሰራም ወንዶቹ የወንድ ስራ የራሱን ትቶ ሲሰራ ሴቶች ደግሞ ቤት ዉስጥ የሚሰራ ሁሉ እንደ ራሷ ቤት ስትሰራ ትኖራለች፡፡ የተወሰኑ ሰዎች የዉጭ ስራ ከሰሩ የተወሰኑ ደግሞ ቤት ዉስጥ በመቅረት የመጣዉን እንግዳ ያስተናግዳሉ፡፡ ቀኑን ሙሉ እንደዚያ ሲሰራ ከርሞ ማታ ደግሞ ሴቶቹ እራት በማዘጋጀት እና ቡና በማፍላት ሲቆዩ ወንዶች በተለይ የእድሜ ባለጸጋ አባቶች ተረት፣ ምሳሌያዊ አነጋገር እንዲሁም የተለያዩ ጨዋታዎች ያመጡና እዚያ የተሰበሰባዉን ማህበረሰብ በጥሩ ሁኔታ ያስተምራሉ፡፡ ሀዘን የደረሳበት ቤተሰብም ሀዘኑን ትቶ የሽማግሌዎችን ትምህርት አዘል ተረት እና ምሰሌያዊ አነገገር በጥሞና ያዳምጣል እንድሁም ይማራል፡፡ ጎረቤቶች የራሳቸዉን ሳይሆን ሀዘንተኛዉን ነዉ የሚያስቀድሙት፤ ኣንድ ላይ በመሆን ወይም በቡድን ሰዉ የሞተበትን ሰዉ ስራ ይሰራሉ፡፡(ቃ.መ 04/08/13)

“Duuti sabbata qabdi” ሞት ሰዉ እንዳይከፋዉ የሚታደርግበት ቀበቶ አላት

“Duutun du’a irraa hin haftu” ደካማ ሰዉ ከሞት አይተርፍም

“Duuti daandii Waaqayyooti” ሞት ከፈጣሪ ዘንድ ነዉ

“Du’aan fira argan” በሞት ሰብያ የቅርብ ዘመድ ይገናኛል

“Kan jaallatu fudhate” ፈጣሪ የወዳደዉን ሰዉ ነዉ የወሰደዉ

“Jireenyaa lafa gahanii du’aa lafa hin hanqatan” በህይዋት ሲወለዱ ምድር ላይ ተገኝተዉ በሞት ደግሞ ከመሬት አይቀርም

“Namni kamuu achuma deema” ማንም ሰዉ ወደዝያ ነዉ የሚሄደዉ

## 2. እድርተኞች

ኣንድ ሰዉ ከእድራቸዉ ከሞተ ሁሉ የእድሩ አባላት የመገኘት ግዴታ ኣለባቸዉ፡፡ እድርተኞቹ በለቅሶዉ ላይ የተወሰነዉን የወጭ ብር እና እህል ያዋጣሉ (ኣዋጥተዉ ካስቀመጡት ዉስጥ) ይሰጣሉ፡፡ ሌላ ደግሞ እንጀራ ያመጣሉ፡፡ ወንዶቹ ግማሾቹ ቀየ ዉስጥ የሚሰራ ስራ ያለ ምንም እረፍትሲሰሩ ሌላዉ ደግሞ ለቅሶዉን ላልደራሰ ሰዉ ለመንገር ሲሄዱ ግማሹ ወፍጮ ቤት ይሄዳል፡፡ ለቅሶ ከገባ ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ሳምንት ተራ በተራ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሞት ተናግሮ ኣይመጣም “ዱት ህመቴ ህንዱፍቱ” ነግ በኔ በማለት ሴቶቹም የማገዶ እንጨት በማምጣት እንዲሁም ከቤታቸዉ ቆሎ በማምጣት ለቅሶ ቦታ ደግሞ ወጥ በመስራት እንጀራ በመጋገር ንፍሮ በመጣድ

ቡና በማፍላት የተጠመቀዉን ጠላ በማቅረብ እየተጋገዙ ይሰራሉ፤ ማንም በዚህ ቦታ በችላባይነት አይገኝም (ቃ.መ 03/08/13) ፡፡

3. ጓደኞች

አንድ ሰዉ ከጓደኛዉ ዘመድ ከሞተ የለቅሶ ቀን ጓደኛዉ መስተንግዶውን አስተካክልልኝ ብሎ የነገረዉን ሁሉ ያስተካክልለታል፡፡ ለቅሶዉ ላይ ምንም ነገር እንዳይጠፋ ሀላፊነት ይወስዳል፡፡ እድርተኞችም ጎረቤትም በዚህ ሰዉ ይመራሉ፡፡ ሁሉንም ክዋኔ ፈር የሚያሲዝ እሱ ነዉ፡፡ በለቅሶዉ ቀን እንዲህ ሲሰራ ከርሞ የስራ ገበታ ላይ ካለ የሚኖርበት እሩቅ ከሆነ በማግስቱ ይሄድና በሳምንቱ እንደአቅሙ እንጀራም ደቦም ሊሆን ይችላል ከቡና ጋር ይዞ ይመጣል፡፡ አቅም ያለዉ ሰዉ ከሆነ የሚታረድ በግ ወይም ፍየል ያርዳል ወይም በድሮ ዘመን ሁለት ብር እና አምስት ብር ነበር ሲሰጥ የነበረዉ በአሁኑ ጊዜ ግን ከሃምሳ (50) ብር እስከ መቶ (100) ከዚያም ኣልፎ አምስት መቶ (500) እስከ ኣንድ ሺ (1000) ብር እና በላይ የሚሰጥበት ሁኔታ ኣለ፡፡ ሟቹ ብዙ ልጆች ካለሉት ማንም ሰዉ አቅሙ እንደፈቀዳለት ከሃምሳ (50) ብር ጀምሮ ለሁሉም ይሰጣል ማለት ነዉ፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ በወሊሶ ኦሮሞ ላይ ኪሳራ እያደረሰ ያለ ድርግት ነዉ፡፡ በዚያ መልኩ ያስተዛዝናሉ ማለት ነዉ፡፡ ሌላዉ ጓደኛዉ በሀዘን እንዳይጎዳ ለማድረግ ጊዜ አመቻችተዉ ጓደኞቹ ብዙ አይነት ጨዋታዎች "ሰዴቀ" ማለት ከእንጨት የተሰራ ለጨዋታ የሚጠቀሙበት ነዉ፡፡ ኣሁን ኣሁን ግን እሱ ቀርቶ ካርታ በዘመናዊ መልኩ ሲጫወቱ ይታያል፤ ሀዘንተኞችን ማስተዛዘን ቀርቶ በካርታዉ የሚገኝ ሳንትም ላይ ሲደባደቡ ይታያሉ፡፡ ይህ እንግድህ ዘመን ያመጣዉ ጣጣ እንደሆነ ይታወቃል (ቃ.መ 02/08/13) ፡፡

**4.3.5.4. ለቅሶ የማህበረሰቡን ታሪክ፣ እምነትና አመለካከት ከመግለጽ አንጻር**

በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ የማህበረሰቡ ታሪክ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍበት፣ ስርዓት የሚዋቀርበት እና የሚከወንበትን አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ ብሄረሰቡ ታሪኩን በለቅሶ ክዋኔ ውስጥ የመግለጽ አቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ በስርዓቱ ላይ የሚታዩት ቁሳዊ ባህሎች እና ስነ ቃሎች የማህበረሰቡን ታሪክ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በለቅሶ ክዋኔው ላይ እምነትን የሚገልፁ ስርዓቶችም በርካታ ናቸው፡፡ ስርዓቶቹ ከሚንጸባረቁበት መንገድ አንዱ የ "ዲባዩ" ስርዓት ነው፡፡ ይህን የ "ዲባዩ" ስርዓት ማህበረሰቡ ከመንጻትና መስዋዕት ከማቅረብ ጋር ያያይዘዋል፡፡ በ "ኤኬሮ" ስርዓት ወቅትም ሆነ በሌሎች የለቅሶ ስርኣቶች ላይ የሚፈጸሙ ስርኣቶች ከማህበረሰቡ እምነት ስርዓት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህም የሟችን ነፍስ ለማስደሰት እንዲሁም ለፈጣሪ መስዋዕት ለማቅረብ ይደረጋል፡፡ ይህ

ባይደረግ ሟችም ሆነ ፈጣሪ በሟች ቤተሰቦች ላይ ችግር ሊያደርሱ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ አቶ ሞሮዳ ቶሌራ እንደሚገልጹት ሰዉ ሲሞት በርከት ያለ ስርአት ይፈጸማል፡፡ ይህም የሚሆነው ኣንድም ለፈጣሪ ሌላም ደግሞ ሰውን ለማስደሰትም ጭምር ነው፡፡ የ "አባ ገዳ" ለቅሶ ጊዜ ብዙ ስርአት ይደራጋል፡፡ ይህም የአባታችንን ነፍስ በጥሩ ሁኔታ እንዲቀበልልን ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ 11/08/13) በስርዓቱ ላይም ከክዋኔው በስተጀርባ የእምነት ጉዳይም መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡ የማህበረሰቡን አመለካከት በስርዓቱ ላይ ስንመለከተው በስርዓቱ ውስጥ "ድባዩ"ን ማዘጋጀት፣ ጦር ጋሻና የጦር መሳርያዎችን መጠቀም፣ አካልን በመጉዳት፣ መነሳት መውደቅ፣ የቆሸሸ መልበስ የሟችን ማህበራዊ ደረጃ እና ለሟች ያላቸውን ፍቅር ይገልጻል የሚል አመለካከት ኣላቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በምትገኝ ከሊበን ልጆች አንዱ በሆነዉ በወሊሶ ኦሮሞ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ትንተና ላይ ነዉ፡፡ የጥናቱ ዋንኛ ዓላማ የነበረው "የማህበረሰቡን የለቅሶ ስርዓት ከሞት እስከ ግብዓተ መሬት ፍፃሜው ድረስ ያለውን የአከዋወን ሂደት ማሳየትና መተንተን ነው፡፡" በመሆኑም ይህን ዓላማ እና ሌሎች ዝርዝር ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ በሁለት ተፈጥሯዊ መቼቶች ላይ ተገኝቼ ምልከታ በማድረግ፣ ስለ ማህበረሰቡ ባህል ጥልቅ መረጃ ካላቸው የተለያዩ አካላት ጋር ቃለመጠይቅ እና የቡድን ውይይት በማካሔድ በቂ መረጃ ለማግኘት ችዬዋለሁ፡፡

የተገኙት መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የወሊሶ ኦሮሞ የለቅሶ ስርዓት ምን እንደሚመስል በአግባቡ ለማሳየት ይበጅ ዘንድ "ለህፃናት የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት"ን እና "ለአዋቂዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት"ን በቅድመ ሞት እና ጊዜ ሞት እንዲሁም በቅድመ ቀብር፣ ጊዜ ቀብር እና ድህረ ቀብር በሚሉ እርከኖች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ቅድመ ሞት በሚለው እርከን ውስጥ ማህበረሰቡ አንድ ሰው ለሞት የተቃረበ መሆኑን ሲገምት የሚያከናውናቸውን ልዩ ልዩ ተግባራት የሚመለከት ሲሆን በጊዜ ሞት ስር የቀረቡት ደግሞ ኣንድ ሰው ህይዋቱ ስታልፍ የሚፈፀሙ ክንውኖችን የሚያሳይ ነው፡፡ በወሊሶ ማህበረሰብ ዘንድ ኣንድ ሰው ከሞተ በኋላ በየደረጃው የሚከናወኑ ተግባራት ደግሞ በቅድመ፣ ጊዜ እና ድህረ ሞት ክዋኔ ስር ተተንትነዋል፡፡

የወሊሶ ኦሮሞ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ አጠቃላይ ሂደት ከቅድመ ሞት እስከ ግብዓተ መሬት ድረስ ሊፈጅ እንደሚችል በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ ይህ ጊዜ አንድ ሰው ከተቀበረ በኋላ ያሉትን የመታሰቢያ ቀናቶች የሚያካትት ነዉ፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ደረጃ እና ኢኮኖሚያዊ አቅም ባገናዘበ መልኩ ከቀብሩ በፊት ለሚፈፀሙ ልዩ ልዩ ስርዓቶች መከወኛ የሚሆን መሆኑ ታውቋል፡፡ በዚህ ወቅት ከሚፈፀሙ ስርዓቶች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት በየአካባቢው ያሉ የማህበረሰቡ ተወላጆች በቀብሩ ዕለት ወገናቸውን ተገኝተው እንዲቀብሩ ለማስቻል፣ ለዝግጅት የሚፈልገውን ባህላዊ ምግብ እና መጠጥ ለለቀስተኞች ለማዘጋጀት፣ በሟች ማሳ ውስጥ መፈፀም ያለባቸውን የእርሻ ስራዎች ለማከናወን፣. . .ወዘተ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

በእርግጥ እድሜ፣ ፆታ እና ማህበራዊ ደረጃ በማህበረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅት የሚፈጥሯቸው የተወሰኑ ልዩነቶች መኖራቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም ሟች

የአካባቢው "ሃደ ስቄ" የጎሳ መሪ ወይም "አባ ገዳ" ከሆነ ሌላም ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ስልጣን ካለዉ በእዉቀቱ እና በንብረቱ ማህበረሰቡን ያገላገለ ከሆነ ልጅ ከሌላዉ ከሌላው ህብረተሰብ ለቅሶ ይልቅ ሰፋ ባለ እና በደመቀ መልኩ እንደሚከወን ተስተውሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከእነዚህም በላይ ዋንኛው የልዩነት ምንጭ ሟች ወይም የሟች ቤተሰብ ያላቸው ኢኮኖሚያዊ አቅም መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንደ ማህበረሰቡ አባላት እምነት የአንድ ሰው የለቅሶ ስርዓት የሚደምቀው ከቀብሩ በፊት በሚሰናዱት ዝግጅቶች ልክ ነው፡፡ ከዝግጅቶቹ መካከል ደግሞ የሌሎች ቅድመ ዝግጅቶችን ስፋት እና ጥበት የመወሰን አቅም ያለው ለለቀስተኞች የሚሆንን ምግብ እና መጠጥ በስፋት ማዘጋጀት ነው፤ ለዚህ ዝግጅት ከሚያስፈልገው በርከት ያለ ጤፍ በተጨማሪ ቆሎ ማባያ የሚሆን ለወጥ የሚሆን ስጋ ይመጣል ተብሎ በሚገመተው ሰው ልክ ታርዶ ስቀርብ ነዉ፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ወይ ሟች አሊያም ቤተሰቦቹ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው ከፍ ያለ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም የኢኮኖሚ አቅም ለለቅሶ ስርዓቱ ድምቀት ወይም መደብዘዝ ከፍ ያለ ሚና የሚጫወት መሆኑ ታውቋል፡፡

በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ኣንድ ህፃን ጥርስ ከማብቀሉ በፊት የሚሞት ከሆነ የለቅሶ ስርዓቱ ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል በእጅጉ የሚለይ መሆኑ ታውቋል፡፡ በወሊሶ ኦሮሞዎች ዘንድ አንድ ህፃን ከእናቱ እቅፍ ሳይወርድ በሞት የተነጠቀ እንደሆነ "ህፃኑ ኃጢያተኛ ስለሆነ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለመረጠው ነው የወሰደው" የሚል ፅኑ እምነት አለ፡፡ በመሆኑም ለዚህ ህፃን ብዙ አይለቀስም፣ ደረት አይደቃም፣ ፊት አይቧጠጥም፡፡ ይልቁንም ብዙም ሰው ሳይሰማ ጎረቤታሞች ብቻ ተሰባስበው እናት እርሟን ለማውጣት ያህል ብቻ ድምፅ ሳታሰማ አልቅሳ እንድትሰናበተው ኣድርገው የህፃኑን አስክሬን ቤት ዉስጥ የሚቀብሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ የሚሆነው ልጁ ርቆ ከተቀበረ ደም ነዉ መራቅ የለበትም ይባላል፡፡ ሌላው በጥናቱ የተደረሰበት መሰረታዊ ነገር የወሊሶ ማህበረሰብ በቀብሩ ዕለት የሚፈፀመውን መሪር ሀዘን የሚያሳርገው "ኦፌን" በተባለ በሙሾ ግጥም ነው፡፡ ይህ ግጥም የሟችን እና የቤተሰቦቹን መልካም ገፅታዎች የሚያወሱ፣ ሞት ለሁሉም የቀረበ ግዴታ መሆኑን የተመለከቱ፣ ሞት ዳግም የሟችን ቤተሰቦች እንዳይጎበኝ የሚመኙ፣…ወዘተ ግጥሞችን ለቀስተኞቹ እየደረደሩ በእግርና በፈረስ ሀዘናቸዉን ከዉስጣቸዉ እንድያወጡ የሚል መልዕክት እንዲያስተላልፍም ታስቦ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ኣንድ ሰዉ ትዳር መስርቶ በሚኖርበት ዘመን ልጅ ከሌላዉ ስሙ እንድቀጥል ለማድረግ የኤኬሮ ልጅ ስሙን ያስጠራል በማለት ከቤተሰቦቹ ወንድ ልጅ በመዉሰድ ስሙን ሰይመዉ የሚቹ ልጅ እንድሆን ይደረጋል፡፡ ሌላዉ ደግሞ በለቅሶ ላይ የሚያዙ ቁሶች ራሱን ችሎ ትዕምርት እንዳለዉ ማህበረሰቡ ቁሱን

በማየት ብቻ የሚማራዉ ሁኔታ መኖሩ በጥናቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሌላዉ ደግሞ አንድ ታዋቂ ሰዉ ከሞተ በማህበረሰቡ ደንብ ፈረስን ቀሚስ በማልበስ አንድ ሰዉ ሲጎትተዉ ሌሎቹ ደግሞ በሰልፍ እሱን በመከተል የሟቹን ጀግንነት እና ታዋቅነት በማሰብ በደመቀ ሁኔታ የሚያለቅሱለትም ሀገረሰባዊ ልማድ እንዳለም ታዉቋል፡፡

በወሊሶ ማህበረሰብ የአዋቂዎች ቀብር የሚፈፀመው በሁለት የተለያዩ አካባቢዎች ነው፡፡ አንደኛው በሟች መኖሪያ ቤት አቅራቢያ በሚገኝ የሟች ግቢ ውስጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአንድ አካባቢ የሚገኙ ሰዎች በጋራ ተስማምተው ኮረብታማ ስፍራ ላይ የሚያሰናዱት ነው፤ ይህ የሀይማኖት ተቋማት የቀብር ስፍራዎችንም የሚያካትት ይሆናል፡፡ በሁለቱም መካነ መቃብሮች ቀብር በሚፈፀምበት ወቅት ዛፎችን በመቃብሩ ዙሪያ መትከል የተለመደ ተግባር ነው፡፡ የወሊሶ ማህበረሰብ ማህበራዊ ትስስሩን ከሚያጠነክርባቸው እና ኢኮኖሚያዊ አቅሙን ከሚገልጥባቸው ባህላዊ ክዋኔዎቹ መካከል "የለቅሶ ስርዓት" ቀዳሚውን ስፍራ እንደሚይዝ ታውቋል፡፡ የለቅሶ ስርዓት የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ እሴቶች የሚገለጡበት፣ የሚፀኑበት እና ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉበት ሁነኛ መድረክ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

## 5.1 ለቀጣይ አጥኚ ያለኝ አስተያየት

1. ይህ ጥናት በወሊሶ ሊበን ኦሮሞ ማህበረሰብ ለይ ብቻ ያተኮረ ነዉ፡፡ በአጎራባች የሚገኙ የአመያና የኩታዬ ሊበን የሆኑ የኦሮሞ ማህበረሰብ የወሊሶ ሊበን ወንድማማቾችን በጥናቴ ማቀፍ ሲላልቻልኩኝ ቀጣይ አጥኚ በእነዚህ ማህበረሰቦች ላይ ቢሰራ የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

2. ጥናቴ በወሊሶ ኦሮሞ ማህበረሰብ ላይ ትኩረት በማድረግ በወሊሶ ከተማና አካባቢዉ የሚኖሩ ሌሎች ብሔረሰቦችን ስላለካተተ ቀጣይ አጥኚ በዚህ ላይ ጥናት ብያደርግ ጥሩ ይመስለኛል፡፡

3. ጥናቴ በተላያየ ንዑስ ዓላማዎች ላይ ስላተኮራና ሰፊ በመሆኑ ምክንያት ዉስን ጉዳይ ላይ ጥልቅ ጥናት ስላልተደረጋ ቀጣይ አጥኚ በተለይ የማህበረሰቡ የለቅሶ ስርአት በግዜ ሀደት እየተቀየረ የመጣበትን ምክንያት በጥልቀት እራሱን በቻለ ርዕስ ቢያጠና መልካም ነዉ የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች

ለማ ከበደ፡፡ (2010)፡፡ "የወሊሶና አካባቢዉ ሽምግልና (ጃርሱማ) ስርዓት አፈጻፀም ትንተና"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአፋን ኦሮሞ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ያልታተማ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡

ሕይወት አበሩ:: (2003)፡፡ "የመኢኔት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርአት ክዋኔ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ያልታተማ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡

ማናዬ እንግዳወርቅ፡፡ (2005፡፡ "በደብረማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ንጽጽራዊ ጥናት፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ያልታተማ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡

ሜሮን ሞላ፡፡ (2011)፡፡ "በጭላጋ ወረዳ በክመንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ፡፡"ያልታተማ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡ አድስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

ሰሎሞን ተሸመ፡፡( 2007)፡፡ ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡ አዲስ አበባ፣ ህትመት ፋር ኢስት ኃላ.የተ.የግ.ማ፡፡

አለም እሸቴ፡፡ (2001)፡፡ *"በመሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ፡፡"*

ኡርጌሳ ጥላሁን፡፡ (2009)፡፡ "በፈረስ አጠቃቀም ወቅት የወሊሶ ኦሮሞ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአፋን ኦሮሞ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ያልታተማ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992)፡፡ *የስነ-ጽሁፍ መሰረታውያን፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ (1992)፡፡የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡(6ኛ ዕትም)፣ አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ (1993)፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

የወሊሶ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ቢሮ ሚያዝያ፡፡ (2009) ያልታተመ

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2004፣178-192)፡፡ <u>የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡</u> (ሦስተኛ እትም)፣ አድስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አየሁሽቶማ፡፡(2005)፡፡ "የወላይታ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ያልታተማ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡

ውቤ ታደገ፡፡ (2005)፡፡ "የቤንች ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ያልታተማ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡

ዘላለም ፋንቴ፡፡ (2004)፡፡ "የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ያልታተማለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡

Bauman, Richard. (1977). *Verbal Art as Performance*. Rowley, Mass: Newbury House Publishers.

Bauman, Richard, ed. (1992). *Folklore cultural performances and popular Entertainment*. New York: Oxford University Press.

Bauman, Richard. (1975). Story, Performance and Event: *Contextual Studies of oral Narrative*. Cambridge: Cambridge University Press.

Dejene Gemechu. (2002). *Some Aspects of Conflict Resolution Among Woliso Oromo of Eastern Macha, with Particular Emphasis on the Guma.* Addis Ababa University, Departiment of Afan Oromo, Literature and folklore.

Dorson, R.(1972). Folklore and Foklife: an Introduction. Chicago: The University of Chicago.

Finnegan, Ruth. (1992). Oral Poetry: *Oral Tradition and the Verbal Arts:* A Guide to Research Practices. New York: Thomson Publishing Company.

Hertiz, Robert. (1960) *Death and the Right Hand*. Trans. Rodney and Need ham, Claudia. Aberdeen: Aberdeen University Press.

Kruger; Richard. (1977). Focus Groups: *A Practical Guide for Applied Research*. New bury Park, CA Stage.

Sims, Martha C. and Stephens, Martine. (2005). Living Folklore*. An Introduction to the study of people and their Traditions*. USA, Utah State University Press.

World Book Encyclopaedia. (1978). World book —child craft International, Inc. Vol, 7.USA.

## አባሪ(1) የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | ስም | ዕድሜ | ጾታ | የት/ት ደረጃ | ስራ | የመኖሪያ አካባቢ | የሰጡት መረጃ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምህረቱ ኩመላ | 75 | ወ | 6ኛ | ኣርሶ ኣደር | ወሊሶ ወረዳ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | ቁልፍ መረጃ አቀባይ |
| 2 | ከበደ ቀልቤሳ | 71 | ወ | 8ኛ | ›› | ወንጪ ወረዳ | ታሪከዊ ዳራን በተመለከተ | “ |
| 3 | ፉርጋሰ ሁንዴ | 69 | ወ | 8ኛ | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 4 | ሀምብሳ መርጋ | 68 | ወ | 6ኛ | ›› | ጎሮ ወረዳ | ›› | ›› |
| 5 | ሚደግሳ ጫልችሳ | 67 | ወ | 7ኛ | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 6 | “ፎሌ”ብሊሱማ ሚደግሳ | 20 | ወ | ቢኤ ድግሪ | ›› | ›› | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | ›› |
| 7 | በዳደ ርቂቲ | 70 | ወ | 8ኛ | ›› | ›› | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | ›› |
| 8 | ረፉ ጎንፋ | 65 | ወ | 7ኛ | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 9 | መሀመድኑር | 72 | ወ | 8ኛ | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 10 | ሞስሳ ተፈራ | 74 | ወ | 8 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 11 | ነገሱ አምዲሳ | 58 | ወ | ድግሪ | ባህልና ቱሪዝም ባለ ሞያ | ወሊሶ ከተማ | ›› | የተ.ቡ. ዉ. |
| 12 | ደራሬ አበራ | 52 | ሴ | 9ኛ | ኣርሶ ኣደር | ወንጪ ወረዳ | ›› | ›› |
| 13 | ሸዋዬ ባይሰ | 54 | ሴ | 5ኛ | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 14 | ቦጋሌ ባይሳ | 56 | ሴ | 4ኛ | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 15 | ደሜ አለሙ | 42 | ሴ | ዲፒሎማ | የእድር ሰብሳቢ | ›› | ›› | ›› |
| 16 | ሙሉ ዳበሳ | 46 | ሴ | 8ኛ | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 17 | ዳበሳ ከፈኒ | 74 | ወ | 4ኛ | ›› | ›› | ታሪካዊ ዳራን በተመለከተ | ›› |
| 18 | “አባ ገደ” ተስፋዬ | 72 | ወ | 8ኛ | የጎሳ መሪ | ወሊሶ ወረዳ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | ›› |
| 19 | ሞሮዳ ቶሌራ | 62 | ወ | ዲግሪ | ባህልና ቱሪዝም ባለሞያ | ወንጪ ወረዳ | ›› | ቁልፍ መረጃ አቀባይ |
| 20 | ገመቹ ታመና | 28 | ወ | ዲግሪ | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 21 | “ሃደ ሲቄ” | 70 | ሴ | 6ኛ | “ሃደ | ›› | ›› | ›› |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወጋየሁ ንጋቱ | | | | ሲቄ” | | | |
| 22 | ጠጂ ዳበሳ | 70 | ሴ | 4ኛ | ኣርሶ ኣደር | ›› | ›› | ›› |
| 23 | ፋንቱ ለማ | 68 | ሴ | 12ኛ | የእድር አባል | ›› | ›› | ›› |
| 24 | ሰናይት አበበ | 65 | ሴ | 10ኛ | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 25 | ማርታ አየለ | 72 | ሴ | 8ኛ | ›› | ›› | ›› | ›› |

**አባሪ (2)፡-** በቃለ-መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉ መነሻ ጥያቄዎች፣

የወሊሶ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት-ክዋኔ ለመዳሰስ የተዘጋጀ የቃለ-መጠይቅ መነሻ ጥያቄ

ቃለ-መጠይቁ የተደረገበት ቀን-----------------------------------

» » የተካሄደበት ቦታ-------------------------------------

» » የተጀመረበት ሰዓት------------------------------------

የቃለ-መጠይቁ ሰጪ አጠቃላይ መረጃ፡-

ስም ----------------------------------------

ፆታ ----------------------------------------

ዕድሜ----------------------------------------

የአፍ መፍቻ ቋንቋ. . . . . . . . . . . .

የትምህርት ደረጃ----------------------------

ስራ------------------------------------------

የአካባቢ ቆይታ ጊዜ--------------------------

የትዳር ሁኔታ -------------------------------

ለቃለ-መጠይቁ የሚረዱ መጠይቆች፡-

1. የወሊሶ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ (በአጎራባች ከሚገኙ ሌሎች ብሔሮች የተለየ) የለቅሶ ስርዓት አለው? ካለው ስርዓቱ እንዴት ይከዊነል?

2. የለቅሶ ስርዓቱ እንዴት እና በምን አይነት ሁኔታ ይከናወናል?

3. የለቅሶ ስርዓቱ በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ የስልጣን፣ የማህበራዊ ደረጃ፣ የእድሜ፣ የፆታ፣ የጎሳ፣. . .ወዘተ ልዩነቶች ሳቢያ ክዋኔው ይለያያል ወይስ አንድ ነው ? የሚለያይ ከሆነ ልዩነቶቹ እንደምን ያሉ ናቸው ?

4. በማህበረሰቡ ውስጥ ልዩ ልዩ ባህላዊ ስልጣን ያላቸው (ማህበረሰቡ ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው ሰዎች ለምሰሌ "አባ ገዳ"፣"ሀደ ስቄ" "ጉላ"ሲሞቱ) የሚደረግ የተለያየ

የለቅሶ ስርዓት አለ? ካለ ከቀብር በፊት፣ በቀበር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ  የሚፈፀሙት ስርዓቶች እንደምን ያሉ ናቸው ?

5. በማህበረሰቡ ውስጥ "ተራው" የማህበረሰብ አካል ሲሞት የሚፈፀሙ የተለያዩ የለቅሶ ስርዓቶች አሉ? ካለ ከቀብር በፊት፣ በቀበር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ የሚፈፀሙት ስርዓቶች እንደምን ያሉ ናቸው ?

6. በማህበረሰቡ ውስጥ ህፃናት ሲሞቱ የሚፈፀሙ የተለያዩ የለቅሶ ስርዓቶች አሉ? ካለ ከቀብር በፊት፣ በቀበር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ የሚፈፀሙት ስርዓቶች እንደምን ያሉ ናቸው ?

7. በለቅሶ ስርዓቱ ወቅት ለሟች የሚገጠሙ፣ የሚዜሙ፣ የሚቅራሩ፣ የሚፎከሩ፣. . .ወዘተ ግጥምና ዜማዎች ካሉ በማን እና እንዴት ይዜማሉ ? ጠቀሜታቸውስ ምንድነው ተብሎ ይታመናል. . . ?

8. በለቅሶው ወቅት የሚለበሱ፣ የሚያዙ፣ በልዩ ልዩ አካላት ላይ የሚታሰሩ፣. .ቁሶች ካሉ አገልግሎታቸው? ቁሶቹ ራሱን የቻለ ትዕምርት አለዉ?

9. የቀብር ስርዓት ተዘወትሮ የሚፈፀምበት እራሱን የቻለ ቦታ አለ? ካለው ለምን ? የቀብር ቦታ ስንት ነዉ? ለምንስ ይለያየል?

10. የግንዘት ስርዓቱ የሚከናወነው እንዴትና በማን ነው? ለሁሉም ሟች የሚደረገው የአገናነዝ ስርዓት አንድ ወይስ የተለያየ ነው ?

11. አንድ ሰው በሞተ በስንት ቀን ውስጥ ቀብር መፈፀም ይኖርበታል?

12. ለሟች ወገን የሚደረግ የተለየ ነገር አለ?

13. በለቅሶ ስርዓቱ ወቅት ይህ የወንዶች፣ ያኛው ደግሞ የሴቶች ተብሎ የሚለይ የአከዋወን ስርዓት አለ?

14. በቀብሩ ወቅት እነማን ይታደማሉ/ የቀብር ቦታው ድረስ እነማን በምን አይነት አኳኋን ይሄዳሉ? ለምን ?

15. በማህበረሰቡ ውስጥ እድር ሚናው እንዴት ይገለፃል?

16. መጠየቅ ነበረብኝ ብለህ የምታምነው ሌላ ጥያቄ ካለ ብትገልፅልኝ?